

ኢስላም እና ሙስሊሞች

የእምነት ጥልፍ

ሰማህ ማሪ

بسم الله الرحمن الرحيم

በ አላህ ስም አጅግ በጣም ሩህሩህ
በጣም አዛኝ በሆነው

ዛኢባተ ከኢስላም ጋር የመተዋወቂያ መጻሕፍት ቅጽ

ኢስላም እና ሙስሊሞች፥ የእምነት ጥልፍ፥ በሰማህ ማሬ

ኢስላም እና ሙስሊሞች

© Zayed House for Islamic Culture 2015

Published by
ZAYED HOUSE FOR ISLAMIC CULTURE
P.O. BOX 16090, AL-AIN, UNITED ARAB EMIRATES
TEL 800555 FAX +971 3 7810633
WWW.ZHIC.AE CONTACT@ABUDHABI.AE

ISBN 978-9948-22-056-5

Commissioned by Zayed House for Islamic Culture, UAE.
Produced by Razi Group, Canada, under the supervision
of Tabah Foundation, UAE.

ALL RIGHTS RESERVED. Aside from fair use, meaning a few pages or less for nonprofit educational purposes, review, or scholarly citation, no part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording, or otherwise, without the prior permission of the Copyright owner.

ZHIC has no responsibility for the persistence or accuracy of URLs referred to in this publication, and does not guarantee that any content on such websites is, or will remain, accurate or appropriate. All information is correct as of November 2009, but ZHIC does not guarantee the accuracy of such information thereafter.

Printed in UAE
© Zayed House for Islamic Culture 2015

አሳታሚ
ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም
ፖ.ሳ.ቁ 16090፣ **አል ዓይን፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች**
ስልክ 800555 **ፋክስ** +971 3 7810633
ድረ ገፅ፣ WWW.ZHIC.AE **ኢ. ሜይል፣** CONTACT@ABUDHABI.AE

የዚህ መጽሐፍ ህትመት ወጪ የተሸፈነው ተቀማጭነቱ በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች በሆነው ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም (Zayed House for Islamic Culture) **ነው።። የመጽሐፉ ዝግጅት በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች በሚገኘው ጣባህ ፋውንዴሽን ተጠባባቂነት፣ ካናዳ በሚገኘው ራዚ ግሩፕ ተካሄደ።።**

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።። በህግ በተፈቀደው መሠረት ክትርፍ ጋር ተያያዥነት ለሌላቸው ትምህርታዊ ዓላማዎች፣ ለሒሳዊ ዳሰሳ፣ ወይም ለምሁራዊ ሥራዎች ማጣቀሻነት ካልሆነ በስተቀር፣ ከቅጂው ባለመብት በጽሑፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳይገኝ ከዚህ ህትመት ውስጥ አንዲትም አንቀፅ ቢሆን ማባዛት፣ በቤተ መዛግብት ማኖር፣ በኤሌክትሮኒክ፣ በሜካኒካዊ መንገድ፣ በፎቶኮፒ፣ በድምፅ መሣሪያ በመቅዳት፣ ወይም በሌላ በማንኛውም ቅርፅ ወይም መንገድ ማስተላለፍ አይቻልም።።

በዚህ ህትመት ውስጥ የተጠቀሱ ድረ ገፆችን ዘውታሪነት ወይም በውስጣቸው የሚገኙ መረጃዎችን ትክክለኝነት በተመለከተ ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም ምንም ዓይነት ኃለፊነትን አይወስድም፤ አንዲሁም በአነዚህ ድረ ገፆች ስለሚገኙ ማናቸውም ይዘቶች ትክክለኛነት ወይም ተስማሚነት ዋስትና አይሰጥም።። በዚህ ህትመት ውስጥ ያሉ መረጃዎች እስከ ኖቬምበር 2009 **ባለው ጊዜ ውስጥ ትክክለኛ ናቸው፤ ያም ሆኖ ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜ የመረጃዎቹ ይዘትም ሆነ ትክክለኛነትን በተመለከተ ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም ዋስትና አይሰጥም።።**

የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ውስጥ ታተመ
© ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም 2015

ሁለተኛ እትም 2015

ኢስላም እና ሙስሊሞች

የእምነት ጥልፍ

ሰማህ ማሪ

ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም
አል ዓይን፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች

ምስጋና

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይድረሰው፣ የሁላችንም ጌታ ለሆነው። የቤተሰቦቼ፣ ወላጆቼ፣ የባለቤቴ ወላጆች፣ ወንድሜ፣ ልጆቼ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ምንጊዜም ትዕግስት የማይለየውና የደጉ ባለቤቴ የሙርተዳ ድጋፍና ማበረታታት ባይታከልበት ኖሮ ይህ መጽሐፍ ሊጻፍ አይችልም ነበር። ባለቤቴ የነቢያዊ ባህሪ እውነተኛ ምሳሌ ነው።

ዕውን ልናደርግ ከተነሳነው ሥራ ጋር በተገናኘ እጅግ ጠቃሚ እና ድንቅ ሐሳቦቻቸውን ከሚያጋሩ የምርጥ አርታዒያን ስብስብ ጋር የመሥራት ፀጋን ታድያለሁ፤ እነርሱም ለእኔ ሐሳብ እና አስተያየት ዋጋ በመስጠት የአጠቃላይ ሐሳባችንን አሻራ በዚህ ፕሮጀክት ላይ አሳርፈዋል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ግድፈት ቢኖር ግድፈቱ የእኔ ብቻ ሲኾን፣ በተባረከው አንባቢዬ ልብ ውስጥ ቦታ ያገኘ ማንኛውም ነገር ከአላህ ነው።

ስለ ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም

ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም ለተወሰነ ዓላማ የተቋቋመ፣ ከልዑል አልጋ ወራሹ ሸንጎ ጋር ተቀራርቦ የሚሠራ ነፃ ተቋም ነው። ተቋሙ የተመሠረተው በቀድሞው የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ገዢ ሸይኽ ዛይድ ቢን ሡልጣን አል ናህያን ሲኾን፣ እ.አ.አ በ2005 በክቡርነታቸው ሸይኽ ኻሊፋ ቢን ዛይድ አል ነህያን፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ፕሬዚደንት እና የአቡዳቢ ገዢ በፀፋ ተመርቆ ሥራውን ጀምሯል።

ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም ኢስላማዊ ባህልን በማስፋፋት በተለያዩ ብሄሮች መካከል የግንኙነት ድልድይ በመገንባት ላይ ያተኮሩ ስራዎችን ያከናውናል። ተቋሙ ስለኢስላም እና ኢስላማዊ ባህል የማወቅ ፍላጎት ያላቸው አዳዲስ ሙስሊሞችና ግለሰቦችን በደስታ ይቀበላል። ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም አዳዲስ ሙስሊሞች ከማኅበረሰብ ጋር ውህደት ለመፍጠር የሚረዳቸውን ርዕይና አቅጣጫ በመስጠት በበርካታ ቋንቋዎች ለማስተማር ያለመ ልዩ ትምህርታዊ መርኃ ግብር አበልጽጓል። በተጨማሪም፣ የቁርአን የቃል ጥናት እና የአረብኛ ቋንቋ፣ የሐጅ አገልግሎቶች፣ የህዝብ ቤተ መጻሕፍት፣ እንዲሁም ባህላዊና በአንድ ጭብጥ ላይ የተመሠረቱ የጉዞ ሁነቶችና ስፖርቶችን የመሳሰሉ ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተቱ ልዩ መርኃ ግብሮችን ያቀርባል።

ጥቂት ስለ ሸይኽ ዛይድ



ሸይኽ ዛይድ እ.አ.አ በ1918 በአል ዓይን ከተማ ተወልደው አብዛኛውን የህፃንነት ጊዜያቸውን በዚያው አሳልፈዋል። የአቡዳቢ ገዢ ሆነው በርካታ የስኬት ዓመታትን ካሳለፉ በኋላ፣ እ.አ.አ በ1971 በአዲስ መልክ የተመሠረተውና ዋና ከተማዩቱን አቡዳቢን ጨምሮ የሰባት ኤሚሬቶች ፌደሬሽን የሆነው የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች መሪነትን ጨብጠዋል። ሸይኽ ዛይድ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶችን እጅግ ፈጣን ለውጥ በሚታይበት ወቅት ላይ በመምራት፣ ለአያሌ አሥርት ዓመታት ከባድ ችግሮችን ላሳለፈው አካባቢ ሀብት፣ ትምህርትና መልካም ዕድሎችን አስገኝተዋል። ሸይኽ ዛይድ በህዝቡ እና በአገሩ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበራቸውና፣ በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ውስጥ የአብሮ መኖር፣ የመቻቻል እና የመከባበር ባህል እንዲዳብር ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ሰው ነበሩ። ሸይኽ ዛይድ እ.አ.አ. በ2004 ከዚህች ዓለም የተለዩ ሲኾን፣ አቡዳቢ ውስጥ ከሚገኝውና በስማቸው ከሚጠራው ታላቅ መስጂድ አጠገብ ቀብራቸው ተፈጽሟል። በዙፋናቸውም ላይ የበኩር ልጃቸው የተከበሩ ሸይኽ ኻሊፋ ቢን ዛይድ አል ናህያን ተተክተዋል።

መልዕክት ከዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም

ለአላህ (ሱ.ወ) ክብር ይገባውና በተባበሩት ዐረብ ኤመሬቶች ውስጥ ኢስላምን የሚቀበሉ ሰዎች ቁጥር በእጅጉ እየጨመረ መጥቷል ። የዛይድ ኢስላማዊ ባህል ማዕከል ከምስረታው አንስቶ ኢስላምን ለሚቀበሉ ሰዎች አስፈላጊውን እገዛና ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀሉበትን ሁኔታዎች እያመቻቸ ይገኛል። በዚህም መሰረት ስለ ኢስላም መሰረታዊና ወጥነት ያለው ስርኣተ- ትምህርት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ በመነሳት ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም ይህን በማኅበረሰቦችና ባህሎች መካከል የሚታይ የግንዛቤ ክፍተት ለማጥበብ ወይም ለመዝጋት በሚደረገው ጥረት ላይ መሪ ሚና ለመጫወት የሚጥር ተቋም ነው። ዓላማችን ውጤታማ የባህል ልውውጥ ሐሳቦችን በማራመድ፣ ህዝቦች በተሻለ ሁኔታ እርስ በእርስ እንዲተዋወቁና እንዳቸው የሌላውን እሴት እንዲያደንቁ መርዳት ነው። የዚህ ጥረት አንዱ ክፍል በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዐውድ የተሰናዱና ለዚህ ዓላማ ጠቀሜታ ያላቸው ስራዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ዓለምን ከኢስላም እና ከአንድ ቢሊዮን ከሚበልጡት ተከታዮቹ ጋር ማስተዋወቅ ነው።

ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም **ከኢስላም ጋር ተዋወቁ!** የተሰኘውን ይህን ተከታታይ ቅፅ ሲያቀርብ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል። በተከታታይ ቅፆች የሚቀርቡት ስራዎች በዘመናችን እጅግ የተዛባ ግንዛቤ ሰለባ በሆኑት ህዝቦች ዙርያ ለየት ያሉ እይታዎችን ያቋድሳሉ። ቅፆቹ የዘመናችንን የተለዩ ተግዳሮቶች ተረድቶ ተገቢ አፀፋ በመስጠት ዓላማ በመገናኛ ብዙኃን ውጤቶች ላይ የተካሄዱ ዙርያ መለስ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው።

በዚህ አጋጣሚ ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የሚገኘው ጧባህ ፋውንዴሽን እና ካናዳ የሚገኘው ራዚ ግሩፕ ይህ ልዩ እና ኪናዊ አቀራረብ የተላበሰ ፕሮጀክት እጅግ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ላደረጉት ያልተቆጠበ ጥረት ምስጋናውን ለማቅረብ ይወዳል። በዚህ ቅፅ ውስጥ የቀረቡት ሥራዎች ስለ ኢስላማዊ መርኖች እና ስለ ሙስሊም ህዝቦች አንባቢያንን በማሳወቅ ረገድ በጣም ጠቃሚ እንደሚሆኑ ተስፋ እናደርጋለን። ይህ አነስተኛ ጥረት የእርስ በርስ መግባባት፣ መልካም ፈቃድና ፍሬያማ የአብሮ መኖር ድልድይ ከመገንባት አኳያ የመጀመርያው እርምጃ ነው።

ዛይድ የኢስላማዊ ባህል ተቋም

ስለደራሲዋ

ሰማህ ማሬ The Whole Story የሚሰኘው ከመንግሥታዊና ከግል ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚተገበረው የብዝኃነት ሥልጠና መርኃ-ግብር ፈጣሪ ነች። ሙስሊሞች በየከተሞቻቸው ከባቢ ውስጥ ጥበባዊና አዎንታዊ በሆነ መልኩ እንዲሳተፉ የማበረታታት ዓላማ ባለው የቁርጡባ ፋውንዴሽን ውስጥ የቦርድ አባል ነች። በተጨማሪም ካናዳ ለሚገኘው የራዚ ግሩፕ የትምህርት ጉዳዮች አማካሪ ናት።

ሰማህ እ.አ.አ በ1996 ሎስ አንጀለስ ከሚገኘው ካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ ትምህርት የመጀመርያ ዲግሪዋን ተቀብላለች። ከዚህም በተጨማሪ በመካከለኛው ምሥራቅ የሴማዊ ቋንቋዎችን እና ባህል በማጥናት በርካታ ዓመታት አሳልፋለች። በቅርቡም በብዝኃነት (diversity) ላይ ያተኮረ የኮሌጅ መማሪያ መጽሐፍ የመጻፍ እንዲሁም አርትኦት የማካሄድ ሥራ ላይ ተሰማርታ ነበር። በአሁኑ ጊዜ በካናዳ፣ ኒያጋራ ውስጥ ከባለቤቷና ከልጆቿ ጋር ትኖራለች።

የአነባበብ መፍቻዎች

ا/آ/ى	አሊፍ	አ
ب	ባ	በ
ت	ታእ	ተ
ث	ሣ	ሠ
ج	ጂም	ጀ
ح	ሐ	ሐ
خ	ኻ	ኸ
د	ዳል	ደ
ذ	ዛል	ዘ
ر	ራ	ረ
ز	ዘይን	ዘ
س	ሲን	ሰ
ش	ሺን	ሸ
ص	ሷድ	ሷ
ض	ዷድ	ደ
ط	ጣ	ጠ
ظ	ዟ	ዘ /በጥርስና ምላስ/
ع	ዓይን	ዐ
غ	ገይን	ገ
ف	ፋ	ፈ
ق	ቃፍ	ቀ
ك	ካፍ	ከ
ل	ላም	ለ
م	ሚም	መ
ن	ኑን	ነ
ه	ሃእ	ሀ
و	ወው	ወ
ي	ያ	የ

የዐረብኛ ምሕጻረ ቃላት

(ሱ.ወ)፡- (ሱብሐነሁ ወተዓላ)
ከሁሉ ነገሮች የጠራና የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ።

(ሰ.ዐ.ወ)፡- (ስልል-ለል-ኂሁ ዐለይሂ ወሰልለም)
የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን።

(ረ.ዐ)፡- (ረዲየል-ላሁ ዐንሁ፣ ረዲየል-ላሁ ዐንሃ፣ ረዲየ-ላሁ ዐንሁም)
መልካም ስራውን ይቀበለው፣ መልካም ስራዋን ይቀበላት፣ መልካም ስራቸውን ይቀበላቸው።

(ዐ.ሰ)፡- (ዐለይሂ አስ-ሰላም)
የአላህ ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን።

ማውጫ

አንዳንድ ነጥቦች “ከኢስላም ጋር ተዋወቁ” ስለተሰኙት ቅጾች 1
መቅድም 3
መግቢያ 7

ክፍል አንድ፦ የኢስላም አስኳል

ምዕራፍ አንድ — አላህ — 13
ምዕራፍ ሁለት — መሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) — 23
ምዕራፍ ሦስት — ቁርአን — 33
ምዕራፍ አራት — ኢስላማዊ አስተምህሮ — 41
— ምስላዊ ወግ፦ አምልኮ — 50

ክፍል ሁለት፦ የኢስላም ሁለመና

ምዕራፍ አምስት — ሀያው ምሳሌ — 57
ምዕራፍ ስድስት — ተተኪዎች እና ቁሳሮች፦ ኢስላም ከነቢዩ በኋላ — 65
ምዕራፍ ሰባት — ምስላዊ ወግ፦ የምዕመናን ሀይወቶች — 74

ክፍል ሦስት፦ የላቁ አሴቶች እና እውነታዎች

ምዕራፍ ስምንት — የእንግሊዝ ጽጌረዳዎችና የደች ቱኪኘ አበቦች የኢስላም እና የምዕራቡ ዓለም አስደናቂ ታሪኮች — 83
— ምስላዊ ወግ፦ አደራውን መጠበቅ — 94
ምዕራፍ ዘጠኝ — የሰዎች መንትያ ክፋዮች — 99
ምዕራፍ አሥር — ምስላዊ ወግ፦ ኢስላም እና ባህል — 106
ምዕራፍ አሥራ አንድ — ፍትኅ እና ሰላም በኢስላም — 111
ምዕራፍ አሥራ ሁለት — ምስላዊ ወግ፦ ሙስሊሞች በዛሬው ዘመን ህዝብ ነክ መረጃዎች እና ባህል — 116
ምዕራፍ አሥራሦስት — ኢስላም እና ዘመናዊው ዓለም — 125

ሚስታወሻዎች — 138
የቃላት መፍቻ — 142
ዋቢ መጻህፍት — 146
የፎቶግራፍ ባለቤቶች — 150

አንዳንድ ነጥቦች “ከኢስላም ጋር ተዋወቁ” ስለተሰኙት ቅጾች

ይህ የተከታታይ መጻሕፍት ቅጽ የኢስላምን አስተምህሮ ሙስሊሞች በተረዱቸው መልኩ ከማብራራት በተጓዳኝ የአንባቢያንን ስሜት በማንቃትና በማስደመም ዓላማ የዘርፈ ብዙ ሙያ ባለቤቶች የትብብር ጥረት ውጤት ነው። የመጻሕፍቱ ትኩረት በዓለም ዙርያ ለሚገኙ አንባብያን የዘመኑን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ አቀራረብ ኢስላምን እና ሙስሊሞችን የተመለከተ ትክክለኛ መረጃን ማቅረብ ነው። በቅጾቹ ውስጥ የሚገኙት መጻሕፍት በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ የተነደፉት የሙስሊሞችን የእምነት ስርዓት እና አመለካከት ከራሳቸው ዕይታ አኳያ ለማብራራት ሲሾን፣ በጽሑፍ ደረጃ የተሰናዱትም ስለ ኢስላም በጣም አነስተኛ አልያም ምንም እውቀት የሌላቸውን የሌላ ባህሎች እና ሃይማኖቶች ተከታይ የሆኑ አንባቢያንን ለማሳወቅ እና እዝነ ህሊናቸውን ለማነቃቃት ነው። ምንም እንኳ ቅፁ በጥልቅ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ ቢሆንም፣ መረጃዎቹን ለመረዳት በማያዳግትና ቀለል ባለ አቀራረብ ለማስተላለፍ ትልቅ ቦታ ሰጥቷል።

እስካሁን በዚህ ቅጽ አንድ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል። ከእነዚህ የመጀመርያው ኢስላም እና ሙስሊሞች፥ የእምነት ጥልፍ በሚል ርዕስ የተሰናዳውና የፎቶግራፍ መግለጫ ስነ ጠበታዊ እሴትን ከጥልቅ ቁም ነገሮች ጋር በማሰናሰል ኢስላምን ውብ በሆነ አቀራረብ የሚያስተዋውቅ ነው። ከመጀመርያው መጽሐፍ በመለጠቅ ሁለት ተጨማሪ መጻሕፍት ይከተላሉ፤ አንደኛው ሙስሊሞችንና እምነታቸውን በተመለከተ በዘመናችን እጅግ በስፋት በተዛቡ ግንዛቤዎችና ጭፍን እሳቤዎች ላይ ዓይን ከፋች ዳሰሳ የሚያደርግ በቃሉ የእንግሊዝኛው ርዕስ Spread by the Word: Common Questions about Islam and Muslims የሚል ሲሾን፣ “ኢስላም በሰይፍ ነው የተስፋፋው” የሚለውን የተሳሳተ አነጋገር መነሻ ያደረገ ይመስላል። የተስፋፋ፥ ስለ ኢስላም እና ሙስሊሞች የሚነሱ ተለምዷዊ ጥያቄዎች የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ ሲሾን፣ ሌላው የኢስላም ነቢይን (ሶ.ዐ.ወ) የሚመለከት ነው።

መቅድም

ፕሮፌሽናል የብዝኃነት አሠልጣኝ ሆኜ ያለፉትን በርካታ ዓመታት አሳልፌአለሁ። ስራዬ በባህላዊ ብቃት ዙርያ አውደ ጥናቶችን ማዘጋጀትና ሊከሰቱ ከሚችሉ ወይም በተጨባጭ ከተከሰቱ የባህል ግጭቶች ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የተለዩ ጉዳዮች ዙርያ ድርጅቶችን መርዳት ነው። ጉዳዩን ለማስረዳት ምሳሌዎችን ሳቀርብ ፕሮፌሽናል ርቀትን ለመጠበቅ ስል ሆን ብዬ ሃይማኖቴን (በምሳሌነት) ከመጠቀም እቆጠባለሁ። ያም ሆኖ፣ ይህ ከዚህ ተብሎ በማይለይ መልኩ፣ በግልም ሆነ በመንግሥታዊ ዘርፎች፣ በርካታም ሆኑ ጥቂት ሰዎች በተገኙበት መድረክ የማቀርበውን ገለጻ ተከትሎ ሁልጊዜም ከታዳሚዎች ኢስላምን በተመለከተ ጥያቄዎች ይቸገደጎዳሉ። በበኩሌ ለእንዲህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች ምላሽ ስሰጥ የምሰብክ እንዳይመስልብኝ ስለምሰጋ እንደምንም ውይይቱን አቅጣጫ ለማስያዝ እጥራለሁ። ነገር ግን ከታዳሚው መካከል ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ገለጻዬን ካበቃሁ በኋላም ገለጻ ከምሰጥበት ሥፍራ መጥተው እኒያኑ ጥያቄዎቻቸውን በማቅረብ ዙርያዬን ከብበው ምላሼን እያደመጡ ረዥም ደቂቃዎች ከኔ ጋር ያሳልፋሉ።

በቀጣዮቹ ጥቂት ገፆች ለዓመታት አሜሪካ ውስጥ ስኖር እና እንደ አሜሪካዊ በሙስሊሙ ዓለም ስዘዋወር በሰዎች ሲነሱ ለሰማኋቸው እና እኔም ራሴ ላነሳኋቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ነው የምሞክረው። መጻፍ ስጀምር፣ "ገበያው" ስለ ሙስሊሞች ሌላ መጽሐፍ ሊያስተናግድ ስለመቻሉ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አልነበርኩም። ነገር ግን፣ በዐብይ ርዕሰ ዜናዎች እና በዕለታዊ መስተጋብሮች መካከል፣ (በኢስላም ዙርያ) ዛሬም ሠፊ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩን ደግሜ ደጋግሜ እንዳስብ (እንዳስታውስ) የሚያደርግ ሁኔታዎች አጋጥመውኛል። ክፍተቱ በአንዳንድ አካባቢዎች ጠበብ ያለ፣ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ በሚያሳዝን መልኩ እየሠፋ መሄዱን የቀጠለ ነው። በተጨማሪም፣ በኢስላም ላይ ያተኮሩ እጅግ በርካታ ጽሑፎች ቢኖሩም፣ በእምነቱ ዙርያ ቀላል የማይባሉ የተዛቡ ዕይታዎች አጋጥመውኛል፤ እኒህን የተዛቡ ግንዛቤዎች/ዕይታዎች ሰዎች ለዓመል ያህል እንኳ ሐቁን ለማረጋገጥም ሆነ በዘፈቀደ ከመናገር ለመቆጠብ ቅንጣት ታህል ጥረት ማድረግ ሳያስፈልጋቸው እንደው እንደዋዛ ሲያንዐባርቋቸው ይሰማሉ። የግንዛቤ ዕጦቱ፣ ኢስላም ዓለምን መቆጣጠርን ማዕከል ያደረገ የፋሺስት ርዕዮተ ዓለም ነው ከሚል ተራ አስተሳሰብ አንስቶ ኢስላማዊ ትምህርቶች ሴቶችን ስለማሰቃየት ይሰብካሉ እስከማለት ይሄዳል። እኒህን መሰል አስተሳሰቦች ሲንፀባረቁ መስማት በጣም የተለመደ ነው። ከዚህ ቀደም የተጻፉ መጻሕፍት የአንዳንድ ጠያቂዎችን ፍላጎት ቢያሟሉም፣ የሌሎችን ግን

አላሚሉም። እዚህ (በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ) ለማድረግ የተሞከረው ሙስሊሞች ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር የሚወያዩትን ኢስላም ለማቅረብ ነው። የዚህን ሃይማኖት ተከታዮች ባህሪይ የሚገዙትን ቅልብጭ ያሉ ሐቆች እና ግንዛቤዎች ለማሳየት። ሰዎችን ለመገፋፋት የታለመ ሥራ አይደለም፤ የመልመጥመጥ ዝንባሌ ያለው ሥራም አይደለም። ደራሲዋ በተወሰነ አዎንታዊ ርቀት ስለምታየው አንድ ርዕሰ ጉዳይ የተጻፈ፣ ከራሷ ማንነት የተነጠለ ምሁራዊ መጣጥፍም አይደለም። ቀድሞ ነገር፣ እያወራሁ ያለሁት ስለ ሃይማኖቴ ነው።

በዚህ መጽሐፍ፣ "ምዕራቡ ዓለም"፣ "ኢስላማዊው ዓለም"፣ ወይም "ሙስሊሞች" የሚሉትን ቃላት፣ ሊብራራ የሚችል አንድ ወጥ ትርጉም ያላቸው በሚመስል መልኩ በመጠቀም ሆን ብዬ የቋንቋ ወጥመድ ውስጥ ወድቄአለሁ። ለወትሮው ሌሎች ሰዎች ከመጠቀም እንዲቆጠቡ አሳስብ የነበረውን "አጠቃላይ አነጋገር" ለመጠቀምም ተገድጃለሁ፤ ነገር ግን እዚህ "አጠቃላይ አነጋገር"ን ማስቀረት አይቻልም። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን፣ በአንድ ሥፍራ ቢኖሩ እንኳ ወይም ለአንድ ዓይነት አጠቃላይ የእምነት መሠረቶች ያደሩ ቢሆኑ እንኳ፣ አላንዳች ስህተት ሁሉንም በአንድ ጥቅል ቃል መግለፅ እንደማይቻል፣ የዚያኑ ያህልም ይህችን በምታህል መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዳቸውን ነጣጥሎ መግለፅም እንደማይቻል አንባቢ እንደሚገነዘብ ተስፋ ይደረጋል።

ላለፉት አሠርት ዓመታት ሙስሊሙ ዓለም ስለ ምዕራቡ ባህልና እሴቶች ሲያይና ሲማር ቆይቷል። በዓለም ዙርያ [በመገናኛ ብዙኃን] ለዕይታ የሚበቁት የሰዎች ገፅታና ምስሎች በዘፈቀደ የሚለቀቁ አይደሉም ታስቦባቸው የተመረጡ እንጂ፤ ይበጃጃሉ፣ በተመጠነ ብርሃን ይዋባሉ፣ ለማመን በሚያዳግት መጠን በዲጂታል ጥበብ ልዩ መስህብ ይጎናፀፋሉ። በእነዚህ ትዕይንቶች አማካይነት እንዲንፀባረቅ የሚፈለገው ውብ እና ሰላም የሰፈነበት ዓለም ሲኾን፣ ይህን ጥያቄ ውስጥ የሚከት ቢኖር ከእብድ ሊቅጠር ይችላል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥም የሙስሊሞችን ገፅታ ይወክሉ ዘንድ በራሳቸው በሙስሊሞች የተመረጡ ምስሎችን ታገኛላችሁ። እነዚህ ምስሎች ገና እንዳየናቸው የእኛ ብለን የምንለያቸው ፊቶችና ገጽታዎች እንጂ፣ ላለፉት በርካታ ዓመታት የግዳችንን ስንጋታቸው የኖርናቸው ሆን ተብሎ የተቀመሩ የተጋነኑ የነውጠኛ ገጽታዎች አይደሉም። ፎቶግራፎቹ ከዚህ ግንዛቤ ጋር ፍፁም የተጣጣመ ህብር ይፈጥሩ ዘንድ ታስቦባቸው የተመረጡ ናቸው።

መጽሐፉ ሙስሊሞች ሌሎች እንደሚስሏቸው ሳይሆን እንደሆኑት፣ እነርሱ ራሳቸውን እንደሚያዩት ለሌሎች ፍንትው ብለው እንዲታዩ የሚያስችላቸው ምስላዊ መስኮት ለመክፈት ይጥራል ውስብስብ እና መልከ ብዙ፣ ሁሌ ቁጡ ያልሆኑ፣ ዘወትር በብሶት ዓለም ውስጥ የማይኖሩ፣ በእርግጠኝነትም አስተኔ (ONE-DIMENSIONAL) ያልሆኑ ህዝቦች። ምስላዊ መስኮቱ፣ በአንዳንድ የመጽሐፉ ክፍሎች ትረካውን በሚደግፍ መልኩ፣ በሌሎች ክፍሎች ደግሞ የቃላትን እገዛ ሳይሻና መቼም ቢሆን ቃላት ሊገልፁ ከሚችሉት በላይ በሆነ መልኩ የዛሬውን ዘመን የሙስሊም ህይወት ሰውኛ መልክ ወለል አድርጎ ያቀርባል። የፎቶግራፎቹ መረጣና አቅርቦት፣ ከጠቢብ ዕይታቸው ባሻገር ከፍተኛ ጥራት ባለው ካሜራቸው ሌንስ አማካይነት ውበት፣ ድባብ እና ጥልቀት ያላቸውን ፎቶግራፎች በከፍተኛ የእኔነት ስሜት ባሰባሰቡ ሙስሊሞች እና ሙስሊም ያልሆኑ የአዲሱ ትውልድ ምርጥ የፎቶግራፍ ባለሙያዎች ነው የተካሄደው። በዛሬው ዘመን እጅግ አዘውትረን የምናየው የኢስላም ገፅታ የተከበበ ወይም መፈናፈኛ ያጣ ማኅበረሰብ ገፅታ ነው። ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ጥሪቶቹን በያሉበት ትቶ፣ በዕውን ካለ አልያም ምናባዊ ወራሪ ጦር ጋር ያልተቀናጀ (ዝግጅት ያልተደረገበት) ፍልሚያ ለመግጠም ከተሰማራ አንድ አንጃ ጋር ይመሳሰላል። ደግሉ እኒያን በያሉበት የተተው ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ጥሪቶች የመጠበቁን ኃላፊነት

በመውሰድ፣ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የህልውና መሠረቶች የሆኑትን ዐበይት እምነቶች፣ እሴቶች እና ክንዋኔዎችን ጠብቀው ያኖሩ አስተዋፅና አርቆ አሳቢ ሰብዕናዎች አሉ። መለኮታዊው መጽሐፍ እነርሱ ዘንድ በጥንቃቄ ተጠብቆ አለ። እነዚህ ሰዎች ዛሬም አሉ፣ በአካል አግኝቻቸዋለሁ፣ ተስፋቸውም ብሩኅ ነው።

ሙስሊሞች ከሚበዙባቸው አገራት የምንኖርና ለሌሎች ባህሎች ተጋልጠን ያደግን፣ ሃይማኖታችንን ለማስተዋወቅ በተለየ ሁኔታ ውስጥ የምንገኝ የሙስሊም ትውልድ አለን። እኛ እምነቱን ከደባል ባህላዊ ድረታዎች ልናጠራው የምንችልበት ዕድል አለን። ምንም እንኳ ደባል ባህላዊ ተቀጽላዎች አልፎ አልፎ አካባቢያዊ የሃይማኖት ክንዋኔን ቢያጎለብቱም፣ እጅግ በአመዛኙ ግን ሃይማኖቱን በአንድ ወቅት እና ቦታ በተንፀባረቁ ሐሳቦች ታጥሮ ባለበት እንዲረግጥ ነው የሚያደርጉት። በካሊፎርኒያ እንደማደጌ፣ የእኔ የምለው ባህል በመሠረቱ የታላላቅ ወንድሞችና እህቶቼ፣ ዘመድ አዝማዶቼ እና ጓደኞቼ ባህል ነው። እነርሱ ትክክል ነው ያሉት በቃ ትክክል ነው። ሃይማኖት ማለት የሆነ ወላጆቻችን ይከውኑት የነበረ፣ ነገር ግን በህይወታችን ውስጥ ብዙም ሚና ያልነበረው ነገር ነበር። ሃይማኖታችንን ለመማር ስንወስን፣ ይህንን የምናደርገው በራሳችን አስበንበት፣ ይሁንኝ ብለን ነበር። እኛ ተወልደን ባደግንበት ምድር ሃይማኖትን ለመማር የሚያስገድድ ይቅርና የሚያበረታታ አንዳችም ነገር የለም። ሃይማኖታችንን ለመማር ወስነን የተነሳነው ሰዎች የትክክለኛነት ተግዳሮት ገጥሞን ነበር። የማንኛው ‹‹ኢስላም›› ነው ትክክለኛ? ሂደን እምናናግረው እንደ ጳጳስ ያለ አካል በሌለበት ሁኔታ፣ የትኛው ነው ትክክል የሚለውን ለመወሰን ቀውስ ውስጥ ገብተን ነበር።

ይህ ቀውስ የኢስላም ማዕከል ወደሆኑት አገራት መራኝ፤ እዚህ ላይ ‹‹የኢስላም አገራት›› የሚለውን ሐረግ እንደዋዛ ነው የተጠቀምሁት፤ ምክንያቱም ኢስላማዊ ከሚባሉትም አገራት ይበልጥ በተሟላ መልኩ ኢስላማዊ በማይባሉት አገራት ውስጥ ልተገብር የምችላቸው አንዳንድ የሃይማኖቴ ገጽታዎች አሉ። ጥንታዊ እና ዘመነኛ ድርሳናትን ለማጥናት ምዕራባዊውን ትምህርቴን ልጠቀምበት ችያለሁ። [የ‹ሙስሊሙ›ን ዓለም] ወግ ልማድ በቅጡ ባለማወቄ ከመጎዳት ይልቅ የተጠቀምሁበት አጋጣሚም አለ። ለምሳሌ፣ አብዛኞቹ የህገሬው ተወላጆች መልስ እንዲሰጥበት በመሻት ጠይቀው የማያውቁትን፣ አልያም መጠየቁም ተገቢ አይደለም ብለው በማሰብ ያልጠየቋቸውን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ረድቶኛል። ምንም እንኳ ያልጣስሁት ባህላዊ ወግና ልማድ አለ ማለት ባይቻልም፣ በዚሁ ሂደት ስለ ሃይማኖቴ ያገኘሁት ግንዛቤ ምዕራባዊ አስተዳደጌ ባይታከልበት /አይጠየቁ የሚመስሉ ርዕሰ ጉዳዮችን ሁሉ ባልጠይቅ/ ኖሮ ላገኝ እማልችለው ነበር ብዬ አስባለሁ። ይህ መጽሐፍ በዚህ ሂደት የተማርሁትን ለማስተላለፍ ያደረግሁት ሙከራ ውጤት ነው።

ሰማህ ማሬ



መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሙስሊሞችን ከማሞካሸት ወይም ከመካብ በመቆጠብ የኢስላምን የጠራ እና የላቀ ደረጃ ለማቅረብ ይሞክራል። በኢስላም ምንነት አንጻር ሙስሊሞች አንድ ወጥ በሆነ ደረጃ እና መልክ አይገለፁም። አንዳንዶቹ ሙስሊሞች ውጫዊ ተግባራትን እጅግ ከዘቀጠ ፀያፍ ውስጣዊ ሰብዕና ጋር አዋህደው ይዘዋል። አለመታደል ሆኖ በስፋት የምናውቃቸው እነዚህን ዓይነቶቹን አንድ ተጨማሪ ሰው በገደሉ ቁጥር የፈጣሪን ታላቅነት የሚያወሱትን ["ሙስሊሞች"] ነው።

አንዳንዶቹ የነቢዩ ሙሐመድ ስብከትን መንፈስ ተላብሰው ቢታዩም፣ ነቢዩ ላስተማሩት ቃል በተግባር ተገዢ ላይሆኑ ይችላሉ። ሌሎች ደግሞ አሉ [የነቢዩን ትምህርት] መንፈሱንም ሆነ ቃሉን ያልጨበጡ፣ ነገር ግን ከአላህ በስተቀር ሊግገዙት የሚገባው አምላክ የለም፣ ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ ናቸው የሚለውን ይፋ የእምነት ማረጋገጫ ቃል እጅግ አጥብቀው የያዙ። ግና ደግሞ የሃይማኖቱን ውስጣዊ እና ውጫዊ አስተምህሮ አጣጥመው የሚኖሩ መኖራቸውም እርግጥ ነው። ምንም እንኳ የእውብ ሰብዕናቸውን ውበት ጋርደው ለመኖር የመረጡ ቢሆኑም፣ አዎ እንዲህ አይነቶቹ ሙስሊሞችም አሉ።

ይህ መጽሐፍ ስለ እያንዳንዱ ግለሰብ ሙስሊም ለማውሳት አይሞክርም፤ ይህንን ማድረግም የሚቻል አይደለም። ለዚህም ነው ይህ መጽሐፍ የሙስሊሞችን ዐብይ ወይም ማዕከላዊ እምነቶች በሚያስተዋውቀው የኢስላም አስኳል የሚጀምረው። ወደ አስተምህሯዊ ዝርዝሮች ከመዋለቅ በመታቀብ፣ መሠረታውያኑ መርኖች እጥር ምጥን ባለና ሙስሊሞችን ከሌሎች በሚለይዋቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ቀርበዋል። ሙስሊሙ የያዛቸው እምነቶች በሙሉ በተለይ በኢስላም ውስጥ ብቻ የሚገኙ አይደሉም።

ምንም እንኳ የጋራ የሆኑ የእምነት አዕማዶችን አንድ ሁለት ብሎ መጥቀሱ ለበይነ ሃይማኖት (በሃይማኖቶች መካከል ለሚደረግ) ውይይትና አላስፈላጊ ጥርጣሬን ለማስወገድ የሚረዳ ቢሆንም፣ ማንነትን ለማብራራት ግን እምብዛም ፋይዳ የለውም። የኢስላም ውጫዊ ገጽታ የሚል ርዕስ የተሰጠው ክፍል እነዚህን መሠረታዊ እምነቶች በታሪካዊ አውድ ያስቀምጣቸዋል። እዚህ ላይም በመጥፋት አፋፍ የሚንገዳገዱ ይመስሉ ከነበሩ ጥቂት የምዕመናን ጓድ ተነስቶ በዓለም ታሪክ ከተከሰቱ ግዙፍ አዒዎች ሁሉ በስፋቱ የላቀ ስለሆነው የሙስሊሙ ዓለም ሰፊ ታሪክ ይቀርባል። በዚሁ ክፍል የኢስላማዊው ታሪክ አበይት ወቅቶች (ክስተቶች) ከውስጥ ወደ ውጭ በሚያይ ዕይታ ይጠቃቀሳሉ። ምዕራቡ ዓለም እዚህ

ላይ የሚጫወተው ሚና አናሳ ነው፤ እንደመሆኑም ዐብይ መስተጋብር የተከሰተባቸው አጋጣሚዎች ብቻ ዘርዘር ባለ መልኩ ተዳስሰዋል።

በመጨረሻ፣ አንዐባራቂው ኢስላማዊ ግዛተ አሜ እና ስኬቶቹ ወደ አይቀሬው [ውድቀት] ካመሩ በኋላ ምን ተፈጠረ? በዚህ ረገድ ዛሬም ድረስ እየተነሱ ያሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች የላቂያ ደረጃዎች እና እውነታዎች በሚል ርዕስ በክፍል ሦስት በሰፊው እናያለን። እኒህ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፣ ዳግመኛ ላይነሱ፣ ግብዓተ መሬታቸው ሊፈፀም አፋፍ ላይ ደርሰዋል ተብሎ ከታሰበ በኋላ፣ ሌላ አዲስ ጉዳይ ዐብይ ርዕሰ ዜና ሆኖ ከተፍ ይልና ቀደም ሲል በተሰጡት ምላሾችና ማብራሪያዎች ላይ ሌላ ጥያቄ ይነሳል። ብዙ ሰዎች ሙስሊሞች ስለሃይማኖታቸው በቅንነትና በገለልተኝነት መናገር አይችሉም፣ ጥያቄ ሲቀርብላቸው የተከላካይነት ዝንባሌ ያጠቃቸዋል፣ መከላከል የማይቻለውን ጉዳይ ሁሉ ይከላከላሉ በማለት ስሞታ ያቀርባሉ። ነገር ግን በመላው ዓለም በሚገኙ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሰባኪያን ማሰልጠኛ ኮሌጆችና በማዕድ ጠረጴዛ ዙርያ የሚካሄዱ የተሟሟቁ ውይይቶችና ክርክሮችን ታድሞ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ይህ ስሞታ ምን ያህል ከሐቁ የራቀ እንደሆነ ይገነዘባል።

በኢስላሙ ዓለም ውስጥ በሚፈፀሙ መጥፎ ነገሮች ራሳቸው ሙስሊሞች ከሚያዝኑት የበለጠ የሚያዝን ማንም የለም። ነገር ግን የሙስሊሙን ዓለም መጥፎ ገጽታ የሚያሳዩት ምስሎች ምን ያህል ከአጠቃላዩ እውነታ እጅግ የራቁ እንደሆኑ እናውቃለን፤ ያ ብቻ ግን አይደለም፣ ስለአንዳንድ በቴሌቪዥን ያልታዩ እውነታዎች ለሰዎች በታላት ማስረዳት በእርግጥም ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነም እናውቃለን። ሃይማኖታችንን እና ሃይማኖታችን ለሰው ልጆች ዕድገት ስላበረከተው ታላቅ አስተዋጽኦ እናውቃለን፣ ግና ጩኸታችን ሁሉ ሃይማኖታችንን በማጠልሸት ዓላማ በሚዥጎደጎዱት መጥፎ ምስሎች ተውጧል "እኒህ ምስሎች የሃይማኖታችንን እውነተኛ ገጽታ አያሳዩም!"

ሙስሊሞች አሁንም አጠቃላይ አነጋገር ተጠቀምሁ ሃይማኖታቸው (ኢስላም) ምንም መቀባባት፣ ከግል ዝንባሌ የመነጨ ማስዋቢያ ይሻል ብለው አያምኑም። ከዚያ ይልቅ ኢስላም የሚሻው በታሪክ ረገድ በተለጠፈበት የተዛነፈ የአሉታዊ አስተሳሰብ ጥላሸት ባልተበረዘ አዕምሮ እና ከዘመናዊ የማዛባት አባዜ በጠራ መንፈስ መቅረብ ብቻ ነው የሚፈልገው። በዓለም ዙርያ ያሉ ሙስሊሞች ታሪካዊ ዳራ እና ተሞክሮ የሚፈጥረው ብዝኃ ህብረ ቀለም እጅግ በጣም ሰፊ ቢሆንም፣ በየትኛውም ዓይነት ዳራ ወይም ተሞክሮ ያላቸው ማናቸውም ሙስሊሞች ይህን መጽሐፍ አግኝተው ሲያነብቡ "አዎ፣ ይህ ነው የኔ ሃይማኖት፤ እነሆ የእኛ ሃይማኖት ይህንን ይመስላል" በማለት አስረግጠው እንደሚናገሩ በእጅጉ ተስፋ አደርጋለሁ።

ክፍል አንድ

የኢስካም አስኳል


الله
الوكيل
القوي
المتين
الرحيم
الرحمن
الباسط
القابض
الخافض
الباعث
المجيد
المنتقم
التوا
العليم
ذل
افع

ምዕራፍ አንድ

አላህ

አንዲት ብቁ የሆነች ሙስሊም የኮሌጅ መምህርት በአንድ ወቅት ሴቶች በኢስላም ያላቸውን ደረጃ በተመለከተ እጅግ ውብ ትምህርታዊ ዲስኩር (ሌክቸር) ካደረገች በኋላ ከአድማጮቿ ጥያቄዎች መቀበል ጀመረች። ለቀረቡላት ጥያቄዎች በምትሰጣቸው መልሶች ታዳሚዎቿን በሳቅ ስታፈርሳቸው፣ በግርምት ስታስቆዝማቸውና አልፎም ሳያውቁት በጉንጮቻቸው ላይ የሚወርዱ እንባዎቻቸውን ስታሳብሳቸው ነበር። ነገር ግን በመጨረሻ ለተጠየቀችው <<ፀጉርሽን በስካርፍ የምትሸፍኚው ለምንድን ነው?>> የሚል ጥያቄ የሰጠችው ምላሽ ከቀደሙት ምላሾቿ የበለጠ ሌክቸሩ ካበቃ በኋላ እዚያ የነበሩ ታዳሚዎቿ ለረዥም ጊዜ በአዕምሯቸው ይዘው ያስቀሩት ነበር።

መልሷ በጣም ግልፅ፣ ግን 'አሳዛኝ' ነበር፡ "ምክንያቱም ፈጣሪ ይህን እንዳደርግ ይፈልጋል ብዬ ስለማምን።"

ይህንን አንዳችም የማቅማማት ዝንባሌ በማይታይበት መልኩ የቀረበ <ከጊዜው ጋር የማይሄድ> ምላሽ በታዳሚው ዕይታ አሳዛኝ (አስደንጋጭ) ያደረገው ምላሹን የሰጠችው ሴት ማንነት ነው። ይህ ምላሽ የተሰጠው የምትናገረውን እያንዳንዷን ቃላትና ሐሳብ በጥንቃቄና በጥልቀት በመመዘን በምትታወቅ ከፍተኛ የአዕምሮ ብስለት ባላት ሴት ነው። ይህች ሴት በዚያን ወቅት በህክምና ኮሌጅ ከክፍሏ ተማሪዎች ሁሉ ብልጫ ያላት ነበረች፤ በአሁኑ ሰአት በሙያ መስኳ ካሉ ስመ ጥር ሀኪሞች መካከል አንዷ ነች። በሌላ አነጋገር፣ ይህች ሴት ተራ ሰው አልነበረችም። ራሷን ልትገልፅበት የሚያስችል ከበቂ በላይ የሆነ ምሁራዊ አቅም ያላት ሁና ሳለ፣ ህይወቷን የምትመራበት ዐብይ መርሳ፣ በመለኮታዊው ፈጣሪዋ ህልውና ላይ ያላት የማይናወጥ እምነት እና ከእርሱ ጋር ያላት ጥብቅ ትስስር ነበር።

አብዛኛዎቹ የኢስላም ህግጋትና የአምልኮ ሥርዓቶች ለአዕምሮ ቅቡል ከመሆናቸውም በላይ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሊብራሩ የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ የአልኮሆል መጠጥ፣ የቁማር እና መሰል ማኅበራዊ ጠንቆች ክልከላን መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን ከእያንዳንዱ አምልኮ በጎገራችን ላይ በኢስላም <አምልኮ> የሚለው ቃል በዛሬው ዘመን አረዳድ ሰዎች ከሚሰጡት ትርጉም እጅግ የሰፋ ፈርጀ ነው ያለው በስተጀርባ ያለው መግፍዔ /አነሳሽ ምክንያት/ አንድ ነው አላህ። የአምላክ ህልውና መካድ የውስብስብ ወይም የሳይንሳዊ ውይይት ቅድመ መስፈርት እየሆነ በመጣበት በዛሬው ዘመን፣ ሙስሊሞች



■ ሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ በመካ አቅጣጫ ስግደታቸውን ይፈጽማሉ። ካዕባ አንድና ብቸኛ የሆነውን አምላክ የማምለክ ተምሳሌት ይሆን ዘንድ በነቢዩ አብረሃምና በልጃቸው እስማኤል እንደታነፀ ሙስሊሞች ያምናሉ።

የፈጠራቸውን ጌታ መኖር ብቻም ሳይሆን ማንኛውም ተግባራታቸው ሁሉ ማዕከል የሚያደርጉት እርሱን መሆኑን አስረግጠው መናገራቸውን ቀጥለዋል። አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፦ (በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለርሱ ያሞግሳል። እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።) (59:24)

ተውሂድ፦ የአላህ አንድነት

በኢስላም እጅግ መሠረታዊው የእምነት አምድ፣ የአላህ አንድነት ተውሂድ በአንድ በኩል በጣም ቅልብጭ ያለ የዚያኑ ያህል ደግሞ እጅግ ጥልቅ ትርጉም ያዘለ ነው። በተውሂድ (በአላህ አንድነት) ማመን ሙስሊም የመሆን ዓይነተኛ መገለጫ ነው ማለት የሚቻል ሲኾን፣ ነገር ግን አምላክ አንድ ለመሆኑ እውቅና በመስጠት ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከዚያ ባሻገር የጠለቀ ትርጉም ያለው ነው። ምንም እንኳ በሃይማኖቱ ውስጥ የሚፈፀሙ የተለዩ ክንዋኔዎችን በተመለከተ ጥያቄዎችና የተራዘሙ ውይይቶች ቢኖሩም፣ ተውሂድ በቁርአን ውስጥ ካሉ በጣም አጫጭር ምዕራፎች በአንዱ እጥር ምጥን ባለ መልኩ ቀርቦ ይገኛል፦ (በል፦ እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደም፤ አልተወለደምም። ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።) (112:1–4)

ተውሂድ በአማኞች (በሙስሊሙ) ማኅበረሰብ ውስጥ የማንነት ዓይነተኛው መገለጫ ነው። የበለጠ በዓይን የሚታዩት ሌሎቹ የኢስላም ምልክቶች በሙሉ ግፋ ቢል የእርሱ ቅጣዮች ናቸው። አንድ በተውሂድ (በአላህ አንድነት) የመሰከረ ሰው በኃጢአት ላይ ወድቆም እንኳ አሁንም ሙስሊም ነው። በአንጻሩ ቀኑን በፆም እና ሌሊቱን በስግደት የሚያሳልፍ፣ ነገር ግን ከአንድ በላይ ፈጣሪዎች አሉ ብሎ የሚያምን (ወይም ፈጣሪ ላይኖር ይችላል) ብሎ የሚያምን እርሱ ሙስሊም አይደለም። ብዙዉን ጊዜ ሙስሊሞች በሰብአዊ ፍጠራን ላይ ከባድ ወንጀል የሚፈፅሙ ሌሎች ሙስሊሞችን ሙስሊምነት እንዳይቀበሉ ወይም ሙስሊም አይደሉም ብለው በይፋ እንዲናገሩ ይጠየቃሉ። እንዲህ ብለው የሚጠይቁ ሰዎችን በጣም ሊያስከፋ ቢችልም ቅሉ፣ ሰውየው የቱንም ያህል መጥፎ ቢሆን እንኳ፣ በፈጣሪ አንድነት ማመኑን የመሰከረን ሰው ከኢስላም ማግለል፣ አይቻልም ለማለት በሚጠጋ ደረጃ እጅግ በጣም ከባድ ነው። በሰማይ ቤት የሚጠብቀው ወይም የሚጠብቃት ፍርድ ምን ይሆናል? ሌላ ጥያቄ ነው።

አምላክ ወይስ አላህ?

እንደ ኢስላማዊው እምነት፣ የአምላክ ፍፁም አሃዳዊነት (አንድነት) መልዕክት በአጠቃላይ የሁሉም ሃይማኖቶች እና በእርግጥም የኢስላም ዐብይ መልዕክት ነው። ከአምላክ ወደ ሰው ልጆች የተላለፈ የመጨረሻው ዘመን ኪዳን እንደመሆኑ ኢስላም የቀደምት ነቢያትን ህልውና ክዶም ሆነ ከብራቸውን በጭራሽ ተጻርሮ አያውቅም። ይልቁንም፣ ሙስሊሞች የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን አምላክ፣ የዓለማት መለኮታዊ ፈጣሪ፣ ከአላህ የተለየ ህልው ነው የሚል ዕይታ ኖሯቸው አያውቅም። በእውነተኛ የአሃዳዊ እምነት ዕይታ "የእኛ አምላክ" እና "የእነርሱ አምላክ" በሚል የሚደረግ ውይይት ትርጉም አልባ ነው። አላህ የአንድ ከባለጋራ ቡድን ጋር ለመጋጠም የተሰለፈ ቡድን አምበል አይደለም፤ አላህ ስንል የእስራኤል ልጆችን ከፈርኦን የጭቆና ቀንበር ነፃ ስላደረገው አምላክ ነው የምናወራው፤ አላህ ስንል ለዳዊት (ዐ.ሰ.) መዝሙራትን ስለላከለት አምላክ ነው የምናወራው። አላህ ስንል ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 7፣ ቁ. 16 "የእኔ ትምህርት ከላከኝ ከአብ የተገኘ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም።" የጥቅሱ ትርጉም በ1980 ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው። በማለት ስላወሳው አምላክ ነው የምንናገረው።

በስያሜዎቹ ልዩነት ዙርያ የሚሸከረከሩ ጥያቄዎች ይነሳሉ፣ አላህ ማለት በትክክል ከአምላክ ጋር ተመሳሳይ ነውን? እዚህም ላይ፣ እንደ አሃዳዊ እምነት ተከታይ የመለኮት ስም ይሰጠው ዘንድ የተገባው አንድ ብቻ አምላክ እስከሆነ ድረስ ይሄ ነጥብ ለክርክር ሲባል ብቻ የሚነሳ ርዕስ ነው። ነገር ግን ከቋንቋም አኳያ የቃሉን ስርወ አመጣጥ እንመርምር ብንል ቃሉ ወይም ስሙ በአሃዳውያን እምነቶች ውስጥ ተመሳሳይ እና ማንም ተራ ተርጓሚ ሊገልፅ ከሚችለው እጅግ በተሻለ በማፈራረቅም ጭምር ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል። አላህ የሚለው ሴማዊ ቃል "አል" እና "ኢላህ" የሚሉ ሁለት ስርወ ቃላት ድምር ነው። "አል" ማለት እንደእንግሊዝኛው the አንድን የተወሰነ አካል የሚገልጽ ሲኾን፣ "ኢላህ" በእውነት የሚገዙት ማለት ነው።

ኢስላም = [ለፈጣሪ አምላክ] እጅ መስጠት
ሙስሊም = የአምላክን አንድነት እና የነቢይ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) መልዕክተኝነት የሚመሰክር

በሥርወ ቃልም ሆነ በትርጉም ከዕብራይስጡ “ኤሎሂም” እና ከአራማይኩ (ጽርዕ) “አላሃ” ጋር አንድ ነው። በዛሬው ዘመን ጥቅም ላይ የሚውለው “God” የሚል የእንግሊዝኛ ቃል የንጉስ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ (King James Bible) ከመዘጋጀቱ ብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ በጥቅም ላይ ነበረ። ስርወ ቃሉ በድምጽ ተቀራራቢው የህንድ አውሮጳዊው “ጉቶ” (Ghuto) የተሰኘ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም “በፀሎት ላይ የሚጠራው”[1] ማለት ነው።

ሁሉ አቀፍ መልዕክት

የሚድኑ ፍጡራንን ቁጥር ከሚገድቡ የሃይማኖት ቡድኖች ወይም አምልኮቶች፣ እንዲሁም አንድን የተወሰነ ሰነድ በይፋ አጽድቀው ከሚንቀሳቀሱ የእምነት ፈለጎች በተቃራኒ፣ ሙስሊሞች በሌሎች ባህሎች ውስጥም አሃዳውያን ሊኖሩ ስለመቻላቸው እውነታ እውቅና ለመስጠት አይቸገሩም። በጥንታዊ ነገዶች እምነቶች (ሃይማኖቶች) ላይ ጠለቅ ያሉ ጥናቶች በተሰሩ ቁጥር፣ ለዘመናት ሙሉ በሙሉ እምነት አልባ ወይም ተፈጥሮ አምላኪ ተደርገው ሲታሰቡ የኖሩ እጅግ አናሳ ሃይማኖቶች እንኳ በሥርዓተ አምልኳቸው ለሚያወሱት ልዕለ ኃያል አካል የሚያወላዳ እውቅና እንደሚሰጡ ይበልጥ ግልፅ እየሆነ መምጣቱ አይቀርም።[2] ለአንድ ሙስሊም ይህ የሚያስደንቅ ነገር አይደለም።

በተጨማሪም ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ከመወለዳቸው አያሌ ዓመታት በፊት አላህን የሚገዝዙ ህዝቦች እንደነበሩ ለማወቅ ያን ያህል አዳጋች አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ይህ ሐቅ ሰፋ ባለ ዕይታ ማንኛውም ሰው ሙስሊም (ለፈጣሪው ፈቃድ ያደረ) ነው የሚለውን ግንዛቤ ያጠናክራል። ሰዎች ሁሉ ባለፈ ህይወታቸው አንድ ወሳኝ ወቅት ለአምላክ ተገዢ ስለመሆናቸው አረጋግጠዋል። ሃይማኖቱን በጽናት የሚተገብር ንቁ ሙስሊም ከእነርሱ የሚለይበት ነጥብ ቢኖር ለዚያ የተገዢነት ማረጋገጫ ታማኝነቱን አጥብቆ መቀጠሉ ነው። አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፦ (ጌታህም ከአደም ልጆች ከጀርቦቻቸው ዘሮቻቸውን ባወጣና ጌታችሁ አይደለሁምን? ሲል በነፍሶቻቸው ላይ ባስመሰከራቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፤ ጌታችን ነህ፣ መሰከርን አሉ፤ በትንሣዔ ቀን ከዚህ (ኪዳን) ዘንጊዎች ነበርን እንዳትሉ።) (ቅዱስ ቁርአን 7፣172)

የአላህ ባህሪያት

ተቀባይነት ያላቸው የአሃዳዊነት መለኪያዎችን በመደንገግ ረገድ የኢስላም አስተምህሮ እጅግ በሚያስገርም የጥልቀት ደረጃ የተዘረዘረና ጥርት ያለ ነው። ሙስሊሞች ከአብዛኛው የዓለማችን የእምነት ማኅበረሰብ ጋር ቢያንስ ያ ሃይማኖት ከምንም በፊትና በላይ የዩኒቨርስ ፈጣሪ ለመኖሩ ዕውቅና የሚሰጥና ያንንም ፈጣሪ የሚያከብር ነው የሚል ስሜት ሲያድርባቸው ከዚያ ሃይማኖት ማኅበረሰብ ጋር የሚጋሩት ነገር እንዳለ ይሰማቸዋል። ነገር ግን፣ በዚህ እውነታ ላይ የሚደረብ ወይም የሚቀጠል አስተሳሰብ እነርሱ ዘንድ በጭራሽ ተቀባይነት የለውም። [7]

ኢስላም በአለመመሳሰል ተቃርኗዊ ባህሪ ዙርያ ከሌሎች ሃይማኖቶች የተለየ አቋም አለው። የኢስላም ስነ መለኮት አምላክ አንድ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ከየትኛውምና ከማንኛውም የእርሱ ፍጡር ጋር ፈጽሞ እንደማይመሳሰል አጥብቆ ያስተምራል። አላህ በቁርአን፣
<<...የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።>> ይላል። (ቅዱስ ቁርአን 42፣11)



■ የአላህ 99 ስሞች አቡ ዳቢ በሚገኘው የሸይኽ ዛይድ መስጂድ በምኩራቡ ግድግዳ ዙርያ ተቀርጸዋል።

ሚካኤል አንጀሎ ሮም በሚገኘው የሲስታይን ቤተ መቅደስ በሚስልበት ወቅት ከዚህ ሐሳብ ጋር ተሟግቷል። ምንም እንኳ ከቅደም ተከተል አኳያ የመጀመርያው ትዕይንት ቢሆንም፣ አንጀሎ አምላክን በስዕል ለመግለጽ በማመንታት ብሩሹ በደንብ እስኪገራለት የዘፍጥረትን ታሪክ (ትዕይንት) ወደኋላ አዘግይቶታል። ዘግይቶም ሆነ ፈጥኖ የሚሠራ ማንኛውም (የአምላክ) ምስላዊ መግለጫ በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት ባይኖረውም፣ ከዚህ ሁነት ታላቁ ጠቢብ እንኳ ይህንን ተግባር ለመፈፀም ምን ያህል ብቁ አለመሆኑ እንደተሰማው ማየት ይቻላል። ምናልባት በስውር አዕምሮው ውስጥ የተቀበረ የገዛ ቃል ኪዳኑ ትውስታ ይሆናል ለዚህ የዳረገው። አዕምሮው ውስጥ ሳይፈጠርበት እንዳልቀረ ለሚገመተው በአንደበት ያልተጠየቀ ጥያቄ ምላሹን ስመ ገናናው ሙስሊም ባለቅኔ መለኮታዊ ህልውን እንዲያስረዳ በተጠየቀበት ጊዜ ከሰጠው መልስ ሊያገኝ ይችል ነበር፣

የጠራ ያለውሃ። የረጋ ያለ እስትንፋስ። ብርሃን ያለ እሳት። ነፍስ ያለ ስጋ።[3]

ምንም እንኳ ከፍጥረት ፍፁም የተለየ እና የማይመሳሰል ቢሆንም፣ አላህ ሩቅ እና የማይታወቅ ግን አይደለም። በእርግጥም፣ እጅግ ጥንታዊ እና ከፍተኛ ተቀባይነት ባለው የቁርአን ትንታኔ (ተፍሲር)፣ ‹‹ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም›› (51:56) በሚለው አንቀጽ ውስጥ ‹‹ሊግገዙኝ እንጅ›› የሚለው ሐረግ ‹‹እንዲያውቁኝ›› በሚል ተተንትኗል። አላህ የሚታወቅ ብቻ ሳይሆን፣ እንዲታወቅ የሚሻም ጭምር ነው። በእርሱ የሚያምኑ እንዳይጠይቁ ሳይሆን በዙርያቸው ያሉትን ምልክቶች እንዲያስተውሉ፣ እርሱን ያውቁ ዘንድ፣ ወደ እርሱም ይቀርቡ ዘንድ አዕምሯቸውን እንዲጠቀሙ ደጋግሞ ይነግራቸዋል ወይም ይጋብዛቸዋል።

‹‹እርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለንን፤›› (41:53)

የአላህ ስሞች

በኢስላም ክህነት የሚባል ነገር የለም። ምዕመናን በየዕለቱ ያለማንም አማላጅነት በቀጥታ ወደ አላህ ይጣራሉ። ከሚታወቁት የአላህ 99 ስሞች ጠቢጥ በርካታ ተቃራኒ ጥንዶች ይገኛሉ፣ ለምሳሌ፣ የመጀመርያው እና የመጨረሻው ['አልፋ እና ኦሜጋ' እንዲሉ]፣ እንዲሁም “ህይወት የሚሰጥ” እና “ሞት የሚሰጥ።” በአንዳሩ ከ99ኙ ስሞቹ አንዱ “ቅርቡ” የሚል ቢሆንም፣ ርቀት የተገለፀበት አንድም ስም የለም። ከዚያ ይልቅ አላህ (ሱ.ወ.) “ሰዉንም ነፍሱ (በሐሳቡ) የምታጫውተውን የምናውቅ ስንኾን በእርግጥ ፈጠርነው፤ እኛም ከደም ጋኑ ጅማት ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ ነን።” ይላል። (50፣16)

እነዚህ በነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) አማካይነት የተገለፁልን 99 ስሞች ከቶውንም የአላህን /ሱ.ወ./ የፍፁምነት ባህሪ የመገደብ ዓላማ የላቸውም፤ ይልቁንም ምዕመኑ ስለመለኮታዊው እውነታ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኝ ለመርዳት የታለሙ ናቸው። እነዚህ ስሞች በምንም መልኩ ከራሱ ከአላህ የተነጠሉ አይደሉም። ዳኛም ፍትኅም እርሱ ነው፤ ተበቃይም አዛኝም እርሱ ነው። አላህ የሚለው ጠቅላይ የተፀውዖ ስሙ እነዚህን ሁሉ ትርጉሞች እና ከዚያም በላይ ያካብባል። ከባህሪያቱ ውስጥ እርሱ ራሱ ደግሞ ደጋግሞ በአጽንዖት የተናገረው “በጣም አዛኝ” (አል-ረህማን) የሚለውን ነው። ከአንዲቱ በቀር እያንዳንዱ የቁርአን ምዕራፍ “በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው” ብሎ ይጀምራል።



እጅግ የላቀ ነው የሚባለው የእናት እዝነት ከአላህ እዝነት ጋ ሲነጻጸር የደቂቅ ደቂቅ ነው

የአላህ እዝነት

የአላህ የእዝነት ባህሪ የተገለጠበት "ራህማ" የሚለው የአረብኛ ቃል "የእናት ማህፀን" ከሚለው የአረብኛ አቻ ተመሳሳይ ስርወ ቃል የተገኘ መሆኑ የአጋጣሚ አይደለም። ለሰብአዊ ፍጡራን የመለኮትን እዝነት የጭላንጭል ያህልም ቢሆን ሊያስረዳ የሚችል ነገር ቢኖር አንዲት እናት ለልጇ ምን ያህል እንደምትሳሳ በጥልቀት ማስተንተን ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ጊዜ ወደ አንዲት እመጫት በማመላከት ባልደረቦቻቸውን፣ "ይህች ሴት ልጇን ወደ እሳት ትወረውረዋለች ብላችሁ ታስባላችሁን?" ሲሉ ጠየቋቸው። እነርሱም፣ "በፍፁም፣ በአላህ እንምላለን አታደርገውም፣ አለማድረግን እስከቻለች ድረስ እንዲያ አታደርግም፤" አሉ። ነቢዩም፣ "ጥራትና ልቅና የተገባው አላህ ለባሮቹ ይህቺ ሴት ለልጇ ከምታዝነው የበለጠ አዛኝ ነው።"[4] አሏቸው።

ሌላ ሐዲስ ደግሞ እጅግ የላቀ ተደርጎ የሚታሰበው የእናት እዝነት ከአላህ እዝነት ጋ ሲነጻጸር የደቂቅም ደቂቅ እንደሆነ ያስታውሰናል። "አላህ እዝነትን መቶ ቦታዎች ላይ በመክፈል፣ ዘጠና ዘጠኙን እራሱ ዘንድ አስቀረ፤ አንዲቷን ወደ ምድር ላካት። በዚህች አንዲት ቁራሽ እዝነት ፍጡራን እርስ በእርሳቸው በመተዛዘን ይኗኗራሉ፤ እንስሳ እንኳ ግልገሉን ላለመጉዳት ሲል ሽሆናውን ያነሳል።"[5]

በዕለታዊ ህይወታችን ውስጥ የአላህ መኖር

ተግባራዊ ሙስሊሞች (ኢስላምን በቁርአንና በሐዲስ ላይ ተመሥርተው የሚተገብሩ ሙስሊሞች) ሁሉ አላህን የህይወታቸው ፍኖት (የትኩረት ነጥብ) አድርገው የሚያዩ ሲሆን፣ ስለመኖሩ እውቅና በመስጠት ብቻ ሳይገደቡ ከዚያም በላይ ለመሄድ የሚሹም አሉ። በኢስላም ታሪክ ከቀደምት ዘመናት አንስቶ አንዳንድ ሙስሊሞች ከሌሎች በበለጠ የአላህን ህላዌ እጅግ ቅርብ እና ዘላቂ በሆነ መንገድ ለማጣጣም ሲተጉ ኖረዋል። እነዚህ እጅግ ጥንቁቅ አማኞች ሃይማኖታዊ ተመስጧቸውን ወደ ፍጽምና ለማድረስ ሞክረዋል። እነዚህ ሙስሊሞች ሙሉ ጊዜያቸውን ፈጣሪን ለማውሳት በማዋል ራሳቸውን ወደላቀ ደረጃ ለመለወጥ ጥረዋል። የፈጣሪያቸውን መለኮታዊ ፍስሐ በመሻትም ራሳቸውን ከስጋዊና ቁሳዊ ክጃሎቶች ለማጥራት ይጥሩ ነበር። የመለኮትን ፀጋ ያገኙ ዘንድ ራሳቸውን ብቁ ለማድረግ



■ ከ17 አመት በታች የግብፅ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾች ጎል ካስቆጠሩ በኋላ አላህን ሲያመሰግኑ ከ17 አመት በታች የዓለም ዋንጫ ጨዋታ ግብጽ እና ቺሌ በካይሮ ስታዲየም

በመሻትም ወደ ወዳጃቸው (ወደ አላህ) ከማያቃርቡ ማንኛቸውም ድርጊቶች ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ያገልሉ ነበር። ስማቸው ማንም ይሁን ማን፣ የእነርሱ ፍላጎት አብደላህ (የአላህ ባሪያ) ተብሎ መጠራት ብቻ ነው።



ምዕራፍ ሁለት

መሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.)

ሙስሊሞች በሰው ልጆች ታሪክ ያለፉ የነቢያነት ታሪኮችን አንድም የዘለአለማዊው እውነት፣ አንድም የምሀረት መለኮታዊ ቃል ኪዳን ማረጋገጫ ቀጣይ መገለጫዎች አድርገው ይመለከቷቸዋል። ቁርአን ነቢዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) "ለዓለማት አዝነት" እንደተላኩ ይገልጻል። የአምላክን የመጨረሻ መልዕክት እንዲወክል የተመረጠው ሰው ራሱን ለአላህ የማይናወጥ እዝነት ሙሉ በሙሉ ያስገዛ ይሆን ዘንድ ግድ ይላል። አንድ ዕለት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ከሃዲያንን እንዲረግሟቸው ሲጠየቁ፣ "ሰዎችን ወደ አላህ መንገድ ልጠራና ለእዝነት እንጂ ለመራገም አልተላክሁም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።[6]

የእርሳቸውን ክብር የሚያዋርድ ተግባር የፈፀመና በመልዕክታቸው ላይ ሲሳለቅ የነበረን አንድ ጎሳ ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ትዕዛዝ ይሰጡ ዘንድ ሲጠየቁ፣ "እንዲጠፋ አልፈልግም። አላህ (ሱ.ወ.) ከልጆቻቸው መካከል የተወሰኑትን አንድ ብቻ የሆነውን አላህ፣ በእርሱ ማንንም ሳያጋሩ የሚገዙ (ጥሩ ሙስሊሞች) እንደሚያደርጋቸው ተስፋ አለኝ።" የነቢዩ ሙሐመድ ተልዕኮና ግብ አንድ ሲኾን፣ ከእርሳቸው በፊት ከተላኩት ነቢያት ተልዕኮና ግብ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ዘመነ ነቢያነታቸው እስኪደርስ አላህ ዘንድ የተቀመጠላቸውን መልዕክት ለሰው ልጆች ማድረስ ነው። ይህም መልዕክት ለአደም፣ ለኑህ፣ ለኢብራሒም፣ ለኢስሐቅ፣ ለዳውድ እና ለሌቹም ከእርሳቸው በፊት በተላኩት ነቢያት ሁሉ የተላለፈው የተውሂድ (የአላህ አሃዳዊነት) መልዕክት ነበር። የአስተምህሯቸው ሥረ መሠረት የእዝነት መለኮታዊ ሞገድ ነው። እጅግ በጣም አዛኝ የሆነው አምላክ መልዕክተኛ እንደመሆናቸው በእያንዳንዷ እርምጃቸው (ድርጊታቸው) ላይ ይህ የእዝነት ባህሪ ታትሟል።

ሙስሊሙ ከነቢዩ መሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር ያለው ግንኙነት

አብዛኞቹ የፈለገ ህይወት መጻሕፍት (biographies) የነቢዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) ህይወት በጊዜ ቅደም ተከተል ይተርካሉ። እነዚህ መጻሕፍት ታሪካዊና ግለሰባዊ አውድ ከማስጨበጥ አኳያ ጠቃሚ ናቸው። ነገር ግን የእርሳቸው ህይወት ዐበይት ክስተቶች ሌላው ይቅርና አቻ ያልተገኘለት ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ድሎቻቸው ትረካ እንኳ ከግል ባህሪያቸው ገለባ ጋር ሲነፃፀር ጠቀሜታው አናሳ ነው። ለዘመናችን ሙስሊሞች ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በከርሰ ታሪክ ውስጥ የተቀበሩ፣ የጥንታዊው ዓለም አካል የነበሩ ሙት ጀግና አይደሉም። ከአንደበታቸው የወጡ ቃላትና አኗኗራቸው

መዲና በሚገኘው የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) መስጂድ በሰልፍ የሚታዩ ቅስቶች

በእያንዳንዱ ሙስሊም ህይወት ውስጥ ቅጽበታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር (ወዲያዊ ፋይዳ ያለው) ሲኾን፣ የህይወት ፈለጋቸው (አርአያነታቸው) ዛሬም ከ1,400 ዓመታት በፊት የነበረውን ያህል ትልቅ ቦታ፣ ትልቅም ፋይዳ ያለው ነው።

የህይወት ምሳሌያቸው ሱንና በመባል ይወሳል። ‹ሱንና› የሚለው ቃል የማንኛውንም ነገር ፈለግ ለመግለጽ ሊውል ቢችልም፣ ዛሬ ቃሉ እጅግ በአመዛኙ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ማለዳ ከእንቅልፍ ከመነሳት አንስቶ ቤተሰባዊ ጉዳይ የከወኑባቸውን ሁኔታዎች፣ ጠላቶቻቸውን በምን መልኩ ያስተናግዱ እንደነበር ሳይቀር ማናቸውንም የምድራዊና የሰማያዊ ህይወት ጉዳዮችን ያከናወኑበትን መንገድ ለማመልከት ነው ጥቅም ላይ የሚውለው። ከዚህም በተጨማሪ ሱንና ግዴታ የሆኑ ተግባራትን እና አማኞች ይፈጽሟቸው ዘንድ ግዴታ ያልተደረጉ፣ ነገር ግን ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ያዘወትሯቸው የነበሩ ተግባራትን ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል። እነዚህም ተጨማሪ ሰላቶችን መስገድ፣ ተጨማሪ ቀናትን መጾም፣ ወይም ሌሎች የአምልኮ ተግባራትን መፈፀምን ያካትታሉ። ብልህ ሙስሊም ሱንናን መከተል ምንዳ የማያስገኝ (ትርፍ የለሽ) "ተጨማሪ ሥራ" መሥራት ብቻ እንዳልሆነ በውል ይገነዘባል። ሱንና አንድ ሰው የአላህን ውዴታ ያገኝ ዘንድ ህይወቱን እንዴት ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊኖረው እንደሚገባ የሚያመላክት ምሉዕና ዝርዝር የአኗኗር ተግባራዊ መመሪያ ወይም ምሳሌ ነው።

ምናልባት ዘመናዊ በሚሰኘው በዚህ ዘመን ሙስሊሞች ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጎላ ብሎ በሚታይ መልኩ ተለይተው ከወጡበት ምክንያቶች አንዱ ይኸው ይሆናል። የነቢዩን ፈለግ (ምሳሌ) በአምልኮ ተግባራት ላይ መከተል አንድ ነገር ነው፤ በአለባበስ እና በዕለታዊ ልማዶችም ቁምር አንድን በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የኖረን ሰው መቅዳት ግን ለአዕምሮ እንቆቅልሽ ይመስላል። ነገር ግን ህይወቱን/ቷን ከአያሌ ምዕተ ዓመታት በፊት በተቀመጠ ፈለግ ላይ በመመሥረት ለመኖር የመረጠ/ች ሙስሊም የሚገነዘቡት አንድ ቁልፍ ነገር አለ፤ እርሱም በትክክል የራሳችን የሆነ (ኦሪጂናል) የአለባበስ ፈለግ መፍጠር (መትከል) የቻልን ሰዎች እጅግ ጥቂት መሆናችን ነው! ያውም ካለን። አነሰም በዛ ሁላችንም የሆንን ሰው፣ የሆነ የአለባበስ ደረጃን እየተከተልን ወይም እየቀዳን ነው። ስለዚህም በዘፈቀዳዊው ወቅታዊ ፋሽን የሚበረታታውን በመልበስ፣ እና የታላቅ ሰብዕና ባለቤት እንደሆነ የሚያምኑትን ሰው ምሳሌ በመከተል መካከል ምርጫ ሲቀርብላቸው፣ የሙስሊሙ/ሚ ምርጫ ግልፅ ነው።

እርግጥ ነው፣ ሁሉም ሙስሊሞች እያንዳንዷን የነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ተግባራዊ ልማዶች በሙሉ አይቀዱም። ይህ በአብዛኛው አንድ ሙስሊም በሚኖርበት አካባቢ እና በአካባቢው ንዑስ ባህል ይወሰናል። የሙስሊም ዩኒፎርም የሚባል ነገር የለም። ነገር ግን፣ የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈለግ የሚከተሉ ሙስሊሞች ይህንን ማድረግ፣ ማለትም የእርሳቸውን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈለግ መተግበር በዓይን የማይታይ መለኮታዊ በረከት እንዳለው ፍፁም እርግጠኛ በሆነ ስሜት ነው።

ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) እና ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.)

የዘመናችን ሙስሊሞች ከሚጋፈጣቸው ፈተናዎች መካከል እጅግ ስሜትን የሚጎዳው እጅግ በጠለቀ የፍቅር ስሜት በሚወዷቸው ሰው ላይ የሚሰነዘረው ግለሰባዊ ጥቃት ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በታሪክ ሙሉ ዕይታ ውስጥ እንደመኖራቸው፣ እያንዳንዷ የህይወት ዘመን ተግባራታቸው ለሰዎች ዕይታም ሆነ ለአስተያየት ክፍት ነው። ለሙስሊሞች ይህ የኩራት ምንጭ ነው። በምድር ላይ ሳሉ የበጎትን እያንዳንዷን ተግባር፣ መንፈሳዊ ፋይዳ የሌላትም እንኳ ብትሆን መከተል ለሚሹ ሙስሊሞች



■ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) በመጀመርያ ከጂብሪል ወሕይ (መለኮታዊ ራዕይ) የተቀበሉበት የሒራ ዋሻ

ይህ (የህይወት ዘመን ተግባራቸው በዝርዝር መዘገቡ) ታላቅ የፈጣሪ በረከት ነው። ነገር ግን ይኸው ሐቅ ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሌሎቹ፣ በደብዛዛ (አጥርቶ በማያሳይ) የታሪክ መነፅር ከሚታዩት ቀደምት ነቢያት እጅግ በሰፊው በተለየ ፈርጅ ውስጥ አስቀምጧቸዋል። ... እጅግ ተደጋጋሚ የሆነው ንፅፅር ነቢዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) ከነቢዩላህ ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) ጋር በማነፃፀር ላይ የሚያተኩር ሲኾን፣ ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) መንፈሳዊነት ሁለተኛ አጀንዳቸው እንደሆነ ወታደራዊ መሪ፣ ኢየሱስን (ዐ.ሰ.) ደግሞ ጠላቶቹ በእርሱና በተከታዮቹ ላይ እንዲገኑ በቸልታ ወይም በተሸናፊነት ስሜት የፈቀደ ደካማ የሰላም መልዕክተኛ አድርጎ የመሳል አባዜ የሚታይበት ነው። ሁለቱም አገላለጾች የእኒህን ታላላቅ ሰዎች ክብር የሚነካ ነው። ከዚህ ባልተናነሰ ደረጃ ንጽጽሩ ራሱም ተቀባይነት የሌለው ነው።

ከኢስላማዊ ጽንሰ ሐሳብ አኳያ፣ ምንም እንኳ ሁለቱም ሰዎች መለኮታዊ መልዕክቱን ያደርሱ ዘንድ በፈጣሪ የተላኩ ቢሆንም፣ የተልዕኳቸው ሁለንተናዊ ቅንብር (logistics) እጅግ በሰፊው የተለያየ ነው። ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ለመላው የሰው ልጅ የተላኩ የመጨረሻው ነቢይ እንደመሆናቸው፣ በሁሉም ዓይነት ሁኔቶች ውስጥ ሰዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የነጠሩ ተግባራዊ ምሳሌዎችን አስቀምጠው

ማለፍ ነበረባቸው። በዚህም መሠረት፣ አግብተዋል፣ ልጆች ወልደዋል፣ ህዝባቸውን በጦርነትም ሆነ በሰላም ወቅት መርተዋል፣ እንደ መናኝ ራሳቸውን አግልለው በፍፁም መንፈሳዊ ተመስጦ የተወሰኑ ወቅቶችን አሳልፈዋል፣ የህዝባቸውን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማጠናከር ጥረዋል፣ የማኅበረሰባቸውን የሙስሊሙንም ሙስሊም ያልሆነውንም ፍላጎት ለሟሟላት መሥራት ያለባቸውን ሠርተዋል፣ አያሌ ዕለቶችን በጾም አሳልፈዋል፣ እንዲሁም ከውጪ መንግሥታት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ትስስር መሥርተዋል።

ሙስሊሞች ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) "ታጋሽና መከራ ቻይ" በሚል የላቀ ክብር ከተወሱ አምስት ታላላቅ የአላህ ነቢያት አንዱ መሆናቸውን ያምናሉ። ከኢየሱስ ጋር ይህ የላቀ ክብር የተሰጣቸው ነቢያት አብረሃም፣ ኖህ፣ ሙሴ፣ እና ሙሐመድ ናቸው።

በአንድ በኩል፣ ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) የሰበኩት ለሦስት አመታት ሲሆን፣ ከአላህ የተሰጣቸውም ለአንድ የተለየ ህዝብ ለእስራኤል ልጆች የታለመ፣ የተወሰነ ተልዕኮ ነበር። በሌላ በኩል፣ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በህዝባቸው መካከል በመልዕክተኝነት፣ በአገር መሪነት፣ እና በጦር ጄነራልነት ከሁለት አሠርት ለዘለቁ ዓመታት የኖሩ ሲሆን፣ በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ገፅታዎች ሁሉ ውስጥ ምሉዕነትን/የተሟላ ምሳሌነትን/ በተግባር ያሳዩ ዘንድ ይጠበቅባቸው ነበር።


ይህም ሆኖ ግን ሁለቱም ነቢያት ፍፁም እውነተኛ በሆነ አባባል <<የፈጣሪ ሰዎች>> ነበሩ። እያንዳንዷን ቅጽበት መለኮታዊ ፈጣሪያቸውን በማውሳት፣ ለተከታዮቻቸውም ፈጣሪን እንዲያልቁት አጥብቀው በማስተማር አሳልፈዋል። ጠላቶቻቸው ከሚሠሯቸው መጥፎ ሥራዎች የተጠበቁ ሲኾን፣ ከጠላቶቻቸው መጥፎ ሥራ ርቀው ብቻ ግን አልቆዩም፤ መጥፎ ሥራው የፈጣሪን ሕግጋት ወደ ማርከስ ደረጃ ሲሸጋገር እነርሱም እርምጃ ወስደዋል። ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) በቤተ መቅደስ ውስጥ የአራጣ አበዳሪዎችን ጠረጴዛ እንደገለበጡት ማለት ነው። ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) ቀኝህን ሲመቱህ ግራህን ስጥ ብለው አስተማሩ፤ ሙሐመድም (ሶ.ዐ.ወ.) ክፋ ሥራን በዚያ በጎ በሆነው ሥራ መልሱ ሲሉ አስተማሩ።

እነዚህ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ወንድማማቾች ነበሩ። ለሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ትምህርቶች ሙሉ በሙሉ ታዛዥነቱን በተግባር የሚገልጥ ሙስሊም፣ በአንጻሩ የኢየሱስን (ዐ.ሰ.) ሰብዕና ዝቅ አድርጎ ቢመለከት አልያም ትምህርታቸውን ቢያናንቅ እርሱ ወይም እርሷ የገዛ ሃይማኖታቸውን /ሃይማኖታዊ ሰብዕናቸውን/ ችግር ውስጥ እንደከተቱ ያህል ነው የሚቆጠረው።

ከዚህ በታች የቀረቡት የነቢዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) ህይወት በተመለከተ በመላው ሙስሊም ዓለም እጅግ በስፋት የሚታወቁ ታሪኮችና ምስክርነቶች ናቸው። በስነ ግጥምና በዝርው የቀረቡ ሲሆን፣ ሙስሊሞች የሚያፈቅሯቸውን እና የሚያከብሯቸውን ታላቅ ሰው ምስል ያንፀባርቃሉ። እኒህ ምሳሌዎች እንዲያው "ጣፋጭ ታሪኮች" ብቻ አይደሉም፤ እጅግ መሠረታውያን ነጥቦች እንጂ። የእኒያ አላህ ለመላው ፍጥረታት የላከውን የመጨረሻ መልዕክት የማድረስ ክብር የተሰጣቸውን ታላቅ ሰው ገጽታ የሚስሉ የጥበብ አሻራዎች ናቸው።

<<በዚህኛው ዓለምም ይሁን በመጪው ህይወት፣ እኔ ከህዝቦች ሁሉ የበለጠ ለኢሳ የመርየም ልጅ ቅርብ ነኝ። ነቢያት ሁሉ ወንድማማቾች ናቸው፤ እናቶቻቸው ይለያያሉ፣ ነገር ግን የሁሉም ሃይማኖት አንድ ነው።>>

ኢማም ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል ቡኻሪ



የነቢዩን (ሶ.ወ.ወ.) አካላዊ ገፅታ በጽሑፍ መግለጽ ከኢስላማዊ ስነ ጥበባት ውስጥ እጅግ ታዋቂው ነው

የሰዎችን ስሜት አዳማጭነት እና ደግነት

ከነቢዩ ሚስቶች በዕድሜ ወጣት የነበሩት እመት አዒሻ (ረ.ዐ.) እንደተናገሩት፣ የቤት ሠራተኛንም ይሁን ሴትን ለመምታት አንድም ጊዜ እጃቸውን ሰንዝረው አያውቁም፤ ነገር ግን በአላህ መንገድ ተዋግተዋል። በራሳቸው ላይ የተፈፀሙ በደሎችን አንድም ጊዜ ተበቅለው አያውቁም፣ ነገር ግን መለኮታዊ ትዕዛዛትን በመተላለፍ የተፈፀሙ በደሎችን ተበቅለዋል።
ከመካ ጣዖታውያን አንዱ የሆነው ገውራዝ ቢን አል ሐሪስ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ከዛፍ ስር ብቻቸውን አረፍ ብለው ሳለ ሊገድላቸው መጣ።

ነቢዩም እንዳዩት አጠገባቸው ደርሶ ጎራዴውን መዝዞ እስኪቆም ድረስ ካሉበት ሁኔታ ሳይንቀሳቀሱ ቆዩ። ገውራዝም ነቢዩን፣ "ማን ነው አሁን ከእኔ የሚያስጥልህ?" ሲል ጠየቃቸው። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ.) መለሱለት፣ "አላህ።" ሰውየው በምላሻቸው ተደንቆ እንደማሸካካት ሲቃጣ ሰይፉ ከእጁ ወደቀ፤ ነቢዩም ከተቀመጡበት ፈጥነው በመነሳት ሰይፉን ከወደቀበት አንስተው ሰውየው ላይ በመደቀን፣ "አሁን ከእኔ የሚያስጥልህ ማን ነው?" ሲሉ ጠየቁት። "ቅጣኝ ከእጅህ ወድቄአለሁ" አላቸው። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ሰይፉን መሬት ላይ ጣሉትና ይቅርታ አደረጉለት። ወደ ግብረ አበሮቹ ሲመለስ ጋውራዝ፣ "ከሰዎች ሁሉ ምርጥ ከሆነው ሰው ዘንድ መጣሁላችሁ!"[8] በማለት ተናገረ።

ደግነት

ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች አንዱ የሆነው ጀቢር ቢን አብዱላህ እንደተረከው፣ "የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) በእምቢታ የመለሱት አንድም ነገር አልተጠየቁም።"

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ዘንድ ምጽዋት ለመጠየቅ መጣ። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ.) "ምንም የለኝም፣ ነገር ግን በእኔ ስም የሆነ ነገር ግዛና እኔ ገንዘብ ሳገኝ መልሼ እከፍለዋለሁ" አሉት። በዚህን ጊዜ ከቅርብ ባልደረቦቻቸው አንዱ የሆኑት ዑመር (ረ.ዐ.) ተቃወሟቸው፣ "አላህ የማይችሉትን ነገር መፈፀምን ግዴታ አላደረገብዎትምኮ!" ሌላ የመዲና ሰው የሆነ ባልደረባቸው በበኩሉ፣ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይለግሱ፣ ከዙፋኑ ጌታ ዘንድ ያለዎ ርዝቅ ይቀንሳል ብለው አይስጉ" አላቸው። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ.) በዚህኛው ተደስተው "እንደዚያ ነው የታዘዝሁት"[9] በማለት መለሱ።

መተናነስ

አዒሻ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ "ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) የሚበልጥ ባህሪ ያለው አንድም ሰው አልነበረም። ከባልደረቦቻቸው አልያም ከቤተሰባቸው አባላት አንድኛቸው ሲጠሯቸው መልሳቸው "ለበይክ" ("ምን ልርዳህ/ሽ") የሚል ነበር። [10]የኢትዮጵያ (ንጉሥ) ልዑካን እርሳቸው ዘንድ በደረሱ ጊዜ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ራሳቸው ሊያስተናግዷቸው ተነሱ። ባልደረቦቻቸው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ለማስተናገድ መነሳታቸውን በመቃወም፣ "እኛ እናስተናግዳለን፣ እርስዎ ይቀመጡ" አሏቸው። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ግን እሺ አላሉም፤ ይልቁንም፣ "ለባልደረቦቼ መልካምን በማድረግ አክብረው አስተናግደዋል፣ ስለዚህም እኔ ወሮታቸውን መክፈል እሻለሁ።"[11]



በቅርቡ ከሚና ሸለቆ በስተምስራቅ የተገኘው የቃል ኪዳኑ መስጂድ ነቢዩ /ሰ.ወ/ ከመዲና ጎሳዎች የቃል ኪዳን መሃላ የተቀበሉበት ሥፍራ ነው

በጦርነት ላይ ከተማረከ በኋላ ተለቆ ወደ ህዝቦቹ ከመመለስ ይልቅ የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) አገልጋይ ለመሆን የመረጠው አነስ እንደተረከው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ኮርቻ በተደረገበት ውርንጭላ ላይ ሆነው በሚጓዙበት ወቅት አገልጋዮች የሚያቀርቡላቸውን ግብዣ አንድም ጊዜ እምቢ ብለው አያውቁም። ብዙም ጣዕም የሌለው ተራ ምግብ አብረዋቸው እንዲበሉ በሚጋብዟቸው ጊዜም ግብዣውን በአክብሮት ተቀብለው ይመገቡ ነበር። [12]

ባልደረቦቻቸው "አንቱ ምርጥ ፍጡር" ብለው ሲጠሯቸው፣ እርሳቸው በፍፁም የመተናነስ ስሜት ይህን ማዕረግ በመቃወም፣ "ይህ (ማዕረግ) የኢብራሂም ነው" ይሉ ነበር።[13]

ታጋሽነት እና እርጋታ

ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በአንድ ወቅት አነስተኛ ወንጀል የፈፀመን አንድ ደሃ የሰራውን ወንጀል አላህ ይሰርዝለት ዘንድ ለድሆች ምጽዋት (ሶደቃ) እንዲሰጥ መከሩት። ሰውየው ለሶደቃ ሊያውል የሚችልው አንዳችም ነገር እንደሌለው ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) በመንገር ላይ ሳለ አንድ ሰው በቅርጫት ተምር ይዞ ወደ መስጂድ በመምጣት ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) በስጦታ አበረከተላቸው።

በመኖሪያ ቤታቸው አንዳችም ትርፍ ነገር ባለማስቀመጥ የሚታወቁት ነቢይም (ሶ.ዐ.ወ.) በተምሮች የተሞላውን ቅርጫት ለደሃው ሰውዬ በመስጠት ተምሮቹን ለድሆች እንዲያከፋፍል ነገሩት። ደሃው ሰውዬ በበኩሉ ከእርሱ ያነሰ ደሃ ሰው እንደማያውቅ ነገራቸው። በዚህን ጊዜ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ፈገግ አሉና አላህ ጥፋቱን ይምረው ዘንድ ተምሮቹን ወስዶ ለራሱ ቤተሰብ አባላት እንዲሰጣቸው መከሩት።[14]

ፍትኅዊነት

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ያለአንዳች ደም መፋሰስ ዳግም ወደ መካ በድል አድራጊነት የገቡት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ባልደረቦቻቸውን አስከትለው ነበር። ወደ ከተማይቱ እንደተቃረቡ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ከመንገድ ዳር አንዲት ወሻ ቡችሎቿን እያጠባች ስትንከባከብ አስተዋሉ። በዚህን ጊዜም ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ውሻይቱ በሰልፈኛው ሠራዊት ደንብራ ቡችሎቿን ማጥባት እንዳታቋርጥ በመስጋት ከጀነራሎቻቸው አንዱን አጠገቧ ቆሞ ሰልፈኛው እስኪያልፍ ድረስ እንዲጠብቃት አዘዙት።

وأما من خاف مقام ربه ونهى النفس عن الهوى فإن الجنة هي المأوى
يسألونك عن الساعة أيان مرساها فيم أنت من ذكراها إلى ربك منتهاها إنما
أنت منذر من يخشاها كأنهم يوم يرونها لم يلبثوا إلا عشية أو ضحاها

سورة عبس اثنتان وأربعون آية مكية

بسم الله الرحمن الرحيم

عبس وتولى أن جاءه الأعمى وما يدريك لعله يزكى أو يذكر فتنفعه
الذكرى أما من استغنى فأنت له تصدى وما عليك ألا يزكى وأما من
جاءك يسعى وهو يخشى فأنت عنه تلهى كلا إنها تذكرة فمن شاء ذكره
في صحف مكرمة مرفوعة مطهرة بأيدي سفرة كرام برره قتل
الإنسان ما أكفره من أي شيء خلقه من نطفة خلقه فقدره

ቁርአን

‹‹ከቁርአንም ለምእመናን መድኀኒትና እዝነት የሆነን እናወርዳለን፤›› (17:82)

ሙስሊሞች ለታላቁ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ.) ያላቸው ውዴታ፣ አክብሮት እና ፊለጋቸውን የመከተል ብርቱ ፍላጎታቸው በምድር ላይ የሃይማኖታቸው ዋነኛ ማዕከል ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ከማወቅ ከቶውንም አልጋረዳቸውም። ያለ አንዳች ጥያቄ ያንን ታላቅ ደረጃ የያዘው የአላህ (ሱ.ወ.) ቋሚ ተአምር የሆነው ቁርአን ነው። ለሐዲስ የሚሰጠው ክብደት ለቁርአን ከሚሰጠው ክብደትና ፍፁም ጥርጥር አልባነት አኳያ ሲመዘን በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው። ማንኛውም ሙስሊም በቁርአን ሽፋን ላይ እጁን ከማሳረፉ በፊት፣ ሰላት ለመስገድ አስፈላጊ የሆነውን ትጥበት የግድ መከወን አለበት። የአላህ (ሱ.ወ.) የመጨረሻ ኪዳን እንደመሆኑ፣ ቁርአን ለሰው ልጆች ቀደም ባሉ ነቢያት አማካይነት የተላለፉ መልዕክቶች ሁሉ ማጠቃለያ እና እስከ መጨረሻይቱ ሰአት (ዕለተ ትንሳዔ) ለእያንዳንዱ ግለሰብ መምሪያ ይሆን ዘንድ የታለመ መልዕክት ነው።

የኢምካክ ቃል

በቁርአን ውስጥ የሚገኙት ቃላት መጀመሪያ ነቢዩ (ከጂብሪል) በተቀበሉበት መልኩ፣ እጅግ ጥቃቅን የሚባሉ ዝርዝር ነጥቦች እንኳ ሳይቀሩ በታማኝነት ተጠብቀው ይገኛሉ። በመጀመሪያ ቃላቱ በቃል ነበር የሚጠኑት፤ ከዚያም ለዚህ ዓላማ የተመደቡ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ፀሐፊዎች አንቀጾቹን በጽሑፍ በማኖር መልሰው ለነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ያነብቡላቸው ነበር። በኸሊፋው ዑስማን (ረ.ዐ.) ዘመን [ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ህልፈት በኋላ ሦስተኛው የሙስሊሞች መሪ] በተለያዩ ቁሳቁሶች ላይ በጽሑፍ የተመዘገቡት የቁርአን አንቀጾች በጥራዝ ውስጥ ተሰብስበው ኦፊሴላዊ ቅጂዎች ተሰናዱና በተለያዩ አቅጣጫዎች ወዳሉት ኢስላማዊ ግዛቶች ተሰራጩ። በአሁኑ ጊዜ በምድራችን ዙርያ በሚገኙ መስጂዶች፣ በእያንዳንዱ ሙስሊም ቤት ውስጥ የሚገኙት የቁርአን ቅጂዎች በእነዚያ የመጀመሪያዎቹ ኦፊሴላዊ ቅጂዎች ውስጥ የነበሩትን ቃላት እንዳለ ይዘው ይገኛሉ።

ብዙዉን ጊዜ የሙስሊሞች ቁርአን የ(ክርስቲያኖች) መጽሐፍ ቅዱስ እኩያ ተደርጎ ይጠቀሳል። ይህ ግንዛቤ ኦሪጂናሎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና ለኢየሱስ የተወረደው ኦሪጂናል ኢንጂል (ወንጌል)፣

እንዲሁም ቁርአን ከአንድ ምንጭ የተቀዱ መለኮታዊ መልዕክቶች መሆናቸውን ለማውሳት ከሆነ ትክክለኛ ነው። ነገር ግን፣ ከዚያ በተሻለ ነገሮችን ለማብራራት ወይም ግልጽ ለማድረግ ቁርአንን ከኢየሱስ (ዐ.ሰ.) ጋር በማነጻጸር ማየት ይቻላል። ክርስቲያኖች ኢየሱስን (ዐ.ሰ.) በስጋ የተገለጠ የአምላክ ቃል አድርገው እንደሚረዱት፣ ሙስሊሞችም ቁርአንን ቀጥተኛ የአላህ ቃል ነው ብለው ያምናሉ።[15] መልአኩ ገብርኤል (ዐ.ሰ.) የመፀነሷን ብሥራት ይነግራት ዘንድ በተገለጠላት ጊዜ ማርያም ማንም ወንድ ያልነካት ንፁህ እንደነበረችው ሁሉ፣ የቁርአን አስተላላፊ የሆኑት ነቢዩ ሙሐመድም (ሶ.ዐ.ወ.) መለኮታዊውን ቃል እንዲያነብቡ ሊያዝዛቸው መልአኩ ገብርኤል መጀመርያ በመጣቸው ጊዜ ፊደል እንኳ ያልቆጠሩ ንፁህ ሰው ነበሩ።

የቁርአን ቋንቋ

የነቢያነት ተልዕኳቸው በይፋ ከተጀመረ በኋላ በቀጣዮቹ ሃያ ሦስት ዓመታት ቁርአን ለነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) አንቀጽ በአንቀጽ መውረዱን ቀጥሏል። የቁርአን አንቀጾች እንደተወረዱላቸው፣ አርሳቸው አዲሶቹን አንቀጾች ለባልደረቦቻቸው እያነበቡላቸው አንቀጾቹ ወዲያውኑ በቃል ይጠኑ ነበር። አረቦች ጠንካራ የስነ ቃል (የቃላዊ) ባህል ያዳበሩ እንደመሆናቸው ረዣዥም ንባቦችን ሳይቀር አንድ ጊዜ ብቻ ከሰሙ በኋላ በቃል መያዝ እና ማነብነብን ህጻናቱ ሳይቀሩ ያዳበሩት ከሂሎት ነበር። በሰው ልጅ ሰፊ የታሪክ ዑደት ውስጥ በተከሰተው በዚያ ታሪካዊ ወቅት በተለይ ይህንን የማኅበረሰብ ክፍል የቁርአንን ተዓምራዊ ባህሪ እንዲጨብጥ ያስቻለው ለዚህም እጅግ የተመቸ ያደረገው በከፊል ይኸው የዳበረ የቃላዊ ባህልና የቁርአኑ ቃላትም የላቀ ስነ ግጥማዊ ደረጃ ነበር ማለት ይቻላል።

የአላህ እዝነት አንዱ ገፅታ የህያውነቱ (የህልውናው) "መከራከሪያ" እና ማረጋገጫ ለአመክንዮም ሆነ ለልብ ዝንባሌ የማይሻክር ወይም የማይጎረብጥ መሆኑ ነው። እያንዳንዱ ነቢይ የተላከው የጌታውን ማኅተም ከያዘ ምልክቶች ጋር ነው። ነቢያት ሲላኩ የመልዕክቱ ተቀባይ ህዝብ እጅግ ልቆ በሚታወቅበት ከሂሎት አኳያ እና ተዓምራዊ እንደሆነ ሊገነዘብ ከሚችለው ምልክት ጋር የሚላኩ ሲሆን፣ ይህም ህዝባቸው ወደ እምነት የሚመጣበትን ሁኔታ በማመቻቸት ዓላማ የሚደረግ ነው።

ነቢዩሏህ ሙሳ (ዐ.ሰ.) ወደ ፈርኦን እና ሕዝቦቹ ሲላኩ፣ በዘመኑ የነበሩትን ታላላቅ አስማተኞች የሚያስንቅ ተዓምራዊ ከሂሎትንም ጭምር ተሰጥተው ነበር። ነቢዩላህ ኢሣ (ዐ.ሰ.) በተላኩ ጊዜም ከየትኛውም የዘመኑ የህክምና ጠቢብ ከላቀ ከሂሎት ጋር ነበር የተላኩት። በተመሳሳይ መልኩ፣ ከኢስላም በፊት የነበሩት አረቦች በንግግር ከሂሎታቸው ተወዳዳሪ አልነበራቸውም። ባለቅኔዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚከበሩ ሲኾን፣ የንግግር ከሂሎታቸው የላቀ በመሆኑ ምክንያት እጅግ ከፍተኛ ተሰሚነት ነበራቸው። የየንገዶቻቸው ታሪክ አዋቂ፣ ፕሮፓጋንዲስት እና አፈ ቀላጤዎች ሆነው ይንቀሳቀሱ ነበር። የታሪክ ምሁሩ ፊሊፕ ኬ. ሒቲ እንደጻፈው፣ "አረባዊው ስነ ግጥም በአሰካክ ምጣኔው ውስብስብነትና በፈርጀ-ብዙነቱ ከ'ኢሊያድና ኦዲሴ' እንኳ እጅግ የላቀ ነበር። በህያው ስሜቶች የበለፀገ፣ በኃያል እና እምቅ ቋንቋ የሚገለጽ ነበር።"[16]

ቁርአን በእነዚህ የቃል አድናቂ ህዝቦች መካከል መነበብ ሲጀምር፣ ምላሹ እጅግ አስደማሚ ነበር። በሰው እጅ ተጠፍጥፈው የተቀረፁ ጣዖታት የማምለክ ልማዳቸውን ሙጥኝ እንዳሉ ለመቀጠል የወሰኑ አረቦች፣ በድንገት የቁርአን ንባብ ሰምተው በአድናቆት እንዳይንዘረዘሩ በመስጋት ጆሮዎቻቸውን በአንዳች ነገር እንዲደፍኑ ይመካከሩ ነበር።



የቴክኖሎጂ ውጤቶች የቁርአንን አስፈላጊነት በሚያጎላ መልኩ ዋቅም ላይ ውለዋል

የዘመኑ ባለቅኔዎች ይጠቀሙባቸው ከነበሩት እጅግ ቁንጠኛ ስነ ግጥማዊ ስልቶች አንዱቱም አንኳ ቁርአን ውስጥ ጥቅም ላይ አልዋለችም፤ ያም ሆኖ ቁርአን የዘመኑ ታላላቅ የአረብ ባለቅኔዎች ካሰናጇቸው ስነ ግጥሞች በእጅጉ የላቀና የመጠቀ ነበር። በሰዋሰው ረገድ እንከን አልባ ሲኾን፣ ዛሬም ድረስ የጠራ አረብኛ ለማስተማር በመሠረትነት ጥቅም ላይ ይውላል። ማንበብና መጻፍ ከማይችል፣ በህይወቱ አንድ መስመር ግጥም እንኳ አንብቦ እንደማያውቅ ከሚታወቅ ሰው ይህ መሰማቱ በራሱ ተአምር ነበር፥ ለብዙዎች በቁርአን መለኮታዊ ድርሳንነት ላይ የሚነሳ ማንኛውም ጥርጣሬን ውድቅ ለማድረግ ይህ በራሱ በቂ ምክንያት ነበር። ነገር ግን፣ ልክ ድንግል ማርያም በስድ ሴትነት እንደተወነጀለችው ሁሉ፣ እንዲሁ የቁርአንን "ትክክለኛ" ምንጮች የተመለከቱ ክሶችን ለማቅረብ የሚሞክሩ አንዳንዶች አሉ።

ቁርአንን በእንግሊዝኛ አልያም ከተወረደበት አረብኛ ውጪ በሆነ በሌላ በማንኛውም ቋንቋ ማንበብ ለአንባቢው የመጽሐፉን ግርማ ሞገስ በምልዓት አይሰጥም። ከየትኛውም የጽሑፍ ዘር እጅግ በላቀ ደረጃ፣ በቁርአን ውስጥ ይዘት እና የይዘቱ ተሸካሚ (ቅርፁ) የማይነጣጠሉ ናቸው። በቁርአን ስነ ልሳናዊ ትንግርቶች ዙርያ በመቶዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት ተጽፈዋል። በአረብኛ ቋንቋ እጅግ አስደማሚ የሆኑት እነዚህ የቃላት ቀመሮች፣ ያለ ዝርዝር ማብራሪያ ድጋፍ በሌላ በየትኛውም ቋንቋ ሊተረጎሙ አይችሉም። ለዚህም ነው የቁርአን ትርጉሞች ለግንዛቤ እንደሚያግዙ የፍቺ ማብራሪያዎች እንጂ አንዳንዶች በተሳሳተ መንገድ እንደሚያስቡት የቁርአን ቅጂዎች "versions" አይደሉም የሚባለው። ሙስሊሞች የቅዱስ መጽሐፋቸውን ወጥነትና ተዓማኒነት በመጠበቅ ረገድ ፍፁም በተለየ ሁኔታ በስኬታማነት ዘልቀዋል። ይህም ከመለኮታዊው ቃል ኪዳን ጋር የተጣጣመ ነው፥ "እኛ ቁርአንን እኛው አወረድነው እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን።" (15:9)

በሁሉም ቋንቋዎች ሊባል በሚችል ደረጃ የቁርአን ትርጉሞች አሉ፤ ነገር ግን ትርጉም እንደ ቁርአን አይወሰድም፤ የትኛውም የቁርአን ትርጉምም የአረብኛውን ቁርአን ያህል ያለመገሰስ ወይም ያለመደፈር ባህሪ የለውም። ከዚህ በላይ የተባለው ሁሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ማንኛውም አረብኛ ተናጋሪ ያልሆነ ሰው ቁርአንን በትርጉምም ቢሆን ሲያነብብ ስለ ውበቱና ኃያልነቱ ሊመሰክር ይችላል፤ ይህም ምናልባት ሌላው የተዓምራዊነቱ አመላካች ነው።

የእዝነት መልዕክት

እጅግ በጣም አዛኝ የሆነው አምላክ በእዝነቱ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ.) አማካይነት መልዕክት ሲልክ፣ መልዕክቱ ራሱ እዝነት መሆኑ የሚጠበቅ ነው። አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡ "ቁርአንን ባንተ ላይ እንድትቸገር አላወረድንም።" (20:2) ምንም እንኳ ይህ አንቀጽ በቀጥታ ነቢዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) ቢያመላክትም፣ መልዕክቱ ቁርአኑን ለሚያነብቡት ሁሉ ይሠራል። ልክ እንደ ኦሪጂናሎቹ ወንጌሎች ሁሉ ቁርአንም ለምዕመናን የምስራች አብሳሪ መጽሐፍ ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) "አብሳሪ እና አስጠንቃቂ" ሁነው እንደተላኩት ሁሉ፣ ቁርአንም እንዲሁ ብርቱ እና የማይዋዥቅ የማበረታቻ እና የቃል ኪዳን ድምፆችን ይጠቀማል። ከአንድ በቀር በሁሉም የቁርአን ምዕራፎች ግንባር ላይ የሚገኘው "በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ፣ በጣም አዛኝ በሆነው" የሚል መግቢያ ከቶም ትርፍ ነገር አይደለም። ቁርአን በመጠን ትልቅ መጽሐፍ አይደለም። በእነዚህ ውሱን ገጾች ውስጥ አንድ ሐረግ አሁንም አሁንም እየተደጋገመ ይህን ያህል ቦታ መባከኑ አንድ የራሱ ትርጉም ሊኖረው ግድ ነው።



■ በኩፋዊ የፊደል አጣጣል የተጻፈ የ9ኛው ክፍለ ዘመን ባለ ሰማያዊ ቀለም ቁርአን ቅጂ አንድ ገፅ

"ከሚያስተውሉ ሕዝቦች"

ቁርአን ሞጋች ነው። ከቶውንም በፈዘዘ መንፈስ የሚነበብ መጽሐፍ አይደለም። ይዘቱም ሆነ ፍጥነቱ አንባቢው ከቃላቱና ከፍቺው ጋር በማያቋርጥ መስተጋብር ውስጥ እንዲሆኑ ያስገድዳል። ሌላው ይቅርና በኢስላማዊ ማኅበረሰብ ውስጥ የተወለዱም እንኳ እንደዋዛ የሚሰለቅጡት አይደለም። አምላክ በቁርአን ፍጥረታቱን የተማሩትንም ሆነ ያልተማሩትን፣ ዘመናውያኑንም ሆነ ጥንታውያኑን በማየት፣ በማስተንተንና ለአቅላቸው ከመተናነስ የመነጨ እውቅና በመስጠት ወደ እምነት እንዲመጡ ይሞግታቸዋል። ቁርአን ስለ ፍጥረተ ዓለም ፍፁም ልከኛነት (perfection) ሲናገር እያንዳንዱ ግለሰብ ከራሱ ምርጫ አኳያ ሊያይ ስለሚወደው ዓለም እያወራ አይደለም።

ያየመጪው ዓለም (መንግሥተ ሰማያት) ጉዳይ ነው። ከዚያ ይልቅ ቁርአን የሚናገረው አንዳችም መፋለስ በሌለበት ቅንብር በየምህዋሩ እየዋኘ የሰው ልጆች የሚተነፍሱት ቅንጣት ትንፋሽ ዕውን ይሆን ዘንድ በህብር ስለሚተጋው ልዕለ ዩኒቨርስ፣ ምድሪቱንበረዶእንዳይውጣት እጅግምሳትርቅ፣ ምድሪቱዶጋመድእንዳትሆንም እጅግም ሳትቀርብ ፍፁም ልከኛ ቦታዋ ላይ ስለምትገኘው ፀሐይ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአን፣ (እርሱም ሌሊትንና ቀንን፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የፈጠረ ነው፤ ሁሉም በፈለካቸው (በመዞሪያቸው) ውስጥ ይዋኛሉ።) (21:33) በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.)፣ "ሁለቱን ባህሮች የሚገናኙ ሲሆኑ ለቀቃቸው። (እንዳይዋሃዱ) በመካከላቸው ጋራጅ አልለ፤ (አንዱ በአንዱ ላይ) ወሰን አያልፋም፤"

(55:19–20) ይላል። ይህ አንቀጽ የሚያወሳው ለሰው ዘር ህልውና ቀጣይነት ቁልፍ ስለሆነው ጨዋማ ውሃንና ጨዋማ ካልሆነው ንፁህ ውሃ የሚለይ በዓይን የማይታይ ድንበር ነው። በእነዚህ ሁለት አካላት መካከል አንዳች ስንጥቅ ቢፈጠር ኖሮ፣ የዓለማችን መልክአ ምድር ሳይውል ሳያድር በረሃማ በሆነ ነበር።

ቁርአን በዕለት ከዕለት ህይወት

ሙስውን ቁርአን በተመሰጠ ማንበብ በመላው የሙስሊሙ ዓለም አዘውትሮ የሚከናወን የተለመደ ተግባር ነው። ህጻናት ከአፍላ ዕድሜአቸው አንስቶ የቁርአን አንቀጾችን መሸምደድ ይጀምራሉ፤ የወጣት ወንዶች እና ሴቶች ሙስውን ቁርአን በቃላቸው ሸምድዶ የመያዝ ልማድም ዛሬም ቀጥሏል። አንድ ሰው አዲስ መኖሪያ ቤት ቀይሮ ሲገባ የቤተሰቡን አባላት እና ጓደኞቹን በአዲሱ ቤቱ ሰብስቦ ሙስውን ቁርአን አልያም ከፊሉን ማንበብ የተለመደ ነው። ከማኅበረሰቡ አባላት አንዱ/ዷ በሞት ሲለዩ፣ ቁርአን የቀሩ ወዳጅ ዘመዶች በቤተሰቡ/ቧ ዙርያ ተሰባስበው እያንዳንዳቸው አንድ አንድ የቁርአን ምዕራፍ በማንበብ በድምሩ ከሙስው የቁርአን ንባብ የሚገኘው ሰዋብ (ምንዳ) ለሟቹ እንዲደርስ ፈጣሪን ይለምናሉ። አንዳንድ የቁርአን ምዕራፎች ወይም አንቀጾች ለተለዩ ጉዳዮች ይነበባሉ። ጋብቻን የሚያወሳው የቁርአን አንቀጽ የማይነበብበት የሙስሊም ሠርግ በጣም ጥቂት ነው። "ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ።" (30:21)



ምዕራፍ አራት

ኢስላማዊ አስተምህሮ

ከክስተቶች ቅደም ተከተል አኳያ፣ ቁርአን ውስጥ ከተወሱ ቀዳሚ ታሪኮች አንዱ በማስተማር ላይ የሚያጠነጥን ነው። አላህ (ሱ.ወ.) አደምን (ዐ.ሰ.) ከፈጠረው በኋላ ያስተምረው ጀመር፤ "ስሞችንም አስተማረው" ይለናል ቁርአን። ቃል በቃል ቢወሰድ እንኳ እጅግ ከፍተኛ ቁምነገር ያዘለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ትረካ የነገሮችን እውነታ፣ እውነትን ከሐሰት የመለየትን አስፈላጊነት ያስገነዝባል። ይህ ኢስላማዊው ታሪክ የተመሠረተበት መርኅ ነው። "ለራስ" እውነተኛ (ታማኝ) መሆን ማለት እንዳሻ መሆን እና ወደጥፋት በሚያመራ መልኩ መንቀሳቀስ ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ነገሮችን በራስ ውስጥና በውጫዊው ዓለም አኳያ በጥንቃቄ ማስተዋል፣ እንዲሁም ነገሮችን እንዲሆኑ በምንመኘው መልኩ ሳይሆን በተጨባጭ ምንነታቸው፣ (ባሉበት ሁኔታ) ማየት ማለት ነው። እውነተኛ የራስ ማንነት ከወይት እንደተገኘና የህልውናውን (የመኖሩን) ዓላማ የሚያስተነትን ያልተበረዘ ነፍስ ማለት ነው።

ጃዕፈር (ረ.ዐ.) ለነጃሽ (ረ.ዐ) ያደረገው ንግግር፥

ንጉሥ ሆይ፣ መሃይማን እና ምግባረ ብልሹ ህዝቦች ነበርን፤ በእጃችን ጠርበን የሠራናቸውን ጣዖታት እናመልክ፣ የበከተ እንመገብ፣ ፀያፍ እና አሳፋሪ የተባሉ ነገሮችን ሁሉ እንፈፅም ነበር። ዝምድናን እንቆርጣለን፤ ለእንግዶች ክብር አልነበረንም፣ ከመካከላችን ኃይለኛው ደካማውን ያጠቃል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን አላህ ከመካከላችን ዘሩን እውነተኛነቱን፣ ታማኝነቱን እና ቃል አክባሪነቱን ጠንቅቀን የምናውቀውን ነቢይ ላከልን። ይህ ነቢይ አላህን በብቸኝነት እንድናመልክ፣ እኛም ሆንን አባቶቻችን ያመልኳቸው የነበሩ ጣዖታትን በአላህ ላይ ደርበን ከማምለክ እንድንታቀብ ጥሪ አቀረበልን። እውነትን እንድንናገር፣ ቃላችንን እንድናከብር፣ ዝምድናን እንድንቀጥል፣ ለጎረቤቶቻችን አጋር እንድንሆን፣ እርም ከሆኑ ነገሮች ሁሉ እንድንርቅ፣ ነፍስን ያለ አግባብ ከማጥፋት እንድንታቀብ፣ ከዝሙት እንድንርቅ፣ በሐሰት እንዳንመሰክር፣ የሙት ልጆችን ገንዘብ እንዳንበላ፣ የንፁሃን ሴቶችን ስም ከማጥፋት እንድንቆጠብ አዘዘን።

በግብፅ፣ ካይሮ፣ የሚገኘው የአዝሐር ዩኒቨርሲቲ ተማሪ መስጂድ ውስጥ የጥናት ወረቀቱን ሲሠራ



■ አንዲት ሴት ሮም በሚገኘው ዋና መስጂድ የጁሙዓ ሶላት ስትሰግድ

ንፁሁ የሰው ልጅ

ኢስላም እንደሚያስተምረው፣ የሰው ልጆች በሙሉ ከነቢዩ አደም (ዐ.ሰ.) እስከ ዘመናዊው ሰው "በጣም በአማረ አቋም" (95:4) ንፁህ ሆነው ነው የተወለዱት። ከዚያም ባሻገር፣ ሰዎች አምላክን በመሻት ውስጣዊ ፍላጎት የተቃኙ ናቸው። ልክ እዕዋት በተፈጥሮ እየተለመጡ ወደ ፀሐይ ብርሃን አቅጣጫ እንደሚዞሩ ሁሉ፣ የሰው ልጆችም ከእነርሱ የላቀ ወደሆነ ህላዌ የሚያስከጅል "በልቦቻቸው ውስጥ ያለ አምላክ ሰራሽ ክፍተታቸው" ይሰማቸዋል። ይህ ተፈጥሯዊ ውስጣዊ ስሜት "ፊጥራ" ይባላል። አላህ በቁርአን፣ "ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤ የአላህን ፍጥረት፣ ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)" (30:30) ይላል። የአንድ ሰው ፊጥራ በገዛ ባለቤቱ ሊበላሽ (ሊላሸቅ) የሚችል ሲኾን፣ የነቢያት ሚና የሰው ልጆችን ተግባራት ተፈጥሯዊ ከሆነው ለፈጣሪያቸው የመገዛት ዝንባሌ ጋር ማስታረቅ ነው። ይህ ማለት በሌላ አነጋገር የሰው ልጅ (በነቢያት) የሚስተማረውን ያውቀዋል፣ ግና በነፃ ፈቃድ (free will) ላይ ተንጠላጥሎ በሚመጣበት ውስዋስ ሳቢያ፣ በአንድ ወቅት ፍፁም ወደነበረው ተፈጥሯዊ የተገዢነት ዝንባሌ እንዲመለስ የማስታወሱ አስፈላጊነት ግድ ይሆናል። ወዲያዊ ሊባል በሚችል መልኩ ለሰዎች ግልጽ ሆነም አልሆነ በኢስላማዊው አስተምህሮ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር ወደዚህ ዐብይ ሐቅ ነው የሚመለሰው።

በኢስላም የውርስ ኃጢአት ብሎ ነገር የለም ማለት የአንዱ ነፍስ የሠራውን ኃጢአት ሌላው አይሸከመውም ማለት ነው። ዘለዓለማዊ ደህንነት በአምላክ እዝነት አማካይነት ነው የሚገኘው። የሰው ልጅ ለዚህ እዝነት የሚታጨውም (የእዝነቱን በረከት የሚያገኘው) ለፈጣሪ ፈቃድና ትዕዛዝት በመገዛት ነው።

ተግባራዊ እጅ መስጠት

ኢስላም የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ "እጅ መስጠት" በሚል፣ ሙስሊም ደግሞ "ለፈጣሪ ፈቃድ እጅ የሰጠ" በሚል ይተረጎማል። በዚህ ትርጉም ላይ ያለው ችግር ሙስሊምነት (እንደ ትርጉሙ አገባብ) ከተከታዩ ንቁ (ተግባራዊ) ተሳትፎ ገለልተኛ በሆነ መልኩ በራሱ እውን የሚሆን ወይም መሆኑ የተደመደመ ማስመሰሉ ነው። ይህ ግን ከኢስላማዊ አስተምህሮ በእጅጉ የራቀ ነው። ግና አንድ ሙስሊም በንቃት ለፈጣሪ ፈቃድ እጅ እንዲሰጥ ቢጠየቅ፣ ያ በዕለት ከዕለት ህይወት ደረጃ ምን ማለት ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ በዛሬው ዘመን ማኅበረሰብ ውስጥ ሙስሊሞች ከሌላው የሚለዩበት እውነታ ሆኖ እናገኘዋለን። ሙስሊም አገሮችን የሚጎበኙ ሰዎች ወይም የሙስሊም ቤተሰቦች የቅርብ ወዳጅ የሆነ ሰው አፍታም ሳይወስድበት ነገሮች በሚከናወኑበት ሁኔታ ረገድ የተለየ ነገር ያስተውላል።

በቀን ውስጥ የግዴታ ስግደቶች በሚከናወኑባቸው መደበኛዎቹ ፋታዎች፣ አልያም በኢስላማዊው የአለባበስ ሥርዓት ረገድ፣ ወይም ከሙስሊሙ ጋር አብሮ በሚገበዩበት ወቅት ሙስሊሙ እንግዳ የሆነ የምግብ ሽቀጥ ውስጣዊ ንጥረ ነገሮቹ ኢስላማዊ የምግብነት መስፈርቶች ማሟላት አለማሟላታቸውን ለማረጋገጥ እያገላበጠ ሲያይ ወዘተ. በመመልከት፣ ኢስላምን በተግባር የሚኖረው ሙስሊም ህይወት በተለየ ሁኔታ በዘርፈ ብዙ ህጎች፣ ደንቦችና ሥርዓቶች የሚገዛ መሆኑን ማስተዋል አይገደውም። የእነዚህ ህጎች፣ ደንቦች እና ሥርዓቶች አድማስ ዛሬ በተለምዶ ሃይማኖት ተብሎ ከሚተገበረውም እጅግ የራቀ እና የጠለቀ ነው።

እነዚህ መመሪያዎች ለሙስሊሞች የተግባራዊ እጅ መስጠት (የተገዢነት) ድልድዮች ናቸው። በቁርአን ውስጥ የተደነገገ ሆኖ ሳለ እጅግም ከብደት የለውም ወይም አላስፈላጊ ነው የሚባል አንዳችም ድርጊት የለም። ከዚህም በተጨማሪ፣ የኢስላም ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ.) ህይወት በጽሑፍ ከተላለፉባቸው ሐዲሶች የላቀ የተዓማኒነት ደረጃ አላቸው፣ ሙስሊሞች ተግባራታቸውን ለመመዘን የሚያስችል ቋሚ እና የቅርብ መለኪያ አላቸው። የትዳር አጋሬን በምን መልኩ ልንከባከብ ይገባኛል? ለሠራተኞቼ በምን መልኩ ነው የላባቸውን ዋጋ መክፈል ያለብኝ? ስግደቴን እንዴት ነው ማከናወን ያለብኝ? ራስን ለፈጣሪ ፈቃድ ማስገዛትን የሚጠይቅ ሃይማኖት እነዚህን ጥያቄዎች ያለ ምላሽ እንዲያው ሊተዋቸው አይችልም። ምንም እንኳ ከጥያቄዎቹ ውስጥ የመጨረሻው ብቻ ሃይማኖት በሚሰኘው ፈርጅ ውስጥ የሚወድቅ ቢመስልም፣ በኢስላም ግን በመንፈሳዊ እና በምድራዊው አካል መካከል የሚለይ አጥር የለም። በሌላ አነጋገር ማንኛውም ነገር ሃይማኖት ነው ማለት ይቻላል።

እንዲህም ስለተባለ የኢስላም ትምህርቶች በውጫዊ አካላት ላይ ብቻ የተወሰኑ ናቸው ማለት አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ታላላቆቹ ራስን ለፈጣሪ ፈቃድ የማስገዛት ተግባራት በአካል የሚፈፀሙ አይደሉም፣ በልብ እንጂ። ከሁሉም ተግባራት የሚቀድመው ዓይነተኛ የእምነት መገለጫ የአምላክን አንድነት በፅኑ እምነት የመሠከረ (የተቀበለ) እና የእርሱም ባርያ የሆነ ልብ ነው። በመጀመርያ ልብ ይህንን ካደረገ በኋላ ነው፣ የቀሪውን አካል ተግባራት በሚያሳልጥ መልኩ ሥራውን የሚቀጥለው።

የኢስካም አዕማድ

የሥርዓተ አምልኮው መልክዓ ምድር ጠፍጣፋ አይደለም። አንዳንድ የአምልኮ ተግባራት ከሌሎቹ ቀድመው መፈፀም ይኖርባቸዋል። ትኩረትን በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ለማድረግ የሚፈቅድ (የተግባራት) ተዋረድ አለ፤ እነዚህ መሠረታዊ ነገሮች ከተሟሉ በኋላ ደግሞ በአጠቃላይ የህይወት መስክ ራስን ለማበልፀግ በሩ ክፍት ነው።

አምስቱ የኢስላም መሠረቶች (አዕማድ)
1. ከአላህ በስተቀር ሊግዘት የሚገባው አምላክ የለም፤ ሙሐመድም መልዕክተኛው ናቸው ብሎ መመስከር።
2. በየቀኑ አምስት ጊዜ መስገድ
3. በረመዳን ወር ከንጋት እስከ ፀሐይ መጥለቂያ መፆም
4. የግዴታ ምፅዋት መስጠት
5. አቅም ከፈቀደ በሕይወት ዘመን አንድ ጊዜ ወደ መካ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ

እነዚህ አምስት የኢስላም አዕማድ እጅግ መሠረታዊ ናቸው፤ በእነዚህ አስፈላጊነት ላይ ቀኖናዊ በሆነ ደረጃ የፀና እምነት ማሳደር ከመከወኑ አስፈላጊነት እጅግ በላቀ ደረጃም አስፈላጊ ነው። አንድ ሙስሊም በተለያዩ ምክንያቶች ሶላት (ስግደት) ቢያመልጠው ይቅርታ ሊደረግለት ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን አንድ ሙስሊም የሶላትን አስፈላጊነት ከካደ ወይም ከካደች ሙስሊምነቱ/ቷ ግልፅ የሆነ አደጋ ውስጥ ይገባል። እነዚህ ተግባራት ዋጋ እንዲኖራቸው የሚያደርገውና ወደ አንድ የሚያስተባብራቸው ሁኔታ አዕማዱ በተደነገጉበት ዓላማ አኳያ የመፈፀም ቁርጥ ሐሳብ ("ኒያያ") ነው። ያለ ቁርጥ ሐሳብ ("ኒያያ") አንድ ሰው ሙሉ ቀን ከምግብና መጠጥ ታቅቦ ቢውል በቃ <<ምግብ አልበላም>> ይባልለታል።

በአንጻሩ ይኸው ተመሳሳይ ተግባር በቁርጠኛ ሐሳብ (በኒያያ) ታጅቦ ሲከናወን ከምግብ መታቀቡ ለመለኮታዊ ምንዳ ዕጩ የሚያደርግ ሃይማኖታዊ ፆም ይሆናል። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) የኒያያን ፋይዳ ሲያብራሩ፣ "ብዙ የሚፆሙ ሰዎች ከፆማቸው መራብን እና መጠማትን እንጂ ምንንም አያገኙም፤ በሌሊት የሚሰግዱ ብዙ ሰዎችም እንቅልፋቸውን ከማጣታቸው በቀር ምንም አያገኙም።"[17] ብለዋል [ተግባራቸውን ከቁርጥ ሐሳብ ጋር ባለማቀራኘታቸው ሳቢያ ማለት ነው]።

አምስቱ የኢስላም አዕማድ ሃይማኖቱን በተግባር የሚገልፅ ሙስሊም የግድ ሊከውናቸው የሚግቡትን አነስተኛ ተግባራት ያመላክታሉ። መላ ህይወታቸው የአምልኮ እና የመግዝዘት ታሪክ የሆነውን የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) ተግባራት በምሳሌነት በመውሰድ፣ ሙስሊሞች በፈቃደኝነት ሌሎች በርካታ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናሉ፡ እነዚህም ተጨማሪ ስግደቶች፣ ተጨማሪ ጾሞች፣ አዘውትሮ ቁርአንን መቅራት (ማንበብ)፣ የበጎ ፈቃደኝነት ምጽዋት (ሶደቃ) መስጠት የመሳሰሉት ናቸው።

አምልኮ አብሮነትን ይወዳል

ሁሉም የኢስላም መሠረቶች በግልጽ የሚታወቅ መንፈሳዊ ፋይዳ እንዳላቸው ሁሉ፣ ከፍተኛ ማኅበራዊ ፋይዳም አላቸው። በአምስቱ ዕለታዊ ስግደቶች ምዕመናን በቡድን እንዲሰግዱ፣ የቡድን ስግደታቸውንም በተቻለ መጠን በመስጂድ እንዲያከናውኑ የሚበረታቱ ሲሆን በዚያም ከሌሎች ምዕመናን ጋር ዘወትር በመገናኘት ከፍ ያለ የማኅበረሰብነት ስሜት ያዳብራሉ።

ኢስላማዊው የስግደት ሥርዓት ራሱን የቻለ አንድ ወጥ ቅርጽ አለው። በስግደቱ ላይ በውል የታወቁ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና በተለያዩ የስግደት አቋቋሞች ላይም የተለዩ ዕሎቶች አሉ። ወደየትኛውም የሙስሊም ዓለም ቢጓዙ ሙስሊሞች ትከሻ ለትከሻ ቆመው በህብረት አንድ ወጥ የአንቅስቃሴ ፈለግ በመከተል ሲፀልዩ ይስተዋላሉ። ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ እምነታቸው አተገባበር ረገድ የተለያዩ ደረጃዎች ሊኖራቸው፣ በፖለቲካ አስተሳሰባቸውም በጣም ሊለያዩ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ለአምላካቸው ጥሪ በጋራ ምላሽ በሚሰጡባቸው በእነዚያ ጥቂት (የስግደት) ደቂቃዎች ያ ሁሉ ተቃርኖ ይረሳና በተጣጣመ ሕብረ አምልኮ ይተካል። በረመዳን በየዕለቱ ከንጋት እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ያሉትን ሰአታት በጾም የሚያሳልፍ ሰው በረሃብ በሚመዘለግበት በእያንዳንዷ ቅጽበት ስለ ፈጣሪ ፀጋ ለማስታወስ ይገደዳል፤ ኋለም ከቤተሰቦቹ እና ወዳጅ ዘመዶቹ ጋር ጾሙን በሚፈስክበት ጊዜም ፈጣሪውን ይበልጥ አመስጋኝ ይሆናል፤ ከዚያ በላቀ ግን እንደ እርሱ ያልሞላላቸውን እነዚያን ምስኪኖች በርኅራኄ ያስታውሳል። በረመዳን ወር ግብፅ ውስጥ ከሚታዩ



■ በግብፅ ሙስሊሞች በረመዳን ወር ገላጣ ስፍራ ላይ የዕለት ጾማቸውን ሲፈስኩ ሙስሊም ያልሆኑ ጎብኝዎች አብረዋቸው ይታደማሉ።

እጅግ ማራኪ ትዕይንቶች አንዱ በገላጣ ሥፍራዎች በሚቀለሱ ባለ ህብረ ቀለም ድንኳኖች ሥር በተደረደሩ ጠረጴዛዎች ላይ የሚቀርቡት ዓይነተ ብዙ የግብዕ ጣፋጭ ምግቦች ብፌ ነው። እነዚህ "የእዝነት ገበታዎች" ሙሉ በሙሉ የሚዘጋጁት በተለይ በዚህ ወር የተራበ አንጀት ምግብ ሲያገኝ ስለሚሰማው ወደር የለሽ እፎይታ ጸመው እንዲያዩትና በዚህም አማካይነት ምስኪኖችን እንዲያስታዉሱ በተደረጉ ግለሰብ ዜጎች ወጪ ነው።

ዘካት ተብሎ የሚጠራው ዓመታዊ የግዴታ ምጽዋት ከተራ በጎ አድራጎት የሚለይ የራሱ ልዩ ባህርያት አሉት። ለይዩልኝ የሚፈፀም የልግስና ተግባር ከመሆን ይልቅ፣ "ማጥራት" ከሚለው ቃል ጋር ቀጥተኛ የስርወ ቃል ግንኙነት ያለው ዘካት ከአንድ ግለሰብ ሀብት ላይ 2.5 በመቶው የድሆች መብት (ሐቅ) መሆኑን ይደነግጋል። አንድ ሙስሊም ገንዘቡ (ሀብቱ) ሠርቶ የሚያገኘው መሆኑን ብቻ ሳይሆን ከዚሁ ሠርቶ ካገኘው ገንዘብ የተወሰነ ያህል የሌላ ሰው ድርሻ እንደሆነ ይገነዘባል። እንደ አይሁድ ጴዳካህ ሁሉ፣ ዘካትም በአምላክ የተደነገገ የግዴታ ምጽዋት እንጂ የበጎ አድራጎት ልግስና አይደለም።

በሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የስነ መንግሥት ትምህርት ተቋም (School of Government) የተደረገ አንድ ጥናት ሙስሊሞች በህይወት ዘመን አንዴ ወደ መካ የሚያደርጉት ሃይማኖታዊ ጉዞ ወይም ሐጅ "የብሔር ቡድኖች እና ኢስላማዊ የአስተሳሰብ ፈለግ ተከታዮች (sects) በእኩልነት እና በህብር ላይ ያላቸውን እምነት ከማጎልበት ባሻገር፣ የሴቶች ትምህርት እና የሥራ ተሳትፎ የበለጠ ተቀባይነት የሚያስገኝ፣ በአጠቃላይ ሴቶችን በተመለከተ ወደተሻለ አወንታዊ አስተሳሰብ የሚመራ ነው>> ብሎ ደምድሟል። እኒህ አዎንታዊ እሴቶች በሃይማኖቱ ተከታዮች ዙርያ ብቻ የታጠሩ አለመሆናቸውንም ጥናቱ አመልክቷል፣ <<በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ የአንድነት ስሜት መጎልበት ማለት ሙስሊም ላልሆኑ ሰዎች ጥላቻ ማሳደርን የሚያስከትል አይደለም...>>

አንድ ሙስሊም በህይወት ዘመኑ/ኗ ቢያንስ አንድ ጊዜ የኢስላም እና ኢስላም እንደሚያስተምረው የአብረሃማዊ ሃይማኖቶች የትውልድ ሥፍራ ወደሆነው መካ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህንን የሃይማኖት አምድ በውል መረዳት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ጉዞው፣ (የአገሩ) ሙቀት እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የማያውቋቸው ሰዎች ባሉበት ውስን ስፍራ በቅርበት መገኘት የሚፈጥረው ከፍተኛ የፍርኃት ስሜት ለዚህ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። እንዲያም ሆኖ ግን፣ ወደዚያ ሥፍራ የሄደ ሰው ሁሉ፣ ተሞክሮውን በጥልቅ ስሜት የሚያጣጥመው፣ በቃላት የማይገለፅ የህይወትን አቅጣጫ ቀያሪ ክስተት እንደሆነ ይናገራል።

ሃይማኖተኛ መሆን እና መልካም ሰው መሆን

መለኮታዊው ሕግ ተግባራትን በሚከተሉት ሁለት ፈርጆች ይከፍላቸዋል። ዒባዳት፣ የግል መንፈሳዊ አምልኮ (በአምስቱ አዕማድ ላይ ያተኮሩ) እና (ሙዓመላት)፦ ከሰዎች እና ከማኅበረሰብ ጋር በሚኖሩ ግንኙነቶች ላይ ያተኮሩ። ሁለተኛው ፈርጅ ከጋብቻ ህግጋት እስከ ንግድ ልውውጥ ድረስ ያሉ ማንኛቸውንም ነገሮች ያካትታል። ከመለኮት የተገለጠው ህግ የሚጠራበት ሸሪአ የተሰኘው የአረብኛ ቃል፣ ቃል በቃል ሲተረጎም ውሃ ወደሚገኝበት ሥፍራ የሚያደርስ ቀጥተኛ መንገድ የሚል መሆኑ አለነገር የሆነ አይደለም። የሸሪአ ሥረ መሠረት ነገሮችን በቀና መልኩ ለማከናወን የሚያስችል መንገድ አለ የሚል ሐሳብ ነው። በዋነኛነት በቁርአን እና በሱና ላይ የተመሠረተው ሸሪአ ሙስሊሞች ከፈጣሪያቸው ጋር ለሚያደርጉት ግንኙነትም ሆነ በዙርያቸው ካለው ዓለም ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ላይ ገዢ



ህይወትን በሚቀይረው የሐጅ ሥነ ሰርዓት ከዓለም ዙርያ የተሰባሰቡ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ተጓዦች ይገናኛሉ።

ነው። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ለሃይማኖቱ ተገዢ በመሆን ውጫዊ መገለጫዎች እና በሰዎች የእርስ በርስ መስተጋብር መካከል ባሉት ውስብስብ ግንኙነቶች ላይ በስፋት አስተምረዋል። <<ከእናንተ በላጮቹ ለቤተሰባቸው መልካምን የሚያደርጉት ናቸው።>>[18] ሲሉ ተናግረዋል። አንድ ሰው ቀኖችንና ሌሊቶችን በስግደትና በጾም እያሳለፈ ነገር ግን የቤተሰቦቹን/ቿን ፍላጎቶች እና ደስታ ከማሟላት ችላ የሚል ከሆነ ይህ ሰው የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) ውዴታ አያገኝም።

መለኮታዊውን ቃል ማንበብ በራሱ ምንዳ የሚያስገኝ ቢሆንም፣ በመላው የሰው ልጆች ምንጊዜም ተቀባይነት ያላቸውን መልካም ምግባራት መተግበር በተከበረው መጽሐፍ ላይ ያሉ ምንባቦችን በምላስ ብቻ ከማነብነብ በእጅጉ የበለጠ ምንዳን ያስገኛሉ። ዛሬ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መገለጫ ተደርገው እንዲታዩ የሚፈለጉት እና ዘወትር በምሽት ዜና ላይ የምናያቸው ሁከት አዘል ተግባራት በኢስላም በጥልቀት የተገሰፁ ተግባራት ናቸው። ለምሳሌ፣ ሙስሊሞች ቁጣ እጅግ መጥፎ ባህሪ እንደሆነ ተነግሯቸዋል። አንድ ጊዜ አንድ ሰው ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ዘንድ መጥቶ "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለህይወቴ የሚጠቅመኝን ምክር ይስጡኝ" አላቸው። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ.) "አትቆጣ" አሉት። ሰውየው ያሄንኑ ጥያቄውን ደጋግሞ አቀረበ። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ.) "አትቆጣ" የሚል ምላሻቸውን ሦስት ጊዜ ደጋገሙለት።[19] ይህንን አንድ ሐዲስ እና እሴቶቹን፣ ሐዲሱን መፈፀም

ሊያስቀር የሚችላቸውን እኩይ ነገሮች፣ ይህን ሐዲስ መተግበር ስንት በሐዘን የተኮማተሩ፣ በብስጭት የተሸበሸቡ ፊቶችን ፈታ ያደርጋቸው እንደነበር በመተንተን ላይ ያተኮሩ በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል።

ቁጣን የመቆጣጠር መልካም ትሩፋትን አላህም በቁርአን አወድሶታል፡ "... ለእነዚያም በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም [ቁጣንም] ገቺዎች፣ ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ጀነት ተደግሳለች)። አላህም በጎ ሰሪዎችን ይወዳል።" (3፡133) በተፈጥሮ ቁጡ የሆኑ ሰዎች ይህ አንቀጽ በተፈጥሯቸው ለቁጣ የማይጋበዙ ሰዎችን የሚያወድስ ከመሆን ይልቅ ለአላህ ሲሉ የተናነቃቸውን የቁጣ ስሜት አውጥቶ ከመግለፅ የሚቆጠቡትን የሚያወድስ ስለመሆኑ እንዲያስተውሉ ይማራሉ።

በአጠቃላይ ሃይማኖት በእኩይ የሕዝብ ግንኙነት ዘመቻ ሳቢያ ለአደጋ የተዳረገ ሲኾን፣ ሙስሊሙ ማኅበረሰብም የዚህ እኩይ ዘመቻ ሰለባ ከመሆን አላመለጠም። ውጫዊ መገለጫ ያላቸው ሃይማኖታዊ ተግባራት የሚፈጽሙትን ያልተገሩ፣ መጥፎ እና ክፋዎች አድርጎ የማሰብ፤ በሌላ በኩል ሃይማኖታዊ ሕግጋትን ቸል የሚሉትን ደግሞ ነፃ መንፈስ ያላቸው "ልበ መልካሞች" አድርጎ ለመረዳት ይዳዳናል።

በሐዲስ፡- አላህ ከኃጢአቶቿ ምህረት ስላደረገላት አንዲት ዝሙተኛ ተነግሮናል። ዝሙተኛይቱ የአላህን ምህረት የማግኘቷ ምክንያት ከአንድ የውሃ ጉድጓድ አቅራቢያ በሚያለከልክ ውሻ አጠገብ ስታልፍ፣ ውሻው በውሃ ጥማት ሞት አፋፍ ላይ መሆኑን በመረዳቷ ጫማዋን አውልቃ በፀጉሯ ሻሽ በማሰር ከጉድጓዱ ውስጥ ውሃ አውጥታ ውሻውን በማጠጣቷ ነበር። ለሚያስተውል ሙስሊም፣ እነዚህ ትርክቶች በመለኮታዊ የፍርድ ሚዛን ደግነት እና አዛኝነት ምን ያህል ክብደት እንዳላቸው፣ ውጫዊ የተገዢነት መግለጫዎችና ገታራ ‹‹የይዩልኝ ተግባራት›› እውነተኛ የአምላክ ተገዢነትን እንደማያመለክቱ ያስታውሳሉ፤ ያስጠነቅቃሉም። እነዚያን ከራሳቸው ድርጊት በቀር የሌላ የማንም ድርጊት የማይዋጥላቸውን፣ በዙርያቸው ያሉትን ሁሉ ከማቅረብ ይልቅ በሚገፋ መልኩ የሚተቹትን፣ የሰዎችን ድርጊቶች በተኮማተረ ገፅታ እያንጓጠጡ የሚያብጠለጥሉትን ቁርአን እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃቸዋል፡ "‹‹በሥራዎች በጣም ከሳሪዎቹን እንንገራችሁን›› በላቸው። እነዚያ እነርሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ፣ በቅርቢቱ ሕይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው።" (18: 103 104)

የተከለከሉት የግጦሽ መስኮች

ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) "ያ እርሱ ሐላል (የተፈቀደ) የሆነው ግልፅ ነው፤ ያም እርሱ ሐራም (ክልክል) የሆነው ግልፅ ነው። በሁለቱ መካከል የተፈቀዱ ይሁኑ የተከለከሉት፣ ሰዎች የማያውቋቸው ብዥታ የሚፈጥሩ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ አጠራጣሪ ነገሮች የራቀ፣ እርሱ ሃይማኖቱን በማጥራት ራሱንም ያድናል። እነዚያን (አጠራጣሪ) ነገሮች የቀረበ፣ እርሱ ወደ ክልክሉ (ሐራም ወደሆነው) ተጠግቷል። ምሳሌውም፣ መንጋዎቹን በተከለለ የግጦሽ መስክ አቅራቢያ እንዳሰማራ እረኛ ነው፤ መንጋዎቹ ፈጥነው በሚገቡበት የተከለለ መስክ። ... ንቁ! የአላህም ክልል እርሱ ሐራም ያደረጋቸው ነገሮች ናቸው።... ንቁ! በአካላችን ውስጥ አንዲት ሙዳ ስጋ አለች፤ እርሷ ከቀናች (ከተስተካከለች) መላው አካል የቀና ይሆናል፤ እርሷ ስትጠም መላው አካልም ይጠምማል። ንቁ! ይህች ሙዳ ስጋ ልብ ናት።"[20]

ማንኛውም ሃይማኖት ህግጋት እና ደንቦች አሉት። በዚህ ረገድ ኢስላም ከሌላው የተለየ አይደለም። ኢስላምን ለየት የሚያደርገው ነገር ህግጋቱ (ድንጋጌዎቹ) ለክፍለ ዘመናት ወጥነታቸውን እንደጠበቁ



■ ሸሪአ የሚለው የመለኮታዊው ሕግ የአረብኛ ቃል፣ ጥሬ ትርጉም ወደ ውሃ ምንጭ የሚያደርስ ቀጥ ያለ መንገድ ማለት ነው። /ገፅ 49/

> <<ከመጠጥ መታቀብ በጣም ቀላል ነው፤ አለመጠጣት የሚከብደውን ያህል።"
>
> ሳሙኤል ጆንሰተን

መዝለቃቸው ነው። ምንም እንኳ ግግር (stagnant) ባይሆንም (ቢያንስ በመርጎ ደረጃ)፣ ኢስላማዊው ሕግ ያጋጠሙትን የተለያዩ ተግዳሮቶች ተቋቁሞ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተጠብቆ ኖሯል። በግለሰብ ደረጃ፣ አንድ ሙስሊም ሃይማኖቱን/ቷን ሳይዛባ ጠብቆ በማቆየት ረገድ፣ ለማመን የሚያዳግቱ ፈተናዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህንን የሕጉን ባህሪ በአርአያነት ይወስዳሉ። እምነታቸውን በተግባር የሚገልፁ ሙስሊሞች በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ያሉ ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው ሰዎች እንደሚያጋጥማቸው ከክብራቸው ምኩራብ ወደታች ሲፈጠፈጡ እምብዛም የማይታየው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሐዲስ ምክንያት ነው።

ምስላዊ ወግ

አምልኮ፥
ስግደት፣ ፀሎት (ዱዓ) እና ሶደቃ

አምልኮ በእስልምና ሀይማኖት ተገልፆ የማያልቅ መልኮች አሉት። ከቶውንም በሃይማኖታዊ ከንዋኔዎች እና ስግደቶች የተገደበ አይደለም። በትክክለኛ እና ልባዊ ሐሳብ እስከተካሄደ ድረስ ማንኛውም ተግባር አምልኮ ሊሆን ይችላል። ምጽዋት መስጠት፣ ማስተማር፣ በማኅበራዊ ተግባራት መሳተፍ፣ ረዳት ያጡትን መደገፍ፣ እንዲሁም ሥነ ጥበብን ለህዝብ በሚጠቅም መልኩ መጠቀም እነዚህ ሁሉ የአምልኮ መልኮች ሊሆኑ ይችላሉ።





■ ኢስታንቡል፣ ቱርክ፣ ውስጥ በሚገኘው ፋቲህ መስጂድ ሙስሊሞች በስግደት ላይ



■ ሙስሊሞች አዳዲስ እና በመጠኑ የተለበሱ ኮቶችን ለክረምት የበጎ አድራጎት ዘመቻ ላይ ሲለግሱ

ኢ.ሙ.አ.ኔ፡- ኢነርሲቲ ሙስኪም አክሽን ኔትወርክ

የሙሉ ሰዓት አስተዳደር ሰራተኛ፣ የበጎ ፈቃድ ሃኪሞችና እና ተንቀሳቃሽ የህክምና ተማሪዎችን ያካተተው አዲሱ "ሄልዝ ክሊኒክ" የተለያየ የኢኮኖሚ፣ የጎሳና የሃይማኖት መሰረት ላላቸው የቺካጎ ነዋሪዎች መሰረታዊ የጤና እንክብካቤና የትምህርት አገልግሎት በነጻ ይሰጣል። ክሊኒኩን በወር ከሁለት መቶ በላይ በሽተኞች የደም ብዛትና የኮሌስትሮል መጠን ለመለካት፣ ዐመታዊ የጤና ምርመራ ለማድረግና ድንገተኛ ያልሆኑ የጤና ምርመራዎችን ለማድረግ ይንበኙታል።

በኢ.ሙ.አ.ኔ ስራ ፈጠራ ተቋም የሚንቀሳቀሰው "ዘ ካሪር ሴንተር" የተሰኘው ማዕከል የአምስት ሳምንት መሰረታዊ የኮምፒውተር ዕውቀትና የስራ ፈጠራ እገዛ ለቺካጎ ላውን ማህበረሰብ ይሰጣል። በመሰረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና ፕሮግራም የተመዘገቡ ተሳታፊዎች ጽሁፍ ከመጻፊያና የተመን ሉህ ፕሮግራሞች ጀምሮ በኢንተርኔት ስራ እስከ መፈለግ ድረስ ይማራሉ። በተጨማሪም የልምድ ማስረጃ አጻጻፍ፣ ስራ ጥየቃና የቃለ መጠይቅ ክህሎቶች ላይ ስልጠና ይሰጣል። ተሳታፊዎች ስልጠናውን በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ በኢ.ሙ.አ.ኔ ስራ ፈጠራ ተቋም እውቅና የሚሰጣቸው ሲሆን ስራ ለመቀጠር ወይም ተጨማሪ የትምህርት እገዛ ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ። ትምህርት በሳምንት ሰባት ቀን በእንግሊዝኛና በስፓኒሽ ቋንቋዎች ይሰጣል።







ክፍል ሁለት

የኢስላም ገቢራዊ መልክ



ምዕራፍ አምስት

ሀያው ምሳሌ

የአንድ ሃይማኖታዊ ማኅበረሰብ እውነተኛ መለኪያው የደንቦቹ እና በመለኮታዊ ትዕዛዝ በተቀረፀው ሥርዓት ውስጥ ያለው የአኗኗር ዘዬ ወጥነት ነው ከተባለ፣ እውነተኛው የኢስላም ወርቃማ ዘመን አቻ ባልተገኘላቸው የአብያተ መንግሥት ህንጻዎቿና በመልከዓ ምድሯ የምትታወቀው የስፔኗ አንዳሉስ አልነበረችም። የዘመነ ባቢሎን ግርማ ሞገስን በተላበሱ ቤተ መንግሥቶቹ የሚታወቀው የሐሩን አል ረሺድ ዘመንም አይደለም። የሙስሊሙ ዓለም የሥልጣኔ ግኝቶች ጎልተው ከታዩባቸው ዘመናት አንዱም አይደለም። እውነተኛው የኢስላም ወርቃማ ዘመን የሙስሊሞች ቁጥር ከጥቂት የአማኞች ቡድን አያበልጥ በነበረበት፣ በታሪክ መዝገብ ላይ ከህዳግ ማስታወሻ የዘለለ ስፍራ ላያሰጠው ይችል የነበረው እ.አ.አ. ከ622 እስከ 632 ዓ.ል ያለው የአሥር ዓመታት ጊዜ ነው።

የአምሳያ የከሸ ማኅበረሰብ ዘሮች

በመካ ጣዖት አምላኪዎች ከሚደርስባቸው የዕለት ከዕለት የግፍ ሥቃይ ነፃ ከሆኑ በኋላ፣ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ከየስሪብ (በኋላ መዲና ተብላ የተሰየመች የነቢዩ ከተማ) ነዋሪዎች ጋር በተጋቡት ቃል ኪዳን ላይ በመመሥረት የወደር የለሹን ሃይማኖታዊ ማኅበረሰብ ዘሮች ተክሉ። የዛሬ ዘመን ሙስሊሞች መቼም ቢሆን የዚያ ማኅበረሰብ አምሳያ ዳግመኛ እንደማይፈጠር በእርግጠኝነት ይገነዘባሉ። ከዚህም ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ በመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ.) አማካይነት ከአምላክ ጋር የቀጥተኛ ግንኙነት የነበረው ትውልድ መሆኑ ነው። እንዲያም ሆኖ ግን፣ ልክ ግለሰብ ሙስሊሞች ለላቀ ስብዕና ሞዴል (template) ሲሹ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) አቻ የለሽ ምሳሌነት እንደሚማትሩ፣ የአማኞች ማኅበረሰቦችም ምዕመናን ምን ደረጃ ላይ ሊደርሱ እንደሚችሉ መመሪያ ይሆኗቸው ዘንድ ወደ እነዚያ ዓመታት ይማትራሉ።

በዋጋ ሊተመን የማይችል፣ እጅግ ጥልቅ የሆነው እና የትክክለኝነት ደረጃ የማረጋገጥ አስገራሚ ሳይንስ ለመባል የበቃው የሐዲስ ዘገባ ጥበብ ለሙስሊሞች ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) እና ባልደረቦቻቸው እንደት ይኖሩ፣ እንደት የእምልኮ ተግባራትን ይፈፅሙ፣ እንደት የዕለት ከዕለት ሥራዎችን ይሠሩ፣ እንደት ያፈቅሩ እንደነበር፣ እንዲሁም እንደት እንደሞቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰጣል። ለብዙዎች የብሉይ ኪዳን ነቢያት እጅግም ከተረት መጽሐፍ ገፀ ባህሪያት ተለይተው አለመታየት ደረጃ ላይ

■ ሙስሊሞች የጁሙዓ የህብረት ሶላትን መዲና በሚገኘው የነቢዩ መስጂድ ከአለት ምሰሶዎች እና ቅስቶች ስር ሲሰግዱ

ቢደርሱም፣ በአንዳሩ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ከአንድ ሺህ የበለጡ ዓመታት በኋላ፣ ዛሬም ድረስ ህያው ምሳሌ መሆናቸውን ቀጥለዋል።

ከመካ ወደ መዲና የተደረገው ይህ ስደት በኢስላም እና በዓለምም ታሪክ እጅግ ቁልፍ ምዕራፍ ነው። የአገር መሪነትን ሚና ለመረከብ የተገደዱት ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ከዚህ በኋላ መንፈሳዊ ብቻ ህይወት እና ተልዕኮ ይዘው የመቀጠል ድሎቱ አልነበራቸውም።
እንዲያም ሆኖ፣ የማኅበረሰቡ የማይናወጥ ትኩረት አምላክን በማወቅ ላይ የተማከለ ህብረተሰብ በመገንባት ላይ ያረፈ ነበር። ገና መዲና ከመድረሳቸው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) እና ባልደረቦቻቸው የመዲና መስጂድን ማነጽ ጀመሩ።

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) እንደ ሚዕከል

ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ቤተሰብ ትናንሽ የመኖሪያ ክፍሎች ጋር ተያይዞ የተሠራው የመዲና መስጂድ የህብረት ሶላት የሚከናወንበት ቦታ ብቻ ሳይሆን የከተማው የህዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽም ጭምር ነበር። በዚህ ሥፍራ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) የእርሳቸውን ምክር ወይም አመራር ከሚፈልገው ማኅበረሰባቸው አባላት ጋር ይገናኛሉ። መስጂድ መጥተው ሊያነጋግሯቸው ያልቻሉ ሰዎች ካሉ የእነርሱን ችግሮች ጠይቀው መልዕክታቸውን እንዲያመጡላቸው በመስጂዱ የተገኙትን ይጠይቃሉ።

በዚሁ ሥፍራ ሁለት የተጋጩ ወገኖችን ሽምግልዋል፤ ይህንን ሲያደርጉ ግን ከመለኮታዊው ፍርድ በተለየ ሁኔታ የሚፈርዱት በሚቀርቡላቸው ማስረጃዎች ላይ ብቻ ተመሥርተው እንደሆነ ተቃራኒ ወገኖቹን አስጠንቅቀዋል። ስለ መዲና የተዘገበባቸው ሰነዶች በመስጂዱ አዳራሽ ውስጥም ሆነ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላኛው ቤት ቁርአን የሚያነብቡ ሰዎች የማያቋርጥ ድምጽ ይሰማ እንደነበር ይገልጻሉ። ከእርሳቸው በፊት የነበሩ ነቢያትን ፈለግ በመከተል ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) መስጂዱንም ሆነ የመኖሪያ ቤታቸውን መዋቅር ንድፍ በጣም ቀላል እንዲሆን አድርገው ነበር፤ የመኖሪያ ክፍላቸው ጣሪያ በጣም ዝቅ ያለ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው ቀጥ ብሎ በሚቆምበት ጊዜ የራስ ቅሉን ይነካው ነበር።

ከመካ ተሰድደው የመጡት ሙስሊሞች ታየሁ አልታየሁ በሚል እየተሸማቀቁና እየተሰቃዩ ይኖሩ ከነበረበት ሁኔታ ወጥተው ከአስተማሪዎቻቸው መልካም መስተንግዶ ጋር ሰላም በሰፈነበት አዲሱ መኖሪያ አገራቸው ራሳቸውን አገኙ። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በመዲና ካከናወኗቸው ተቀዳሚ አስተዳደራዊ ተግባራት መካከል በመካ ስደተኞች (ሙሐጂሮች) እና በመዲና አስተናጋጆቻቸው (አንሷሮች) መካከል የመሠረቱት የወንድማማችነት ቃል ኪዳን ይገኝበታል። እያንዳንዱ የመዲና ነዋሪ ከመካ ተፈናቅሎ የመጣው አዲስ የቤተሰቡ አባል የሚፈልጋቸውን ማናቸውንም የቁሳቁስ ድጋፎች ለመስጠት ቃል ኪዳን ገባ። በአፀፋውም፣ ቀደምቶቹ የመካ ሙስሊሞች ለአስተናጋጆቻቸው ታማኝ ለመሆን ቃል በመግባት በአጭር ጊዜ ኢስላማዊ ሰብዕናን አላበሷቸው።

ግለኝነት በገነነበት የዛሬው የእኛ ማኅበረሰብ የዚህ ድንቅ እሴት ታላቅነት ብዙም አይስተዋልም፤ ነገር ግን፣ ይህ ቤተሰባዊ ቃል ኪዳን በቅድመ ኢንዱስትሪ ዘመን፣ ያውም በጎሳ ላይ በተመሠረተ ማኅበረሰብ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉና በታማኝነትም መፈፀሙ ከተዓምር የሚቆጠር ነው። አላህ በቁርአን፣ "ጠበቆችም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ፀጋ አስታውሱ። በልቦቻችሁም መካከል አስማማ። በፀጋውም ወንድማማቾች ሆናችሁ፤" (3:103)



መዲና የሚገኘውን የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) መስጂድ የሚያሳይ ስዕል፣ እ.አ.አ. በ1854 ገደማ የተሳለ።

ይላል። ከዚህ ቃል ኪዳን በኋላ ብዙም ሳይቆይ፣ ሌላ አስደናቂ ሊባል የሚችል ሕግ ተደነገገ። በአውስ እና በኸዝረጅ ጎሳዎች፣ እንዲሁም በዚያ ይኖሩ በነበሩ የተለያዩ የአይሁድ ጎሳዎች መካከል ሰላም ይፈጥሩ ዘንድ ወደ መዲና እንዲመጡ የተጋበዙ መሆናቸውን ባለመዘንጋት፣ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ዛሬ ‹‹የመዲና ቻርተር›› በመባል የሚታወቀውን ሰነድ ነደፉ። ቻርተሩ በማያሻማ መልኩ የመጀመርያውን ሙስሊም አገር ከመመስረቱም ባሻገር፣ ሌሎች ነገሮችን ጨምሮ፣ ማኅበረሰብ (ዑማህ) የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ኢስላማዊ ድንጋጌ በግልፅ አስቀመጠ። ይህ ቃል ዛሬ ሙስሊሞች የሃይማኖቱን ተከታዮች በድምር ለመግለጽ በብቸኝነት የሚጠቀሙበት ቃል ሲሆን፣ የመዲናው ቻርተር የነቢዩን ዑማ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች የማይገሰሱ መብቶች በስፋትና በእጅጉ አካታች በሆነ መልኩ በዝርዝር የደነገገ ነበር። ከእነዚህም መብቶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፦

1. በቻርተሩ የታቀፉ ቡድኖች ሁሉ ሙስሊሞችም ሙስሊም ያልሆኑትም የደኅንነት ቃል ኪዳን /ዚማ/ ዋስትና አላቸው።
2. ሙስሊም ያልሆኑ የዑማው አባላት ከሙስሊሞቹ እኩል የሆነ የፖለቲካ እና የባህል መብቶች አሏቸው።
3. ሙስሊም ያልሆኑ የማኅበረሰቡ አባላት የሃይማኖት ሉዓላዊነት እና ነፃነት አላቸው።
4. የመዲና ግዛት ጥቃት ከተሰነዘረበት፣ ሙስሊም ያልሆኑ አባላትም እርሷን በመከላከል ይሳተፋሉ የጦርነቱን ወጪም ይጋራሉ።

ምንም እንኳ ሙስሊሞች መካ ውስጥ ከነበራቸው የላቀ ደኅንነት መዲና ውስጥ ቢያገኙም፣ አዚህም ሆነው ግን የጦርነት ነጋሪት ከሩቁ ሲንሰም ይሰማቸው ነበር። ማንም ሊረዳ እንደሚችለው፣ መካውያን ከመካ አምልጦ የሄደው ቡድን እያስመዘገበ ያለው ስነ ዜጋዊ ስኬት እጅግ አብሣኂቸው ነበር። የነገደ ቁረይሽ ጎሳዎችም ወደ አጎራባች ከተሞች ለማለፍ የንግድ መስመራቸውን በመቀየር በመዲና ዙርያ ያሉ ሌሎች የአረብ ነገዶች በሙስሊሞቹ ላይ እንዲነሱባቸው መቀስቀስ ጀምረው ነበር። የመካውያኑ ፍላጎት ግልጽ ቢሆንም፣ በአንፃሩ የመዋጋት ፈቃድ ድንጋጌ ከአላህ ባለመወረዱ የሙስሊሞቹ እጆች እንደታቀቡ ነበሩ። ለዓመታት፣ ለሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ይወረዱ የነበሩት ቁርአናዊ አንቀጾች መከራን ቻይነት እና ትዕግስተኝነትን የሚመክሩ ነበሩ። ‹‹አላህም ትዕዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ይቅርታ አድርጉ፤ አለፏቸውም።›› (2:109)[21]



■ የሐጅ ሥርአት ፊዎሚዎች ነቢዩ የመጨረሻ ንግግራቸውን ባሰሙበት የአረፋት ተራራ ላይ ተሰብስበው

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ የሚከተለው ነው። እንደ ኢስላም መሠረታዊ መርኅ ከሆነ ሁከት /ነውጥ/ የሚፈቀድ ነገር አይደለም። የሰው ልጅ ከጥንተ መሠረታዊ ተፈጥሮው ሰላማዊ ነው፥ ፥ነገር ግን በታሪክ ሂደት እንደታየው ለሁከት የተሰጠው አፀፋ ተጨማሪ ሁከት ሆኗል። ለአሥርት ዓመታት ሊዘልቁ የሚችሉ ደም አፋሳሽ ግጭቶች በሚፈጠሩባቸው ጊዜያት፣ ቤተሰቦቻቸው እና ወዳጆቻቸው እየተሰቃዩ፣ እየተሰደዱ እና እየተገደሉም እንኳ ሙስሊሞች በተደጋጋሚ ትዕግስት እና ቻል አድርጎ ማለፍን በተግባር አሳይተዋል። በመጨረሻም፣ ከአሥራ ሦስት ዓመታት በኋላ፣ ለአጥቂዎች አፀፋ የመስጠት (ጥቃትን የመመከት) ፈቃድ ተሰጠ። ይህም ፈቃድ ግን ጥብቅ በሆኑ ስነ ምግባራት እና ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች ተለያተው የተዘረዘሩ ነበሩ። የፍትኃዊ ጦርነት ሕግጋት እና የጦርነት ውስጥ ፍትኃዊነት ከዚያ ቀደም ባለው የሰው ልጅ ታሪክ እንደዚያ በጥብቅ ተደንግጎ አያውቅም።

የበድር ጦርነት እና ከዚያ በኋላ፡ ከ624 እስከ 632 (ዓ.ል.)

<<አላህ ሆይ፣ ይህ የሙስሊም ቡድን ዛሬ የሚጠፋ ከሆነ፣ በምድሪቱ የሚያመልክህ አይኖርም።>>[22]

ወራሪ ሠራዊቱን እስከ መዲና ዳርቻ በመላክ ድንገተኛ ጥቃት በመክፈት፣ የሙስሊሞችን የፍራፍሬ ዛፎች ካወደመ እና የቁም እንስሳቶቻቸውን ከዘረፈ በኋላ፣ በአንድ ሺህ ሰዎች፣ በሰባት መቶ ግመሎች እና በአንድ መቶ ፈረሶች የተደራጀው የመካውያን ሠራዊት በ624 (ዓ.ል) የመፀው ወራት ወደ መዲና ተቃረበ። የዚህን ጦርነት እጅግ መጠነ ሰፊ አንድምታ ያለው ውጤት አስቀድሞ ለመተንበይ ለሰብአዊ ፍጡር በጭራሽ የሚቻል አልነበረም። የታሪክን አቅጣጫ በቀየረ መልኩ በምድር ላይ ያሉ አገራትን በሙሉ የነካ ተጽዕኖ ያሳደሩ ጦርነቶች ኢምንት ናቸው። ምንም እንኳ ለአንድ ተጋዳይ ከሦስት በላይ ሙሽሪኮች በሚደርሱት መጠን በቁጥር እጅግ ቢበለጡም፣ ሙስሊሞች በዚህ የጽናታቸው የመጀመሪያ መፈተኛ በሆነው በዚህ ጦርነት ላይ ድል ተጎናጽፈዋል።

ምንም እንኳ መካውያን ቀጣዩን ጦርነት ማሸነፍ እና ነቢዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ.) ማቁሰል ቢችሉም፣ በበድር ጦርነት ላይ ከደረሰባቸው አስደናቂ ምት ፈፅሞ ሊያገግሙ አልቻሉም። ወደ መዲና ከተሰደዱ ከስምንት ዓመታት በኋላ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) እና ባልደረቦቻቸው ወደ መካ ተመለሱ። ከትውልድ ቀዬአቸው በከባድ ስቃይ እና ችግር ቢሰደዱም፣ በድል አድራጊነት ተመልሰውባታል።

አዎ፣ ሙስሊሞች ለብዙ ዓመታት እንዳይረግጧት ታግደው ወደተለይዋት የአያት ቅድመ አያቶቻቸው ምድር በድል ተመልሰው ገቡ። ነገር ግን፣ ከድል አድራጊነት ሆታና ጭፈራ ይልቅ በፍፁም የመተናነስ ስሜት ነበር ወደ መካ የዘለቁት።

በግመል ላይ ሆነው ወደ መካ በሚገቡበት ወቅት ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) አንገታቸውን እጅግ በጣም ከማቀርቀራቸው የተነሳ ጺማቸው የግመላቸውን ኮርቻ ለመንካት በጣም ቀርቦ ነበር ሲሉ የዜና መዋዕል ፀሐፍት ገልፀዋል። ካዕባ እንደደረሱ የመካ ዜጎች ከፊታቸው በተሰበሰቡበት፣ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.)<<ቁረይሾች ሆይ፣ ከእኔ እንዴት ያለ አያያዝ ትሻላችሁ?>> በማለት ጠየቋቸው። እነርሱም፣ <<የአላህ መልዕክተኛ ሆይ፣ ምህረት ነው የምንፈልገው። ከእርስዎ መልካምን ነገር እንጂ ሌላን አንጠብቅም፤>> ሲሉ መለሱላቸው። በዚህም ጊዜ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.)፣ <<ዩሱፍ (ዮሴፍ) ለወንድሞቹ የተናገራቸውን ቃላት እነሆ ዛሬ እኔ ለእናንተ እናገራለሁ፥ <<በዚህች ቀን በእናንተ ላይ ምንም ወቀሳ የለባችሁም፥ ወደየፈለጋችሁበት ሂዱ፣ እናንተ ነፃ ናችሁና።>> ከዚህችኛዋ ቅፅበት በፊት

እስከነበሩት ደቂቃዎች ድረስ የጠላትነት ስሜታቸውን አምቀው ይዘው የቆዩት ሰዎች ምህረት የማግኘት ተስፋቸው ከመለምለሙም ጋር ምንም ዓይነት በቀል አለመኖሩን ለማመን በመቸገር በየተራ ወደ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) መጡ።

ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ቀሪዎቹን ጥቂት ዓመታት መላውን የአረቢያ ምድር በኢስላም ጥላ ስር አንድ በማድረግ አሳለፉት፤ ለእርሳቸው የታማኝነት ቃል ኪዳን ለመግባት በርካታ ነገዶች ወደ መዲና ተመሙ። በ632 ዓ.ል. ነቢዩ ባልደረቦቻቸውን በማስከተል መካ ወደሚገኘው ካዕባ የመጀመርያቸው የሆነውን የሐጅ ጉዞ አደረጉ። የሐጅ ስነ ሥርዓትን ከፈፀሙ በኋላ፣ መለኮታዊው ራዕይ መወረድ ከጀመረባቸው ጊዜያት አንስቶ ከአጠገባቸው ያልተለዩትን ጨምሮ ተከታዮቻቸውን በሙሉ ሰበሰቧቸው። ቁጥራቸው አንድ መቶ ሺህ ከሚሆኑ አማኞች ፊት በመቆምም፣ እጅግ ዝነኛ የመሰናበቻ ንግግራቸውን አደረጉ።

ንግግራቸውን እንዳጠናቀቁ፣ ወደላይ ቀና በማለት እንዲህ ሲሉ ጌታቸውን ተማፀኑ፥- <<አላህ ሆይ! መልዕክትህን አድርሻለሁን?>> ከዚያም፣ <<ከእኔ በኋላ ከእምነታችሁ ተመልሳችሁ፣ እርስ በእርሳችሁ አንገት የምትቀላሉ ከሃዲያን እንዳትሆኑ።>>[24]

ከዚህ በኋላ የወረደው የቁርአን አንቀጽ በዚያን ጊዜ የነበሩት አይሁዶች <<ዛሬ እጅግ ልትደሰቱ ይገባል>> በማለት ለሙስሊሞች የተናገሩለት አንቀፅ ነበር።(ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለእናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በእናንተ ላይ ፈፀምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።) (5:3)ነገር ግን ይህንን አንቀጽ እንደሰሙ፣ ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች በጣም ኃይለኛ የሆኑት ዑመር (ረ.ዐ) ተንሰቅስቀው ሲያለቅሱ ተገኙ። በዙርያቸው የነበሩት ሰሀቦች ግራ ተጋብተው፣ "ምን ሆነሃል፣ ምን አገኘህ?" በማለት ጠየቋቸው።

"ከፍጽምና በኋላ፣" አሉ ዑመር፣ "ከፍጽምና በኋላ ሐዘን ብቻ እንጂ ምንም የለም።" ከወራት በኋላ፣ ታላቁ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ.) በባለቤታቸው በአዒሻ (ረ.ዐ) እጅ ላይ እንዳሉ ህይወታቸው አለፈች።


الله جل جلاله
أبو بكر الصديق رضي الله عنه

ተተኪዎች እና ቁሳሮች
ኢስካም ከነቢዩ በኋላ

በአሁኑ ዘመን የሚኖሩ ሙስሊሞች ቀደምት ታሪካቸውን በሚገባ ይገነዘባሉ። በዚህም የተነሳ ነው ከእነርሱ ውስጥ የተወሰኑት አሁን ለሚታየው ዓለማዊ ግርግርና መሯሯጥ ብዙም ትኩረት የማይሰጡትና ግዴለሽ ሆነው የሚታዩት። ሙስሊሞች የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አባባሎች ሲናገሩም ሆነ የቀደምት ደጋግ አባቶችን ታሪክ ሲያወሱ በእነርሱ ጊዜ እንደተፈጸሙ አድርገው ማሰባቸውና ራሳቸውን የታሪኩ አካል አድርገው የሚቆጥሩ መሆናቸውም እውነት ነው። ሌላው ሙስሊሞች ታሪክን የሚመለከቱበትን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው ታሪካቸው ሁልጊዜም የዕድገት፣ የብልጽግናና የሰላም ብቻ ነበር ብለው አለማሰባቸው ነው። ምክንያቱም ምንም እንኳን በዓለም ላይ ታላቅ የሆነን ስልጣኔ መሥርተውና በዚያም የፍካት ዘመን ቢያሳልፉም ይህ ብቻውን የሰው ልጅ ታሪክ የሚገመገምበት ወይም የፍርድ ሚዛን ላይ የሚቀመጥበት ብቸኛ መስፈርት ነው ብለው ስለማያምኑ ነው። ሙስሊሞች ያለፈውን ታሪካቸውን በተደጋጋሚ እያነሱ መቆዘማቸውና ያንን ዘመን መናፈቃቸው ለተለያዩ ትችቶች እየዳረጋቸው ይገኛል። ይሁን እንጂ ያ ዘመን የሰው ልጅ በመንፈሳዊውም ሆነ በቁሳዊው ዓለም ታላቅ እመርታ ያሳየበት እንደመሆኑ ከቶም በኋላ ቀርነት ሊፈረጅ እንደማይችል ሁሉም የማይስተው ሐቅ ነው። እናም ያንን ወርቃማ ዘመን ወደኋላ ዞረው እያማተሩ መኖራቸው ሊያስወቅሳቸው አይገባም። ምነው ቢባል የታላቅ ስልጣኔ፣ ሳይንሳዊ እመርታና ከሁሉም በላይ የሥነ-ምግባር የበላይነትን ይዘው የቆዩበት ማለፊያ ጊዜ ስለነበር ነው።

በአራቱ በትክክል የተመሩ ኸሊፋዎች ጥላ ስር

በተደጋጋሚ ሲሆን እንደሚስተዋለው ኢስላማዊውን ታሪክ በሁለት ምዕራፎች ከፍሎ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው በትክክል የተመሩ ኸሊፋዎች (ኹለፋእ አር-ራሺዲን) ያስተዳደሩበት ምዕራፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከእነርሱ በኋላ የተከሰተውና በአብዛኛው በንቅዘት የተሞላው ንጉሳውያንና ሱልጣኖች የገዙበት ምዕራፍ ነው። አራቱ ኸሊፋዎች የታላቁ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) የቅርብ ወዳጆችና ባልደረቦች የነበሩ ሲሆን ከአላህና ከመምህራቸው የወረዱላቸውን ኢስላማዊ ሕግጋትና ደንቦችን ሙሉ በሙሉ የመተግበር የማይናወጽ አቋም ነበራቸው። በድምሩ በአመራር ላይ የቆዩት ሰላሳ ለሚሆኑ ዓመታት ብቻ ነው። ልክ እንደ ነቢያቸው (ሶ.ዐ.ወ) ሁሉ የእነዚህ አራት ሰዎች ሕይወት በታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት የታጀበና ማራኪ ነበር። የመጨረሻው በትክክል የተመሩ ኸሊፋ ዐሊይ (ረ.ዐ) ከሞቱ በኋላ ግን በኡ

ኡመያዎች (Umayyad Dynasty) ሙስሊሙን ዓለም መምራት የቀጠሉ ሲሆን እስከ 1924 ድረስም የተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች በየተራ አመራሩን ተፈራርቀውበታል። የአላህ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) በ632 (አ.ል) ይህችን ዓለም ከለቀቁ በኋላ ኡማውን የመምራቱን ኃላፊነት የቅርብ ጓደኛቸውና አማቻቸው አቡበክር አስ-ሲዲቅ (ረ.ዐ) ናቸው የተረከቡት። አቡበክር (ረ.ዐ) ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አንደበት የኢስላምን ጥሪ እንደሰሙ ነበር በጎ ምላሻቸውን የሰጡት። በዚህም የተነሳ ከአዋቂ ሰዎች ኢስላምን በመቀበል የቀደማቸው አልነበረም። ከዚያ በኋላ በቀጠሉት ዓመታትም የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ቀኝ እጅ በመሆን ኢስላምንና ኡማውን አገልግለዋል።

በሕይወታቸው ካጋጠሟቸው ታላላቅ ፈተናዎች መካከል ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በሞቱ ጊዜ የተከሰተው አንዱ ነው። በርካታ ቁጥር ያላቸው የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች የተወዳጁን መሪያቸውን መሞት እንዲህ በቀላሉ ሊቀበሉት አልቻሉም። ከእነርሱ መካከል ዑመር ኢብኑ አል-ኸጣብ (ረ.ዐ) አንዱ ነበሩ። በዚያ ሁኔታ ላይ በከባድ ሐዘን ተመትቶ ሲታመስ የነበረውን ሕዝበ ሙስሊም የማረጋጋትና ወደ ትክክለኛ ሕሊናው እንዲመለስ የማድረጉን ሥራ አቡበክር (ረ.ዐ) አንድ እጣ ነፍሳቸውን ነበር የተጋፈጡት። ሁኔታው ይህን የመሰለ መልክ ላይ እንዳለ አቡበክር (ረ.ዐ) ከፍ ያለ ስፍራ ላይ ወጡና እንዲህ አሉ፦ "ሰዎች ሆይ! ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ሲያመልክ የነበረ እርሳቸው መሞታቸውን ይወቅ። አላህን የሚያመልክ ግን አላህ ዝንታለም ሕያውና የማይሞት አምላክ እንደሆነ ይገንዘብ።"[25] ይህን በሃይማኖት ታሪክ ከተደረጉ ንግግሮች ሁሉ ግንባር ቀደም የሆነውን ዲስኩር ካደረጉ በኋላ ሰዎች የመረጋጋት ምልክት አሳዩ።

ከዚያ በኋላ አቡበክርን (ረ.ዐ) የገጠማቸው ሌላ ፈተና ደግሞ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ማለፍ ተከትሎ አዕራቦች (ቤዶዊኖች) ዘካ ላለመስጠትና የገቧቸውን ቃል ኪዳኖች ለመፈጸም የማወላወል አዝማሚያ ማሳየታቸው ነበር። አቡበክር (ረ.ዐ) በኸሊፋነት በቆዩባቸው ሁለት ዓመታት እነዚያን የአመጽ አዝማሚያዎች በመስበር ኡማውን አንድ ማድረግ ተሳክቶላቸዋል። እርሳቸው በሞቱ ጊዜም የሙስሊሙ ዓለም ስፋቱ በእጥፍ ማደግ ችሎ ነበር። ይህም የሆነው ፋርስንና ምስራቃዊውን የሮማ ግዛት ማጠቃለል በመቻላቸው ነበር።

ቀጣዮቹ አሥር ዓመታት ደግሞ በገናናው ኸሊፋ ዑመር ኢብን አል-ኸጡብ (ረ.ዐ) መሪነት ፍጹም መረጋጋትና ጸጥታ የሰፈነባቸው ሆኑ። በእነዚያ ጊዜያት ሙስሊሙ ዓለም ሰሜን አፍሪካ፣ ግብፅ፣ ሶሪያ፣ እርሜኒያና ፍልስጤም ድረስ መስፋፋት ችሎ ነበር። በክርስቲያን ጸሐፍት በተዘጋጁ ዜና መዋእሎች ተከትቦ እንደሚገኘው ዑመር (ረ.ዐ) እየሩሳሌም የገቡት በግመላቸው ላይ አገልጋያቸው እንደተቀመጠ እርሳቸው ደግሞ ግመሏን እየሳቡና ትሁን ሆነው ነው። እዚያ እንደደረሱም የግሪክ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የነበሩ ጳጳስ የተቀበሏቸው ሲሆን የከተማዋን ቁልፍ አስረክበዋቸዋል። ከዚያም ወደ ጥንታዊው የአይሁዶች ቤተ-አምልኮ የወሰዷቸው ሲሆን ዑመር (ረ.ዐ) ቦታው በአሳራ ተሸፍኖ ስላገኙት በእጆቻቸው ካጸዱት በኋላ በዚያ ላይ መስጊድ እንዲገነባበት አዘዙ።

የእየሩሳሌም ፓትሪያርክ የሶላት ሰዓት ሲደርስ 'ቸርች ኦቭ ሆሊስክሪፕቸርስ' በሚባለው ስፍራ ይጸልዩ ዘንድ ዑመርን (ረ.ዐ) አስታወሷቸው። ይሁን እንጂ ዑመር (ረ.ዐ) በቤተ-ክርስቲያኑም ሆነ በቅጽሩ ውስጥ ለመስገድ አልፈቀዱም። ከዚያ ይልቅ ከቅጽሩ ውጪ ባለ ስፍራ መስገድ ነበር የመረጡት። ያንንም ያደረጉት መጪዎቹ ትውልዶች ቤተ-ክርስቲያኑን እርሳቸው የሰገዱበት መሆኑን በመጥቀስ

እንዳይቀሟቸው በማሰብ ነው። በዚህም የተነሳ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችና አይሁዶችም ቄምር ዑመርን (ረ.ዐ) "ፍትሐዊው ዑመር" በማለት ይጠሯቸው ነበር። ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አይሁዳውያን ከተለያዩ ሥፍራዎች ተሰባስበው ሃይማኖታቸውን በግልጽ እየተገበሩ ለመኖር ወደ ፍልስጤም ገቡ።

ዑመር (ረ.ዐ) አቡ ሉዕሉዕ (ፌሩዝ) በተባለ ፋርሳዊ ሰው ከቀኖ ከቆሰሉ በኋላ በእርሳቸው አሳሳቢነት የተወሰኑ ሶሐባዎች የሹራ (ምክር ቤቱ) ቡድን ተቋቁሞ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን (ረ.ዐ) ሦስተኛው ኸሊፋ በመሆን ተመረጡ። በእርሳቸው የአስተዳደር ዘመን ኢስላማዊው ኢምፓየር ከአሁኗ ሞሮኮ እስከ ታናሽ ኢሲያ (ሕንድና ፓኪስታን) ድረስ ተለጥጧል። ዑስማን (ረ.ዐ) እንዲያውም ወደ ተለያዩ መሪዎች አምባሳደሮችን መላክ የጀመሩ ሲሆን በቻይና ለሚገኘው የታንግ ሥርወ መንግሥትም ሰዕድ ኢብኑ አቢ ወቃስን (ረ.ዐ) ልከውታል። ምንም እንኳን ንጉሱ ጋኦዞንግ ኢስላምን ባይቀበልም በዑስማን አምባሰደር በጣም የተመሰጠ በመሆኑ በ651 (ድ.ል) የመጀመሪያው መስጊድ እንዲገነባና ሳዕድም (ረ.ዐ) ኢስላምን እያስተማረ በቻይና እንዲቆይ ፈቅዶለታል።



■ ይህ የኒውጂ መስጊድ ሲሆን፣በ966 (ድ.ል) የለያኦ ሥርወ- መንግሥት ይገዛ በነበረበት ጊዜ በቤጂንግ የተገነባ ነው።

በዚሁ ዘመን ነበር ኸሊፋው ዑስማን (ረ.ዐ) ቁርኣን እንዲሰበሰብና በመጽሐፍ መልክ በአንድ ላይ እንዲጠረዝ ያስደረጉት። እያንዳንዱን ፊደልና አንቀጽ በቅርብ ሆነው በማረም አስተካክለውና አስጠርዘው አንድ ቅጂ ለራሳቸው በማስቀረት የቀሩትን በተለያዩ ግዛቶች ለሚገኙ ከተሞችና መንደሮች እንዲዳረሱ አዘዙ። በሌላ አባባል በተለያዩ ግዛቶች የሚኖሩ ሙስሊሞች አዲስ ከተዘጋጀው የቁርኣን ቅጂ ብቻ እየገለበጡ ሌሎቹን እንዲያቃጥሏቸው በማድረግ ቁርኣን እርስ በርሱ እንዳይቃረን አደረጉ። በዛሬው ጊዜ በእጆቻችን የሚገኙ ቅጂዎች በዚያ ዘመን ከነበረው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው ማለት ይቻላል።

ዑስማን (ረ.ዐ) በአስተዳደር ዘመናቸው ከዘመዶቻቸው የተወሰኑትን ሰፊ ከሆኑት ግዛቶች በአንዳንዶቹ ላይ በአስተዳዳሪነት ሾመዋቸው ነበር። ይሁን እንጂ ሹመቱ ከተሰጣቸው ውስጥ ሁሉም በኢስላማዊው መርህ የታነጹ አለነበሩም። ስለሆነም በስራቸው የሚያስተዳድሩት ሕዝብ የጭቆና አገዛዛቸውን በመቃወም አመጽ አስነሳባቸው። ያንን አመጽ ተከትሎ መናፍቃንና ላይ ላዩን ኢስላምን የተቀበሉ በመምሰል ሃይማኖቱን ለመጉዳት ያሴሩ የነበሩ ኃይሎች ምኞታቸውን ለመፈጸም መልካም አጋጣሚ አገኙ። በዚሁ ጦስ በ656 (ድ.ል) ከእነዚህ የአመጽ ሃይሎች የተወሰኑት ኸሊፋውን ገደሏቸው። ኡስማን (ረ.ዐ) ግድያ ሲፈጸምባቸው ቁርኣንን እያነበቡ ነበር።



■ በደማስቆ (ሶሪያ) የሚገኘው ታላቁ መስጊድ የኡመያ ኸሊፋዊ መንግሥት አባሲዮች በ750 (ድ.ል) አስኪያስወግዱትና የመንግሥቱን መቀመጫ ወደ ባግዳድ አስኪያዛውሩት ድረስ በደማስቆ (ሶሪያ) መሠረቱን አድርጉ ቆይቷል።

ከአራቱ በትክክል የተመሩ ኸሊፋዎች (አል-ኹለፋ አር-ራሺዲን) መካከል የመጨረሻው ዓሊ ኢብን አቡ ጣሊብ (ረ.ዐ) ናቸው። ዓሊ (ረ.ዐ) የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአጐት ልጅና የልጃቸው የፋጢማ (ረ.ዐ) ባል እንደነበሩም ይታወቃል። በአስተዳዳሪነት የቆዩት ለሶስት ዓመታትና ጥቂት ወራት ሲሆን እነርሱም በአመፃና በግርግር አለፍ ሲልም በጦርነት ያለፉ ነበሩ። በመጨረሻም የራሳቸውን ነፍስ የሚጠይቅ ወቅት መጣባቸው።

ዓሊ (ረ.ዐ) መዲና አካባቢ ያለው ሁኔታ ለአስተዳደራቸው ችግር እንደሚያስከትልባቸው በተገነዘቡ ጊዜ የመንግስቱን መቀመጫ ብዙ ደጋፊዎቻቸው ወደሚገኙባት የኢራቋ (ኩውፋ) አዛወሩት፥ ፥ እዚያም ሕብረተሰቡ በሃብት እየተንበሻበሸ እርሳቸው ግን የዙህድ ኑሮን ይገፉ ነበር። በዚያ እያሉ መንግስታዊው ግምዣ ቤት በወርቅና በብር መሞላቱን እንደሰሙ የኩፋን ሰዎች በመጥራት አከፋፈሏቸው። በጊዜውም ወርቁን "አንተ ቢጫ!" ብሩን ደግሞ "አንተ ነጭ! ከእኔ ራቁና ወደሌሎች ሰዎች ሂዱ" እያሉ አከፋፍለው ከጨረሱ በኋላ ግምዣ ቤቱ ባዶ ሲሆን እንዲጠረግ አድርገው ሁለት ረከዓ ሶላት እንደሰገዱበት ተወስቷል። አለባበሳቸው ተራ አንደነበረና አነስተኛ ከበሮ እየመቱ ወደ ገበያ በመሄድ ሻጮችና ገዢዎች በሃቅ እንዲገበያዩ ያስታውሱ እንደነበረም በዜና መዋዕላቸው ተጠቅሷል።

የኡስማን (ረ.ዐ) አሟሟት ዘግናኝ ስለነበር መላውን ኡማ አስደንግጧል። ብዙዎችም ዓሊ (ረ.ዐ) ገዳዮቹን በፍጥነት አድነው በመያዝ ፍርድ እንዲሰጣቸው ፈልገዋል። ይሁን እንጂ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ዓሊ (ረ.ዐ) ያንን ማድረግ ባለመቻላቸው ኸዋሪጅ ከሚሰኘው አፈንጋጭ ሃራጥቃ አባላት በተሰነዘረባቸው የደፈጣ ጥቃት ተገደሉ።

ኢስካሚዊው ሥልጣኔ ያከፈባቸው ውጣ ውረዶች

ከዓሊ (ረ.ዐ) በኋላ ዋነኛው ተቀናቃኛቸው የነበሩት ሙዓዊያ (ረ.ዐ) መንግስቱን ወደ ደማስቀ በማዘወር የኡመያ ሥርወ-መንግስት ለቀጣዮቹ ዘጠና ዓመታት ከዚያ ሆኖ እንዲገዛ ሁኔታዎችን አመቻቹ። ኡመያዎችን ያሸነፉት አባሲዮች ደግሞ በ750 (ድ.ል) የመንግስቱን መቀመጫ ወደ ባግዳድ አዛወሩት። በዚያ ወቅት አንድ የበኑው ኡመያ ወጣት ልዑል አምልጦ የሜዲትራንያን ባሕርን በማቋረጥ ወደ አንዱሊሲያ (ስፔይን) አቀና። እርሱ የመሠረተው የኸሊፋ መንግሥት በደቡብ ስፔይን በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት የዘለቀ የአውሮፓውያን የዘወድ ላይ ዕንቁ ሆኖ ቆይቷል።

ይህ በእንዲህ እያለ ባግዳድ ላይ መቀመጫውን ያደረገው የአባሲዮች መንግስት ጥቅሞቹን ለማስከበር ከሰሜን በኩል ቱርካውያን ወታደሮችን ማስመጣት ጀመረ። እነዚህ ቱርካውያን ወታደሮችና ፋርሳውያን ሚኒስትሮች ቁጥራቸው እያደገና ተጽዕኖአቸው እየሰፋ ሲመጣ የአባሲዮች ሥርወ-መንግስት መዳከም ጀመረ። በ1055 (ድ.ል) የሴልጁክ ቱርኮች ምንም እንኳን እውነተኛ የፖለቲካ ጉልበት ቢኖራቸውም ተቃዋሚዎች እንዳይነሱባቸው አባሲዮችን ለስሙ ያህል እየሾሙ መንግስቱን ማስተዳደር ቀጠሉ። ናዚም አል-ሙልክ የተባለው አማካሪ በአስተዳደሩ ውስጥ በዋነኛነት ይገኙ የነበሩትን ሶስቱን ዋና ዋና የብሔር ቡድኖች አንድ ላይ በማዋሃድ የመንግስቱን አመራር ለማጠናከር ሞክሯል። ናዚም የቡድኖቹን የሥራ ድርሻ ማከፋፈሉን ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፥-

"ቱርኮች ያላቸውን ወታደራዊ ኃይል በማጠናከር መስተዳድሩን ይመራሉ። አረቦች ደግሞ ሃይማኖታዊ ዕውቀትን በማስፋፋት እገዛ ያደርጋሉ። ፋርሳውያን በበኩላቸው የመስተዳድሩን ሥልጣኔ በተለያዩ የዕደ

ጥበባት ሥራዎቻቸው እየታገዙ ይዘውራሉ። በዚህ ዓይነት አዲሱ መስተዳድር ቱርካዊ ሱልጣንና የጦር ሃይል፣ የአረብ ሙፍቲዎችና በፋርሳውያን ባለሙያዎችና አሳቢዎች (thinkers) የተሞላ ቢሮክራሲ ይኖረዋል።"[26] ይህ ከላይ የተጠቀሰው ክፍፍል በሚገባ ሥራ ላይ ውሎ በ1071 (ድ.ል) አልፕ-አርስላን የተባለው ቱርካዊ ሱልጣን ሮማኖስ ዲዮጂነስ የተባለውን የቤዛንታይኖች ንጉሥ በመግጠም ጦሩን መገርሰስ ቻለ። በዚህ ጦርነት ሱልጣኑ ንጉሡን ከማረከው በኋላ በነዓ አሰናብቶታል። በዚህ ወሳኝ ጦርነት የተነሣም የአናቶሊያ ግዛት በቱርኮች ቁጥጥር ስር ሊገባ ችሏል። ሱልጣኑ የቤዛንታይኖችን ንጉስ

> አልፕ-አርስላን፦ "እኔ ያንተ ምርኮኛ ሆኜ እፊትህ ብቀርብ ምን ታደርገኝ ነበር?"
> ንጉስ ሮማኖስ፦ "እኔ እንጃ! ምናልባት እገድልህ ይሆናል ወይም ደግሞ በኮንስታንቲኖፕል ጐዳናዎች አስሬ ላስጐትትህ እችላለሁ።"
> አልፕ-አርስላን፦ "የእኔ ቅጣት ደግሞ ከዚህ የከበደ ነው። ነዓ ስለሆንክ ወደሃገርህ መሄድ ትችላለህ።"

ከማረከው በኋላ በሁለቱ ሰዎች መካከል የሚከተለው ምልልስ እንደተደረገ ተወስቷል፦
ይህ እንግዲህ የካቶሊክ አውሮፓ የጦርነት ጨኸት መሆኑ ነው። መጀመሪያ ላይ የፈረንሳውያን ክሩሴደሮች ቡድን ፒተር ዘ-ኧርሚት በተባለው ሰው መሪነት በንዴት ጦፎ ቢመጣም ብዙም ትኩረት አልተቸረውም ነበር። ይሁን እንጂ በሚገባ በፈረሰኞች የታጠቀው የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የጀርመን ናይትስ (knights) ቡድን ግን ችላ ሊባል አይችልም ነበር። በኒቂያ፣ አንጾኪያና ማራ በኩል ሲንደረደር የመጣው ይህ ሃይል ብዙም ሳይቆይ ነዋሪዎቹ በራቸውን ከከፈቱ ምንም ዓይነት አደጋ እንደማይደርስባቸው አረጋገጠላቸው። ይሁን እንጂ ጦሩ ወደነዚህ ከተሞች እንደገባ ከነዋሪዎቹ መካከል ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀር ነበር ሁሉንም የጨፈጨፋቸው።

ይህ ስትራቴጂ በእየሩሳሌምም ተሰርቶበታል። የእየሩሳሌም ነዋሪዎችም እንዲሁ በራቸውን ክፍት እንዲያደርጉ በመስቀለኞች ተጠየቁ። ነዋሪዎቹም ምንም አይደርስብንም ብለው በማሰብ በራቸውን ከፈቱ። ከዚያም ታላቁ እልቂት ተጀመረ። ከሞላ ጐደል መላው ሙስሊምና የአይሁድ ማሕበረሰብ ከክርስቲያኖች እየተለየ ታረደ። የምስራቃዊው ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ከዚያ አካባቢ የተጋዙ ሲሆን ንብረታቸውንም ተወርሰዋል። ከዚህ ሁሉ ሰቆቃ በኋላ ነበር እንግዲህ አንድ ጀግና ሊወለድ ግድ የሆነው።

ሰላሁዲን አል-አዩቢ እውነተኛ የእንበሳ ልብ የነበረው ጀግና

እየሩሳሌም (አል-ቁድስ) በመስቀለኞች ስትወረርና ስትመዘበር ሳላሃዲን በትውልድ መንደሩ ሃይማኖታዊ ትምህርት የሚያጠና ትንሽ ልጅ ነበር። በጣም መንፈሳዊና በሃይማኖቱ የተመሰጠ ሆኖ ያደገው ሳላሃዲን ቁርአንና ሐዲስን አሳምሮ ያጠና ብቻ ሳይሆን የሂሳናዊውን (ግሪክን) ዓለም የፍልስፍና ሥራዎች ሁሉ ልቅም አድርጐ ያውቅ ነበር። ይህ ወጣት ሱልጣን ሆኖ መንበሩን ከያዘ በኋላ በ1187 (ድ.ል) ያለብዙ ደም መፋሰስ ነበር አብዛኛውን የመስቀለኞች ይዞታ ለመቆጣጠር የቻለው። ይህንንም ለማድረግ የተጠቀመው ስልት ሰራዊታቸውን በመከበብ የኢኮኖሚ እቀባ በመጣልና የውጊያ ማቆም ስምምነትን በማድረግ ነበር። በዚህ ሁሉ ድርጊት ሳላሃዲን ግዛት ብቻ ሳይሆን በሁለቱም በኩል የተመሰገበትን ዝናም አትርፏል። ይህ መልካም ስሙም እስከዘመናችን የደረሰ ሲሆን እስከ ዓለም ፍፃሜም ይዘልቃል።

ሳላሃዲን እያንዳንዷን ግዛት በተቆጣጠረ ቁጥር የኸሊፋው ኡመርን (ረ.ዐ) ባሕሪ ነበር ያንጸባርቅ የነበረው። ማንኛውም ዜጋ በፈለገበት ቦታ የመኖር መብቱ የተጠበቀ ነው። ይህም መብት የሚረጋገጠው

በንብረቱ፣ በሃይማኖቱና በሕይወቱ ዋስትና እንዲኖረው በማድረግ ጭምር ነው። መስቀለኞች ስምምነት ለማድረግ በማይፈልጉባቸው ጊዜያት ደግሞ ሳላሂዲን ጦርነት ይገጥምና ያሸንፋቸዋል። ብቀላም ሆነ ዘረፋ አይፈጽምባቸውም።

ሙድመት ወደ ስርወ-መንግሥትነት ሲቀየር

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር እንግዲህ ታላቅ የሆኑት የጥፋት ሃይሎች ከማዕከላዊ ኢሲያ እየተንደረደሩ በመምጣት የሙስሊሙን ዓለም ክፋኛ ያፈራረሱት። በጀንጊዝ ኻን የሚመሩት ሞንጐሊያውያን ለወረራቸው እንደ ምክንያት የሆናቸው የኽዋራዝሚያ (የአሁኗ ኢራን) ንጉስ መልእክተኞቻቸውን ማጉላላቱና መበደሉ ነበር። ከዚያም እንደ ቋያ እሳት በፍጥነት የሚገሰግሰው ሠራዊታቸው ኽዋራዝሚያን ካፈራረሰ በኋላ በአባሲዮች መንግሥት (ኢምፓየር) በኩል አልፎ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ጋለበ። በአሥራ ሁለተኛው መቶ ዘመን ሞንጐሊያውን የሙስሊሙን ዓለም በመውረርና ሚሊዮኖችን በመፍጀት ስልጣኔውን ጨርሰው ከምድረ ገጽ የሚያጠፉ መሰሉ። ኽዋራዝሚያን ጨምሮም በርካታ ከተሞችን ሙሉ ለሙሉ አወደሟቸው። ከአንድ ሚሊዮን ሕዝብ የበለጠ የሚኖርባቸውን ሄራትና ኒሸፑርን የመሣሠሉት ከተሞች ከመቶ ያነሱ ነዋሪዎች ብቻ ቀሯቸው። የተወሳሰቡ የመስኖ ቦዮች ዳግም ላያንሰራሩ ፈራረሱ። ኢብን ባጡጣ የተባለው ሙስሊም ተጓዥ ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ




■ በኢስታንቡል ቱርክ የሚገኘው የሜይደን ታዎር (ሕንፃ)

እነዚያን ከተሞች ሲጐበኝ እንደፈራረሱ ነበር ያገኛቸው። በ1258 (ድ.ል) የአባሲዮች መቀመጫ የነበረችው ውቧ ባግዳድ በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መጽሐፍቶቿና ቅርሶቿ ጋር ወደመች። ከዚያም በኢስላም ታሪክ እጅግ አስደናቂ በሆነ ክስተት ሙስሊሞች ሁሉንም ነገር እንደገና ሊመልሱት ችለዋል። ይህ የሆነው በወታደራዊ ዘመቻ ሳይሆን በ1257 (ድ.ል) የሞንጐሊያውን መሪዎች ኢስላምን በመቀበላቸው ነበር። የሙስሊሞች መንግስት (ኢምፓየር) ከዚያ በኋላ ተለጥጦ በምስራቅ በኩል እስከ ሩሲያና ቻይና ደረሰ።

በሌላ በኩል ደግሞ በምዕራብ በኩል ኦቶማን ቱርኮች ወደ ባልካን ሃገራት በመገስገስ የቤዛንታይኖችን ግዛቶች በመያዝ ላይ ነበሩ። በ1453 ሱልጣን ሙሐመድ ዳግማዊው ኮንስታንቲኖፖልን ተቆጣጠረ።

በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ አካባቢ በሙስሊሙ ዓለም ሶስት የተለያዩ ግዛቶች (empires) ብቅ ብለው ይታዩ ነበር። እነርሱም ሳፋዊዮች በፋርስ፣ የሞንጐሊያዊያን ዝርዮች የሆኑት ሞጐሎች በሕንድ፣ እንዲሁም ይዞታውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሰፋ የሄደው የኦቶማኖች መንግስት ነበሩ። የመጀመሪያው በ17ኛው መቶ መጀመሪያ ላይ የከሰመ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ18ኛው መቶ ወድቋል። ለእነዚህ ሁለቱ ታላላቅ ኢምፓየሮች መክሰም ምክንያት የሆነው ከውስጣዊ ችግሮች ባሻገር በዓለም ጂኦፖለቲካ ላይ የደረሰው ለውጥ ነው። ኦቶማን ቱርኮች መስፋፋታቸውን ቀጥለው ወደ አውሮፓና ሰሜን አፍሪካ የገፉ ሲሆን በ1922 ቪየና ላይ ከገጠማቸው ሽንፈት በኋላ ግን እነርሱም መክሰም ጀመሩ። ይህ ሁኔታም ሙስሊሙ ዓለም ዛሬ ለሚገኝበትና በተለያዩ ሃገራት (መንግስታት) እንዲከፋፈል መንገድ ጠርጓል።

በኢስላም ታሪክ ዋነኛው ተዓምር ተደርጐ የሚወሰደው በፍጥነት መስፋፋቱ አይደለም። ከዚያ ይልቅ ተንቀውና ተረስተው የኖሩ ዘላኖች በየምድር ማዕዘናት ከዚያ በፊት ታይቶና ተሰምቶ የማያውቅ ስልጣኔን መመስረታቸው እንጂ። ሞንጐሊያውያን የጂን ሥርወ-መንግስትን በመውረር አብያተ መንግስታቱን ሲያፈራርሱ ቪስገቶት የሚባሉት የአውሮፓ ጐሣዎች ደግሞ ሮምን ለመያዝ ይጥሩ ነበር። የሞንጐሊያውያንን ዘላኖችን ወረራ ለየት የሚያደርገው ካደረሱት ልኩ የማይታወቅ ጥፋት ጐን ለጐን በባሕል፣ በሳይንስና በፍልስፍና የራሳቸውን የሥልጣኔ አሻራ ትተው ማለፋቸው ነው። በዚህ አጋጣሚ የተስተዋለው ሌላው ጉዳይ ደግሞ ሞንጐሊያውያን በሙስሊሙ ዓለም ላይ ባደረሱት ጥፋት ሃይማኖቱ ከነስልጣኔው አለቀለት ከተባለ በኋላ እንደገና በሌላ አቅጣጫ በራሳቸው በሞንጐሊያውያኑ እጅ የማንሰራራቱ ብስራት ነው። (የሕንዱን ሞጉል ኢምፓየር ሥልጣኔ ያጠፏል)። ኢምፓየሮች ይነሳሉ ይከስማሉ። ይሁን እንጂ ሃይማኖት የሚለካው በግዛቶች መስፋፋትና ወይም መዳከም አይደለም። በተደጋጋሚ እንደተስተዋለው ሃይማኖት ጠንካራ ሆኖ የታየው ተከታዮቹ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሆነው በተገኙባቸው ጊዜያት ነውና።



■ በላሆር ፓኪስታን የሚገኘውን የበድሻሂ መስጊድ ቱሪስቶች ሲጎበኙት። የመስጊዱ ግንባታ የተጀመረው በስድስተኛው የሞጉል ንጉስ አውራንግዘብ አታምጊር ጊዜ ሲሆን የተጠናቀቀው ደግሞ በ1673 (ድ.ል) ነበር።

ምስላዊ ወግ ፦ የምዕመናን ሕይወቶች

የግብጻዊው ሙዚይን ቤተሰቦች

የመስጊዱን ግምገ ቤት የመጠበቁንና የሙዓዚንነቱን ሥራ ደርቦ የሚሠራው ኸሊፋ ተቂ መሐመድ ከተፋፈገው የካይሮ እንብርት ወጣ ብለው ከሚኙት መንደሮች አንዱ ውስጥ በሚገኝ መስጊድ የተለያዩ ተግባራት በማከናወን በሥራ ተወጥሮ ይውላል። ከሥራዎቹ መካከል ለመስጊዱ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮችን ማቅረብ፣ ሌሎች ሠራተኞችን መቆጣጠርና ጐላ ባለው ድምጹ በቀን አምስት ጊዜያት ያህል ምዕመናንን ወደ ጸሎት መጥራት (አዛን ማድረግ) ይገኙበታል። የሚኖረው ከባለቤቱ እንዲሁም ዩሱፍና መርየም ከሚባሉት ልጆቹ ጋር ነው። ኸሊፋ ሰው ወዳድ ሲሆን ቤተሰባዊ ትስስርን ማጥበቅና በመልካም ሥነ-ምግባር መኖርን መመሪያው አድርጐ ይዟል። በተጨማሪም መልካም ነገሮች ሁሉ የሚመነጩት ለወላጆች በምናሳየው ደግነትና ርህራሄ ነው የሚል እምነት አለው። ለዚህም ነው እስከዛሬዋ ቀን ድረስ እናቱን ሁልጊዜም ጧትና ማታ የሚጐበኛቸው። ኸሊፋ በቀን ለአምስት ጊዜያት ያህል ለሶላት ጥሪ ማድረጉንና የታላላቅ ኢማሞችን ዜጥባ (ትምህርታዊ መግለጫ) በማዳመጡ ይኮራል። ከፊቱ ላይ ምንጊዜም ፈገግታ የማይለየው ሲሆን በተለይም ደግሞ እምነቱ ለሌሎች ሰዎች በጐ ማድረግን እንዳስተማረው ሲናገር ፊቱ ይበልጥ ይደምቃል።

የሕይወቱ መነቃቃት ምንጭ የዝንታለም ብርሃን የሆነው ቁርኣን ነው። ኸሊፋ ማንበብና መጻፍን በራሱ ጥረት ተምሮ ያወቀ ቆራጥ ሰው ነው። የዓለምን ሕዝብ ሁኔታ አስመልክቶ ሲናገር ትልቁ የሥነ-ምግባር ክፍተት የተፈጠረው ሰዎች ሃይማኖትን እንከተላለን እያሉ ከበጐ ተግባር ጋር የተፋቱ በመሆናቸው እንደሆነ ይተቻል። እንዲህ ይላል፡- "ሰዎች ምንም እንኳን በራሳቸው ወይም በሚወዷቸው ሰዎች ላይ ችግር እንደሚመጣ ቢያውቁም ሁልጊዜም እውነትን ብቻ መናገር አለባቸው። እያንዳንዱ ሰው ከራሱ መጀመር አለበት። ከዚያም ከሚቀርቡት" ይህን ካለ በኋላም ወደ ተለመደው ፈገግታው በመመለስ "መልካም ነገር በእኔና በኡማዬ ላይ እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ ይኖራል።" የሚለውን ነቢያዊ ሐዲስ ጠቀሰ።











የአሜሪካውያን ቤተሰብ፡ ስድስት ልጆችና የትምህርት ማዕከል

ሳራህና ማይክ ኪም ከዩናይትድ ስቴትስ የባሕር ኃይል አካዳሚ ተመርቀዋል። ይሁን እንጂ ሁለቱም ቢሆኑ የወደፊቱ ሕይወታቸው በሰሜን ካሮላይና በሚገኝና ሃያ ሰባት ኤከር በሚሸፍን የእርሻ ቦታ (የከብት ርባታ ጣቢያ) ይሸከረከራል ብለው አስበው አያውቁም። ስድስት ልጆችን እንደሚወልዱና 'ILM TREE' የተባለ ለትርፍ ያልተቋቋመና ለሃገሬው ሙስሊም ልጆች የሚበጅ የዕውቀት ማዕከል እንደሚመሰርቱም እንዲሁ በምናባቸው ውል ብሎባቸው አያውቅም። ያኔ ገና በማደግ ላይ የነበረችው ሳራህ ስለሙስሊሞችና የሙስሊሙ ዓለም የነበራት ዕውቀት የቅርብ ጓደኛዋ ኢስላምን አስከተቀበለች ድረስ ውስን ነበር። ጓደኛዋ በአንድ ዓይነት አዲስ የአምልኮ ሥርዓት እንደተጠመደች የተሰማት ሳራ ኢስላምን መመርመር ትጀምርና ብዙም ሳትቆይ እውነታው ፍንትው ብሎ ይገለጽላታል። ከዚያ በኋላ ለረዥም ጊዜ ጓደኛዋ በነበረው ማይክና አዲስ ባገኘችው እውነታ መካከል ልዩ ክፍል ይልባታል። ሆኖም ግን በውሳኔዋ በመጽናት አዲሱ ሃይማኖቷ ከቆየው ወዳጅነታቸው ጋር አብሮ ሊሄድ እንደማይችል በመግለጽ ደብዳቤ ትጽፍለታለች። ውሳኔዋ መጀመሪያ ላይ ያስደነገጠው ማይክ በበኩሉ ፍቅረኛውን የሚነጥቀውን ይህን ሃይማኖት ለማጥናት ቆርጦ ተነሣ። ጥናቱን እንዳገባደደም የሳራህ ኃይማኖት የእርሱም እንደሆነ በግልጽ አወጀ።

ምንም እንኳን የሁለቱ ተጓዳኞች በርካታ ቤተሰቦች ኢስላምን ገና ባይቀበሉም ሁለቱ ሰዎች የመሠረቱትን ድርጅታቸውን በመደገፍ ከጐናቸው ቆመዋል። ኢልም ትሪ የተባለው የነሳራህ ድርጅት የካሊፎርኒያን ባሕረሰላጤ አካባቢ ቤተሰቦች የትምህርት ፍላጐታቸውን ከማርካት ጀምሮ በሁሉም የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያሉ ሰዎችን ይረዳል።











ኢንዶኔዢያውያን በተሰብ፡- ማሕበረሰቡን በማገልገል የሚሸመት ደስታ

ሰላሃዲን አል-አዩብ፣ አቲቅ ኑርዋህዩኒና ሴት ልጆቻቸው ዘሃራ አማሊያና ኧንሳ መሊሃ የሚኖሩት በዓለም በርካታ ሙስሊሞች በሚኖሩበት ኢንዶኔዢያ ነው። ሁለቱም ወላጆች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሥራ ይሠራሉ። አቲቅ በእንዶኔዢያ ዩኒቨርስቲ የጤና ፖሊሲና አስተዳደር የምታስተምር ሲሆን GTZ በተባለ የጀርመን ቴክኒካዊ ተራድኦ ድርጅት በአማካሪነት ታገለግላለች። ባለቤቷ ሳላሃዲን ደግሞ በኢንዶኔዢያ የኡለማ ምክር ቤት የፊትዋ ኮሚሽን ጸሐፊ ሲሆን በኢንዶኔዢያ ፕሬዚዳንታዊ መማክርት ካውንስል የሃይማኖት ኤክስፐርት ሆኖ ያገለግላል። ባልና ሚስቱ ካለባቸው የሥራ መደራረብ ጐን ለጐን በአቅራቢያቸው በሚገኝ መስጊድ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ ልጆቻቸውን ከማሳደግ ጐን ለጐን ሃይማኖታዊና ማሕበረሰባዊ ዋጋ ላላቸው ጉዳዮች ጊዜያቸውን ይዋጃሉ።











ክፍል ሦስት፣

የካቴ እሴቶች እና እውነታዎች



የእንግሊዝ ጽጌረዳዎችና የደች ቱሊፕ አበቦች

የኢስላምና የምዕራቡ ዓለም አስደናቂ ታሪኮች

በ1603 (ድ.ል) አህመድ አል-መንሱር የተባሉ የሞሮኮ ንጉስ በጊዜው ለነበሩት የእንግሊዝ አቻቸው ቀዳማዊት ኤልዛቤት አንድ ሃሳብ አቅርበውላቸው ነበር። ንግስቷ ሃሳቡን ተቀብለው ቢሆን ኖሮ አሁን ያለው የዓለም ታሪክ ሊቀየር በቻለ ነበር። ንጉሡ ያቀረቡት ሃሳብ የሞሮኮና የእንግሊዝ መርከቦች አንድ ላይ ሆነው በአሜሪካ የሚገኙ የስፔይን ግዛቶችን እንዲያጠቁና የጋራ ጠላታቸው የሆነችውን ስፔይንን ኃይሎች ከዚያ ጠራርገው በማውጣት ግዛቶቹን ለሁልጊዜውም አብረው እንዲያስተዳድሩ ነበር።[27]

ንጉሱ በተጨማሪም አዲሱ ዓለም ሞቃት በመሆኑ ለወደፊቱ ከእንግሊዛውያን ይልቅ የሞሮኮአውያን እንደሚሆን ተንብየው ነበር። ምን ያደርጋል! የሞሮኮው ንጉሥ ሃሳብ ተቀባይነት አላገኘም። ይህን ታሪክ የሚመረምር ዘመናዊ አንባቢ የእንግሊዞችን ውሳኔ መገንዘብ አይከብደውም። ምክንያቱም ኤልዛቤትና አማካሪዎቻቸው የሁለቱን ሃገራት የሃይማኖትና የባህል ልዩነቶች ባገናዘበ መልኩ ያንን የዘመቻ ሃሳብ ሊቀበሉት እንደማይችሉ ይታወቃልና ነው። ታሪክ በተደጋጋሚ እንዳሳየን ሙስሊሙ ዓለምና የሌላ ሃይማኖት ተከታይ የሆነው ዓለም ለረዥም ጊዜያት የዘለቀ ቅራኔና ግጭት ሲያካሄዱ ቆይተዋል።

አውሮፓ በፊውዳል ባላባቶች ትተዳደር በነበረችባቸው ጊዜያት ለባሮችና ለሴቶች ነፃነት ያጐናጸፈው ኢስላም ክፋኛ ሥርዓት አልበኛ ሃይማኖት ተደርጐ ተብጠልጥሏል። አውሮፓውያኑ ኢስላምን ይመለከቱ የነበረው ለእነርሱ ማሕበራዊ እሴቶች ቦታ የማይሰጥና በሁሉም መልኩ ተቃርኖ የሚያሳይ እንደሆነ አድርገው ነበር።[28] በዚህም የተነሣ በምዕራቡ ዓለም የትምህርት ተቋማት ዘንድ የኢስላም ታሪክ በሰፊው ችላ ተባለ። ይህም ልክ ዓለም ከጥንቱ ሥልጣኔ ያለምንም መሸጋገሪያ በአንድ ጊዜ እምመር ብላ ወደ ዘመነ-ተሃድሶ (Renaissance) የደረሰች ያስመስላታል።

ትርፉማ ንግድ?

ምዕራባዊያን ምሁራን ያለነርሱ አስተዋጽኦ ለዘመነ-ተሃድሶ (Renaissance) ሊበቁ እንደማይችሉ እውቅና የሚሰጧቸው ሕዝቦች በእርግጥም አልሉ። አሁን የሚገኙ የሙስሊም ማሕበረሰቦችን ያስገኙት ቀደምት ትውልዶች ያለምንም ጥርጥር ኢስላማዊ ሥልጣኔን ለያዙበት ኢምፓየር ያበረከቱ ናቸው። በቀደምት (classic) ስልጣኔ ያለፉ፣ ሳይንስን፣ ሕግንና ሌሎች ጥበባትን የቀሰሙና ሄሊናዊውን ሥልጣኔ

ቀዳሚ አድርገው ይመለከቱ የነበሩ ተማሪዎች በዕለት ተዕለት የዕውቀት ፍለጋ ሂደት የሚያገኟቸው ማጣቀሻዎች ከኢስላማዊው ዓለምና ምሁራን በኩል የተገኙ መሆናቸውን ያውቃሉ ያረጋግጣሉም።

በርካታ ክላሲካል የሆኑ የላቲን መጽሐፍት በሙስሊሙ ዓለም ምሁራን ጥበቃ ባይደረግላቸውና ተተርጉመውና ተሻሽለው ለኋላኛው የአውሮፓ ማሕበረሰብ ባይቀርቡ ምናልባትም ዓለም አሁን ለደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ ባልበቃም ነበር። የአላህ ነቢይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ ከምዕተ ዓመታት በኋላ ሙስሊሞች ወደ ምዕራብ፣ ምሥራቅና ሰሜን በመስፋፋት ታላቅና አዲስ ዓለም እንዲወለድ አበርክቶ አድርገዋል። በ732 (ድ.ል) የሙስሊሞች ሠራዊት በስፔን በኩል የፒሬኒስን ተራሮች አቋርጦ የዛሬዋ ፈረንሳይ ምድር ሊገባ ተቃርቦ ነበር። ይሁን እንጂ ቻርለስ ማርቴል የተባለው መሪያቸው ጠንክሮ በመመከት ይህ እንዳይሳካ ማድረግ ችሏል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም 'ኢስላማዊውና' 'ክርስቲያናዊው' ዓለም በግልጽ ድንበሮች ለሁለት እንደተከፈለ እስካሁንም ድረስ ቆይቷል።

ይሁን እንጂ ሙስሊሞች ሙስሊም ካልሆነው ዓለም ጋር በብዙ መንገድ ግንኙት ያደርጉ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የንግድ ትስስር አንዱ ነው። ሌላው ቀርቶ የመስቀል ጦርነት ይካሄድ በነበረባቸው ጊዜያት እንኳን ሳይቀር የአውሮፓ ወደቦች ከሙስሊሙ ዓለም ጋር በሚደረግ የንግድ ትስስር በሥራ የተወጠሩ ነበሩ።

በሚሪያም መጐናጸፊያ ላይ የተሳኩ የዐረብኛ የጥበብ አሻራዎች

የቬኒስ ከተማ ዕድል ይበልጡንም ከሙስሊሙ ዓለም ጋር ከ17ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ ከፍ ባለ ሁኔታ የተሳሰረ ነበር። ይህም ትስስር የተጀመረው ቪኒሲያኖች "የቅዱስ ማርቆስን" ቅርስ ከግብፃውያን እጅ ለማስለቀቅ ወደዚያው በተጓዘበት ጊዜ ነበር። ቬኒስ ሙስሊሞች አውሮፓውያንን ከመስቀልኝነት ይልቅ ጥሩ የንግድ አጋሮች አድርገው እንዲመለከቷቸው ትልቅ ሚና ተጫውታለች። ሃር፣ ምንጣፍ፣ ቅመማ ቅመምና ሴራሚክስ ወደ ምዕራቡ ዓለም ከሚገቡት ሸቀጦች ጥቂቶቹ ሲሆኑ ሱፍ፣ እንጨት (ጣውላ)ና የመሣሠሉት ደግሞ ወደ ሙስሊሙ ዓለም የሚገቡ ሸቀጦች ነበሩ። በዚህም የተነሣ በሃይማኖት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ የቅብ ስዕሎች በጨርቅ ላይ ሲሳሉ የዐረብኛን የቅርፃ ቅርጽና ቅብ ዘየን ተከትለው እንደነበር ማስተዋል ይቻላል።

ቬኒስ ሪፓብሊክ ከሙስሊሞች ጋር በምታደርገው የንግድ ትስስር ግማሽ የሚሆነውን ገቢዋን ትሸፍን ነበር። ይህን የንግድ እንቅስቃሴዋንም የቀረው የአውሮፓ ክፍል ከመጀመሩ ከረዥም ዘመናት በፊት ታካሂድ ነበር። ይህ ቀዳሚ የሆነ የኢኮኖሚ ትስስሯ ደግሞ በሜዲትራኒያን ባሕር ዳርቻ ከሚገኙ ከተሞች ሁሉ ቅድመ ተሐድሶ (Pre-Renaissance) የበለጸገች እንድትሆን አስችሏታል። ምንም እንኳን ቬኒስ ከሙስሊሙ ዓለም ጋር የንግድ ትስስር በማድረግ ግንባር ቀደም ሚና ብትጫወትና በኢብን ኸልዶን የ13ኛው መቶ ዘመን ካርታ ላይ እውቅና ያገኘች ብቸኛ የክርስቲያኖች ከተማ ብትሆንም በማምሉኮችና አቶማን ቱርኮች በሚመራው ሙስሊም ዓለም የነበራት ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም።

ቬኒሲያዊ የንግድ ሰዎች የሙስሊሙን ዓለም በጐበኙ ጊዜ እዚያ በተመለከቱት የዕደ ጥበብ ውጤት በእጅጉ የተደነቁ መሆናቸው ተወስቷል። የፍሎረንስ ተወላጅ የሆነው ሲሞን ሲጐሊ በ1384 (ድ.ል) "አንድ ዓመት ለሚሆን ጊዜ መላው የክርስቲያን ዓለም ከደማስቆ በሚመጡለት ሸቀጦች ላይ ሙሉ



■ በዘመኑ በነበሩ የቅብ ስዕሎች ላይ የሚታዩ አልባሳት የዐረባዊ ትውፊት አሻራ የሚንጸባረቅባቸው ናቸው።

ለሙሉ ጥገኛ ሆኖ ነበር" በማለት እውነታውን ሳይሸሽግ ተናግሯል። ሲሞን አክሎ እንደተናገረው "እዚያ የሚገኙ ዕቃዎችና ሸቀጦች በጣም ማራኪ ከመሆናቸው የተነሣ አንዱን ገዝቶ ሌላውን መተው ስለማይቻል ሌላው ቀርቶ በእግሮችህ መቅኒዎች ውስጥ ገንዘብ ቢኖርህ እንኳን ሰብረህ ገንዘቡን በማውጣት ከመግዛት አትቆጠብም" ብሏል።[29]

ጆን ሩስኪን የተባለውና 'ዘ-ስቶን ኦቭ ቬኒስ' የተባለውን መጽሐፍ ያዘጋጀው ሰው "አብዛኛው የቬኒስ ሥነ-ሕንፃና ቁሳቁስ ከመካከለኛው ምስራቅ የተቀዳ አሻራ ይስተዋልበታል። ሌላው ቀርቶ ዝነኞቹ ካፌዎቿ እንኳን ከኢስታንቡል ካፌዎች ጋር በሞዴል ተመሣሣይ ናቸው" ብሏል። የፖሌርሞው (ሲሲሊ) ንጉስ ዳግማዊ ሮጀር የቤተመንግሥቱ የመልከዓ ምድር ባለሙያ ከነበረው አል-ኢድሪሲ ጐን ተቀምጦ 'ዘ-ቡክ ኦቭ ሮጀር' በተባለው መጽሐፍ ዙሪያ ይወያያሉ። ንጉሱ አፍሪካዊውን በሲሲሊ ደሴት ስለነበሩት ሙስሊሞች ታሪክ ይነግረው ዘንድ ይጠይቀዋል።

ሮጀር የሲሲሊ ንጉስ ሆኖ አልጋውን ሲቆናጠጥ በሲሲሊ የነበረው ኢስላማዊው ኢምፓየር ከመቶ ዓመት በፊት ፈራርሶ ነበር። ይሁን እንጂ ያለፈው ምዕተ ዓመት ኢስላማዊ ውርሶች በእያንዳንዱ የሕዝቡ ሕይወት በግልጽ ይንጸባረቁ ነበር። አረብኛ በሰፊው ይነገራል። እንዲሁም ልዩ የሆነው የአረብ ሥነ-



■ የቬኒስ ካፌዎች ከኢስታንቡል ካፌዎች ጋር በሞዴል ተመሳሳይ ናቸው።

ጥበብ አሻራ በመላዋ ፓሌርሞ ከተማ አብያተ ክርስቲያናት ይታያል። ንጉስ ሮጀር ያሳተማቸውና በሁለት አንዳንዴም በሶስት ቋንቋዎች የተፃፈ ጽሑፍ የሚታይባቸው ሳንቲሞች ላይ "ንጉስ ሮጀር በአላህ ጸጋ ኃይልን የተጐናጸፈ!" የሚል ንባብ ይታያል። ብዙዎቹ የመንግስቱ መዛግብት የሚጠበቁት ሙስሊም በሆኑ ሠራተኞች ነው።

ሁሉንም ነገር ኢስላማዊ ገፅታ እንዲላበስ በማድረግ ፍላጐቱ አየተገፋ ሮጀር በሳሌርኖ የሚገኘው የተርጓሚዎች ቡድን የአይሁድና የሙስሊም መጽሐፍትን ከአንድሉስ በማስመጣት ወደ ክሪስቲያኑ ዓለም እየተረጐመ እንዲሰራጭ ያደርግ ነበር። ሮጀር ራሱ አረብኛን በሚገባ ይናገር የነበረ ሲሆን ከካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን ጋር አዘውትሮ ይጋጭ ነበር። ከሁለት ትውልዶች በኋላ አልጋውን የተቆናጠጠው የልጅ ልጁ ፍሬደሬክ ዳግማዊውም የእርሱን ፈለግ በመከተሉ "የተጠመቀው ሱልጣን" የሚል ቅጽል አትርፏል። ምክንያቱም ፍሬደሬክ ኢስላማዊ ባሕልና ወጐችን ያደንቅ ነበርና ነው። ሁለቱም ንጉሶች ሙስሊሞችን ከመስቀለኞች ጋር ሆነው ለማጥቃት አሻፈረን ብለዋል። እንዲሁም ሁለቱም መንግስታዊውን መስተዳድር ያዋቀሩት ቀደም ሲል ሲሲሊን ይገዛ የነበረው ኢስላማዊ መንግስት ይምመራበት በነበረው የማሊኪ መዝሃብ ነበር።

ቫይኪንግ የሚባሉት ሕዝቦች በቀን አምስት ጊዜ ይሰግዱ ነበርን?

የዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ኢስላማዊ መጽሐፍት ያልተለመዱ የሆኑ የሶላት አሰጋገድ ሕግጋትን ያቀፉ ነበሩ። ይህም የሆነው ሩቅ በሆኑት የስካንዲኔቪያ ሃገራት ከዓመቱ ውስጥ በተወሰኑ ወራት ጨለማ የሚባል ነገር ስላልነበረ ነው። ታዲያ ጨለማ ሳይኖር እንዴት የኢሻን ሶላት መስገድ ይቻላል? በሜዲትራኒያን አካባቢ የነበሩ ሙስሊም ምሁራን ለዚህ ጥያቄ ሁነኛ መልስ በማግኘት ግኝታቸው በኢስላማዊው የሸሪዓ ሕግ ላይ እንዲካተት አድርገዋል።

በ920 (ድል) የስላቭ ሕዝቦች ንጉስ ለባግዳዱ ኸሊፋ «እውነተኛውን እምነት» ለሕዝቦቹ ያስተምሩለት ዘንድ ምሁራንን እንዲልክለት ጠየቀው። ከአንድ ዓመት በኋላ መልዕክተኞቹ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ማይሎችን አቋርጠው እዚያ ደረሡ። ይህን ዜና ማግኘት የተቻለው የአምባሳደሩ ፀሐፊ በነበረው ኢብን ፈድላን አማካይነት ሲሆን ለዚህ ድርጊቱ ምስጋና ይገባዋል። የኢብን ፈድላን ማስታወሻ ከዚህም በተጨማሪ ከሮማውያን በኋላ የተገኘ የሩሲያን ገለጣ መልከዓ ምድር የሚያስተዋውቅና የቫይኪንግ ሕዝቦች ያነጿቸው አስደናቂ ጀልባዎች የተቀበሩባቸውን ሥፍራዎች የሚያመለክት ከዓይን አማኝ የተገኘ መረጃ መሆኑ ታውቋል።

ንጉሡ እንዲላኩለት የጠየቀው ምሁራን ኢስላምን ስለማስተማራቸው የሚታወቅ ነገር ባይኖርም መልዕክተኞቹ ያደረጉት ጉዞ ግን እጅግ በጣም በስኬት የተደመደመ ነበር። ኢብን ፈድላንና ባልደረቦቹ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ባደረጉት ጉዞ በካስፒያን ባሕርና በኡራል ተራሮች መካከል የኡጋዝ ቱርኮችን አገኙ። ቱርኮቹ ኢስላምን እንዳልተገነዘቡ የተረዳው ኢብን ፈድላን የሃያማኖቱን መሠረታዊ ትምህርቶችና ቁርዓንን አስተማራቸው። ይህንን ካደረገ በኋላም ከቡድኑ ጋር ጉዟቸውን ቀጠሉ። ይህ ከሆነ ከመቶ ዓመት በኋላ የኡጋዝ ቱርኮች የኢስላምን አርማ ተሸካሚዎች በመሆን ታላቁን የኦቶማንን ኢምፓየር መሠረቱ።

የዓለም ፈርጥ የሆነች ምድር

የኡመያ ሥርው መንግስት ወድቆ በአባሲዮች ሲተካና የመንግስቱ መቀመጫ ከደማስቆ ወደ ባግዳድ ሲዛወር አንድ ወጣት የኡመያ ልዑል ብቻ ተርፎ ነበር። ይህ አብዱር-ረሕማን የተባለ ልዑል ጥቂት ተከታዮቹን ይዞ በሰሜን አፍሪካ በኩል አድርጎ ደቡብ ስፔይን (አል-አንደሉሲያ) ገባ። እርግጥ ነው በጊዜው አብዱር-ረሕማን ለስላሳ ዓመታት የቆየው አገዛዙ በአውሮፓ የመካከለኛው ዘመን ታላቅ ሥርወ መንግስት መነሻ እንደሚሆን ለመገመት አይችልም ነበር። ሙስሊሞች በደቡብ ስፔይን ከዚያ ጊዜ ጀምረው ለቀጣዮቹ ስምንት መቶ ዓመታት የዓለማችን ፈርጥ የሆነውን ኢስላማዊ ኢምፓየር ሊመሠርቱ በቅተዋል። በሳይንስ በባሕልና በቴክኖሎጂ በኪነጥበብና በሃይማኖት መቻቻል አቻ ያልተገኘለትን ያንን መንግሥት ለዓለም ያበረከቱ ሙስሊሞች ታላቅ ባለውለታዎቻችን ናቸው። ይህን ለማለት በቂ ምክንያት ማቅረብ ይቻላል። ዋና ከተማዋ ኮርዶባ (ቁርጡባ) በክርስቲያኑ ዓለም «የዓለማችን ዕንቁ» ለመባል በቅታ ነበር።

እርግጥ ነው በሕዝቦቿ መካከል ስለነበረው መቻቻል የተጋነኑ አፈታሪኮች ቢነዙም ለሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ጊዜው ለአይሁዳዊያን ባሕልም ወርቃማው ዘመን እንደነበር አፍን ሞልቶ መናገር ግን ይቻላል። ክርስቲያኖችም ቢሆኑ በመንግስቱ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የተሰጣቸው ሲሆን የሚከፋበት ምንም ሁኔታ አልገጠማቸውም።

የዘጠነኛው መቶ ዘመን የሊዮን ንጉስ የነበረው ወፍራሙ ንጉሥ ሳንቾ ከአካላዊ ግዝፈቱ ጋር በተያያዘ የወጣለት 'ኪንግ ሳንቾ ዘ-ፋት' (ወፍራሙ ንጉስ ሳንቾ) የተሰኘው ቅጽል ስሙ ፍጹም ቅዠት ፈጥሮበት ነበር። ጠላቶቹም ቢሆኑ ይህንን ግዙፈነቱን በማንሳት ለአመራር ብቃት እንደማይኖረው እየተናገሩ አሳቀቁት። ንጉሱ የወደፊቱ እጣ ፈንታው ያምር ዘንድ ዕድሉ ሁሉ ያለው በደቡባዊ ግዛቱ በኩል ካለው የጠላት ምድር መሆኑን አልሳተውም። በዚህም የተነሣ እርሱና እናቱ በቀጥታ ከፈረንሳይ ምድር ተነስተው ወደ ሙስሊሟ አንዱሊሲያ (ደቡብ ስፔይን) ተጓዙ።

አብዱር-ረሕማን ሳልሳዊው የተባለው የአንዱሊሲያ ኸሊፋም ንጉሱንና እናቱን ተቀብሎ በሚገባ እየተንከባከበ አስቀመጣቸው። ከዚያም ቢን-ሻርቸት የተባለውን አይሁዳዊ ሐኪሙ ንጉሱን እንዲያክመው አዘዘለት። የአብዱረሕማንን ቤተመንግስት እንደ ህክምና ማዕከል በማድረግ ንጉስ ሳንቾ ውፍረቱን ሁሉ አራግፎ ቀጭን እስኪሆን ድረስ ሕክምናውን ገፋበት። በመጨረሻም ወደ ሃገሩ ሊዮን በድል አድራጊነት መንፈስ ተመለሰ። ተሚም አንሳሪ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሲጽፍ "ክርስቲያን ንጉስ በሙስሊም መሪ ቤተ መንግሥት ውስጥ በአይሁዳዊው ዶክተር አማካይነት ታከመ። ይህ ነው እንግዲህ የሙስሊም ስፔይን የአብሮነት ሕይወት መገለጫ" ብሏል።

የዲፕሎማሲና የሳይንስ ቋንቋ ሆኖ እንደማገልገሉ፤ አረብኛ ሙስሊም በሆኑትም ሆነ ባልሆኑት ምሁራን ዘንድ የሚመረጥ ለመሆን በቃ። የዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኮርዶባ (ቁርጡባ) ጳጳስ አረብኛ ቋንቋ በካቶሊኮች ዘንድ በስፋት ከመነገሩ የተነሣ ላቲንን እያሸነፈና ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን በመጥቀስ እስከ ማማረር ደረሱ። ጳጳሱ እንዲህ ሲሉም ተደምጠዋል፦ «አንድ ካቶሊካዊ ወጣት በአሁኑ ጊዜ ለጓደኛው በላቲን ቋንቋ ደብዳቤ ለመጻፍ የሚቸገርበት ሁኔታ ላይ ደርሷል። ይሁን እንጂ አረብኛን በሚገባ የሚናገሩ በእርሱ የሚቀኙና ከአረቦች በበለጠ ሁኔታ በቋንቋው የሚራቀቁ በሽበሽ ናቸው።»[30]



ፖርቹጋል በሚገኘው የሶልቭ አልግራቭ ቤተ-መንግሥት ቅጽር ውጭ የቆመ የንጉስ ሳንች ቀዳማዊ ሐውልት።

በአንዱሉሲያ ሰፍኖ የነበረው የሃይማኖት መቻቻል መልካም ሁኔታ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ የሆነ ፖሊሲም ነበር። ሙስሊም መሪዎች በኮርዶባ (ቁርጡባ) ቶሌዶ (ጡለይጢላ) እና ሲቪሊ ያቋቋሟቸው የዕውቀት ማእከላት የቀረው የምዕራብ አውሮፓ ሕዝብ በአድናቆትና በቅናት የሚያስተውላቸው ነበሩ። ሙስሊም እንደሉሲያ (ስፔን) በጊዜው ከነበሩት ኃያላን የምትፈርጅ እንደመሆኗ ከቻይና ጋር በነበራት የንግድ ትስስር አማካይነት ሌላው የአውሮፓ ክፍል ወረቀትን መጠቀም ከመጀመሩ አራት መቶ አመታት በፊት ትጠቀም ነበር። በዚህም የተነሣ በሌሎች ሃገራት ይገኙ የነበሩ አብያተ መጽሐፍት የአንደሉሲያን አብያተ መጽሐፍት ፈጽሞ አይወዳደሯቸውም ነበር። በቁርጡባ ብቻ የነበሩ አብያተ መጽሐፍት በሌሎች ሃገራት ዋና ከተሞች ከነበሩት መጽሐፍት ድምር የሚበልጡና አራት መቶ ሺህ የሚያህል ጥራዞችን ያካተቱ ነበሩ። መስጊድ በጨለማ የብርሃን ወጋገን ፈክቶ ሲታይ።



■ ዘ- መዝኩዊታ ደ-ኮርዶባ በሚል የስፓኒሽ መጠሪያ የሚታወቀው የኮርዶባ (ቁርጡባ) የምሽት እይታ

የጳጳሱ ስጋት ተገቢ ነበር። ምንክያቱም ላቲን እየተዳከመ በሄደ ቁጥር አረብኛን የመሳሰሉ ተወዳጅ ቋንቋዎች የመስፋፋት ዕድላቸው ከፍ እያለ በመምጣቱ ነው። ለምሳሌ ያለ አረብኛ ቋንቋ ታዋቂው ስፔናዊ ደራሲና የዶንኪሆቴ ገጸ-ባሕሪ ፈጣሪ ሴርቫንቴስ አይኖርም ነበር። ያለ ሴርቫንቴስ ደግሞ ዳንቴ የለም። ያለ ዳንቴም ሸክስፒር አይታሰብም።

ያ ዘመን በሙስሊሙ ዓለም የቤተመንግስት ገጣሚዎች የፈኩበት ዘመን ነበር። አንዳንዶቹ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ውብ ግጥሞቻቸውን ለሕዝብ በማቅረብ ገንነው ለመታየት ችለዋል። ከእነዚህ ድንቅ ገጣሚዎች እጅግ ታዋቂ የነበረው ዚሪያብ የተባለው ሲሆን በስምንተኛ መቶ ዘመን ከባግዳድ ከመጣ በኋላ በስነ- ግጥሞቹ ብዙዎች ይመሰጡበትና እርሡን ለመምሰል ይሞክሩ ነበር። ይህ ሰው ለአውሮፓ ነዋሪዎች ሥነ- ግጥሞቹን ብቻ ሳይሆን የጥርስ ሳሙና፣ ዶድራንትና፣ የሚያምር የገበታ ሥርዓትን (ምግቦችን ከፋፍሎና አስውቦ ማቅረብን) ያስተዋወቀ ሰው ነው።

የአውሮፓ የተከበሩ ሰዎች በአብዛኛው የአል- አንደሉሲያን ስልጣኔ በማድነቅ ሥራ በዝቶባቸው ይስተዋሉ ነበር። በተለይም የካስቲል ክርስቲን ናይታስ (Knights) በሙስሊሞች አለባበስ እጅግ በመደነቅ ሞዴሉን ይኮርጁ የነበረ ሲሆን ከሙስሊም ሃገራት የሚመጡ ዶድራንቶችን (መልካም መዓዛ ያላቸው ሽቶዎች) እንዲሁም የአረቢያን ፈረስ እጅግ አድናቂዎች ነበሩ።

የመሰኪመሙ ዓኪም ቄሳሮች

ቀደም ባሉት በዚህ ምዕራፍ ክፍሎች ሙስሊሙ ዓለም ከምዕራቡ ዓለም ጋር ያደረጋቸውን ግንኙነቶች ለማየት ሞክረናል። በተለይም ደግሞ ከሁሉም በበለጠ ሁኔታ ይህን መስተጋብር በስፋት ያደርጉ የነበሩት የኦቶማን ቱርክ መሪዎች ነበሩ። ከእነዚያ መሪዎች መካከል ደግሞ የሱልጣን ሙሐመድ ዳግማዊውን ያህል ከምዕራቡ ዓለም ጋር ትስስር የነበረው መሪ ማግኘት አይቻልም። ኮንስታንቲኖፕል በሙስሊሞች እጅ ከወደቀች በኋላ ሙሐመድ የሮም ቄሳር መሆኑን አወጀ። ምንም እንኳን ይህን ማዕረጉን ግሪኮች ባይቀበሉትም ማዕረጉ ግን መሠረት አልባ ነው ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም መቀመጫውን ኮንስታንቲኖናል አድርጎ የነበረው የቤዛንታይን ኢምፓየር የሮማ ኢምፓየር ቀጥተኛው ወራሽ ነበርና። ሙሐመድ ደግሞ ዝርዮቹ በአብዛኛው ከቤዛንታይን ቤተ መንግስት ከተገኙ ወይዛዝርት ጋር ጋብቻ ይፈጽሙ ስለነበር የደም ትስስር አለን ማለታቸው ተገቢ አባባል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ሙሐመድ ራሱን የአውሮፓ ታላቅ ውርስ ተረካቢ አድርጎ ይቆጥር ስለነበር በሁለመናው ፋሽን ተከታይ ነበር ማለት ያስኬዳል። በጊዜው የነበረውን የዘመነ- ተሃድሶ (Renaissance) ስነ ጥበብ አጥብቆ ይከተል የነበረ ሲሆን ይህንኑ ፍላጎቱን የሚያውቁ የአውሮፓ ነገስታትም ገጽታውን የሚያሳምሩለት የስነ- ጥበብ ሰዎችን ይልኩለት ነበር። ለምሳሌ ከኔፕልስ ኮንስታንዞ-ደ-ፌሬራን ከቬኒስ ደግሞ ቤንትል ቤሊኒን ወደ ሃገሩ በማስመጣት ባለሟል አድርጎ በኦቶማን ቤተመንግስት ለብዙ ዓመታት እንዲቀመጡ አድርጓል።

እነዚህ ጥበበኞች ወደየሃገሮቻቸው ሲመለሱ ኢስላማዊ የሆነውን የቱርካዊያን አለባበስ በተለያዩ ጌጣጌጦች በማስዋብ ለክርስቲያኑ ዓለም አስተዋውቀዋል። ዝነኛቹ የሞናሊዛ ሰዓሊ ሊዮናርዶ ዳ-ቪንቺና ቀራጩ ማይክል አንጀሎም ሳይቀሩ ሱልጣን ሙሐመድን ሃገሩ ድረስ በመሄድ እጅ ነስተዋል።

ይህ አሠራር የኦቶማን ኢምፓየር እስከፈራረሰበት 1920ዎቹ ድረስ ቆይቷል። የዚህ አሠራር አዋጅ የተነገረበት ኦርጅናል ጽሑፍ ዛሬ ፎጂኒካና ቦስኒያ ሄርዜጎቪና ውስጥ በሚገኙ የካቶሊክ ገዳማት ውስጥ በሰነድነት ተቀምጦ ይገኛል። ሱልጣን ሙሐመድ እንዲህ ማለቱ ተጠቅሷል፦

«ከዚኀች መካከል የትኛው ሙስሊም መሆኑን የማውቀው በመስጊድ ሲሆን፤ የትኛው ክርስቲያን መሆኑን በቤተ ክርስቲያን፤ የትኛው አይሁድ መሆኑን ደግሞ በምኩራብ ነው። በእዘቦት ቀን ማን ምን እንደሆነ ለመለየት አይቻልም።»

> የሱልጣን ሙሐመድ ቤተ መንግስት ለሰዓሊያንና ለሥነ ጥበብ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለፈላስፋዎችና ለግሪክ ምሁራን ጭምር ክፍት ነበር። የቤዛንታይን ኢምፓየር ቅርሶች ወደ ሙስሊም ዓለም እንዲዋሃዱ ፍላጎት ስለነበረው የክርስትና እምነት አስተምህሮትን የያዙ መጻሕፍትን በቱርክ ቋንቋ እንዲተረጉሙ አድርጓል። አሁን እኛ ከምንገምተው እጅግ በሰፋ ሁኔታ የኦቶማን ኢምፓየር በተለጠጠ ጊዜ ሱልጣኖች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ (ራስ ገዝ የሆኑ) ሃይማኖታዊ ማሕበረሰቦችን በማቋቋም ሲገዙ ቆይቷል።

የሙሐመድ በፖለቲካ በሳል መሆን ከዚኀች ጋር በአንፃራዊነት መልካም ትስስር እንዲፈጥር ያስቻለው ሲሆን ከመሰሎቹ ጋርም እንዲሁ ጥሩ ግንኙነት (መስተጋብር) እንዲመሠረት ረድቶታል። መቼም



■ ‘ኢንግሊሽ ሮዝ’ የተባለችው ምርጥ ጽጌረዳ ከፋርስ ምድር ተነስታ በንግድ አማካይነት በቱርክ በኩል አድርጋ ወደ እንግሊዝ እንደሄደች ይታመናል።

ቢሆን እያንዳንዱ መሪ ጠላት አያጣውምና ሙሐመድ ዳግማዊም የምዕራቡ ዓለም የሥነ-ጥበብ ሰዎች የሰጡትን ክብር በሚገዳደር መልኩ አንድ ጠላት ተንሣበት። ይህ ሰው ልዑል ብላድ ሳልሳዊ በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን (ድራኩላ ተብሎም ይጠራል) በሱልጣኑ ላይ ቢነሳም ራዱ የተባለው የገዛ ወንድሙ ከሙሐመድ ጎን ሆኖ ጥቃት ከፍቶበታል። በመጨረሻም የቱርኮችን ደም የሚመጥ አውሬ (Vampire) ተደርጎ የተሳለው ድራኩላ ተሸንፎ ኃይሉንና ግዛቱን አጣ።

ቱሊፕ የሚባሉት አበቦች ከሆላንድ ጋር የተሳደረ ታሪክ ያላቸው ቢሆንም በአውሮፓ እንዲታወቁ ያደረጓቸው ቱርኮች ናቸው። በ1554 (ድል) ሱለይማን ዘ-ማግኒፊከንት ወደ ተባለው ዝነኛ የኦቶማኖች ሱልጣን አምባሳደር ሆኖ የተላከው የቀዳማዊ ፈርዲናንድ ዲፕሎማት ባቀረበው ዘገባው ቱርኮች አሁን ‹ቱሊፕ› ተብላ የምትጠራውን ተወዳጅ አበባ ጨምሮ በበርካታ ጽጌዎች ተከብበው እንደሚኖሩ መስክሯል። ሱልጣኑ በየ አመቱ ሃምሳ ሺህ የሚሆኑ የአበባ እምቡጦች እንዲዘጋጁ ትዕዛዝ ይሰጥ ነበር። እንደሚባለው ከሆነ ‹ኢንግሊሽ ሮዝ› በሚል መጠሪያ የምትታወቀው ምርጥ ጽጌረዳ ከፋርስ ምድር ተነስታ በቱርክ በኩል አድርጋ ነበር ወደ እንግሊዝ ያቀናችው።

ምስላዊ ወግ

አደራውን መጠበቅ

ሙስሊሞችና ቁሳዊው ዓለም

የምድር ባለአደራዎች

ኃያሉ አላህ የሰውን ልጅ ሲፈጥረው ምክንያትንና የመሥራትና የመተው ፈቃድን (መሺአን) ሰጥቶታል። ከፍጡራኑ ሁሉ በተለየ ሁኔታ ይህን የሃላፊነት ሸክምና ክብር የተጎናጸፈው ሰው መሆኑ እውነት ነው። ከአሥራ አራት ምዕተ ዓመታት በፊት የአላህ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዮቻቸው ወንዝ ዳር ላይ እንኳን ቢሆኑ ውሃ እንዳያባክኑ መክረዋል። እንዲሁም «አንድ ሙስሊም አዝርዕት አብቅሎ ሰዎች ወይም እንስሳትና አዕዋፋት ቢመገቡት ምጽዋት (ሶደቃ) ይሆንለታል። በዚያ ስራውም ምንዳ ያገኛል» በማለት ተናግረዋል። አንድ ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በአንድ የተራበና አጥንቶቹ በገጠጡ ግመል አጠገብ ሲያልፉ ባለቤቱን እነዚህን ዱዳ (መናገር የማይችሉ) እንስሳት በተመለከተ አላህን ፍራ በማለት አስጠነቀቁት። በዘንዚባር እየተካሄደ ያለውን <ማሳሊ ማሪን ኮንሰርቬሽን ኤንድ ማንግሩቭ ሪሃብሊቴሽን> እንዲሁም በፖኪስታን የሚገኘውና <የካሽሚር ሸለቆ የደን ልማት> የተሰኘውን ንቅናቄ የመሳሰሉት የአካባቢ ልማት ላይ የተሰማሩ ናቸው። እነዚህ ንቅናቄዎች የሚፈጽሙት ተግባር ሁሉ በጥሩ ንያ (እሳቤ) ከተፈፀመ ታላቅ ምንዳ (አጅር) የሚያስገኝ መሆኑ ይታወቃል። ፍጥረተ ዓለሙን ማሰስ (Exploration) ከአምልኮ ተግባር ይቆጠራል። ለአንዳንድ ዘመናዊያን የፍጥረተ ዓለሙን ምስጢራት መመርመርና ፈጣሪን ማምለክ የሳይንሳዊ ምርምርን ደጃፍ መዝጋት ነው። ለሙስሊሞች ደግሞ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው።



■ በታንዛኒያ ሞሆሮ የባሕር ወሽመጥ አንድ መንደርና ረግረጋማ አካባቢ ከአየር ላይ ሲታይ።



ኒሊም የተባለውና በካሽሚር አስተዳደር ስር የሚገኘው ሸለቆ።



በሚስሊ ደሴት የሚገኝ የአካባቢ ጥበቃ ሠራተኞች ተቆጣጣሪ። በዚያ የሚገኘው የአካባቢ ጥበቃ ፕሮጀክት በኢስላማዊ መርሆች ላይ መሠረቱን ያደረገና በዛንዚባር ታንዛኒያ የሚንቀሳቀስ ነው።

ሙስሊሞች ራሳቸውን ለእምነታቸው በማስገዛት ፈጣሪያቸውን ብቻ እያመለኩ ይኖራሉ ማለት አጽናፈ ዓለሙን መመረመራቸውን እርግፍ አድርገው ይተዋሉ ማለት አይደለም። እንዲያውም ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ቁርኣን ሙስሊሞች ፍጥረተ ዓለሙን በአንክሮ እንዲያስተውሉና ይህን ሁሉ ያስገኘ ፈጣሪ ለከንቱ እንዳልፈጠረው እንዲገነዘቡ ያሳስባል።

በኢስላማዊና ዓለማዊ ሳይንስ መካከል ያለው ልዩነት ኢስላማዊ ሳይንስና ምርምር ሁሉንም ግኝቶች የሚመለከታቸው ከመለኮታዊው ኃይል እንደተገኙና ሁሉም ነገሮች በመጨረሻ መመለሻቸው ወደርሱ እንደሆነ አድርጎ መሆኑ ነው። ስለሆነም ማንኛውንም ሳይንሳዊ ፈጠራ ያገኘ ሰው ይህንን ያሳወቀውን ጌታውን ከማመስገን ውጪ ራሱን አይኮፍስም። ቁርኣን እንዲህ ይላል። ‹‹ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር። በምድርም ላይ ተንቦጣረህ አትሂድ። አላህ ተንበጣራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና።›› (ሉቅማን፡ 18)

> «ሙስሊሞች ለእውቀት የነበራቸው ጥማት ሌላው ቀርቶ በሃይማኖት የተመረጡ መሪዎችና ምሁራን ሳይቀሩ ነጻ አስተሳሰብንና ሳይንሳዊ ፍተሻን እንዲደግፉ ያሳሳቸው ነበር።» ሚካኤል ሞርጋን ሎስት ሂስትሪ 2007

በሂሳብ፣ በጠፈር ምርምር በኬሚስትሪ፣ ፊዚክስና ሕምክና ዘርፍ ሙስሊሙ ዓለም ከሰባት መቶ ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ብቸኛው የዓለማችን ሳይንሳዊ ኃይል ሆኖ ቆይቷል።

የተወሳሰቡ ኢስላማዊ የውርስ ሕግጋትን ለማቃለል አል- ኽዋሪዝሚ አል- ጀብራን በአስረኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፈለሰፈ። ይህ ሰው ነው ሎጋሪዝም የሚባለውን የስሌት ዓይነት ያስገኘው። ያለ ሎጋሪዝም የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ እንደማይሰራ ይታወቃል። አሁን ‹ሳይንተፊክ ሜተድ› ተብሎ የሚታወቀውን የስሌት ዓይነት የፈለሰፈው ደግሞ የ12ኛው መቶ ዘመን ሰው አል ሃይተሚ ነው። በርትራንድ ሩሴል የተባለው ዝነኛ የእንግሊዝ ፈላስፋ እንዲህ ማለቱ አያስደንቅም። «ተፈጥሮን በጥልቀት ለመፈተሽ የሚያስችለንን መንገድ ያስተዋወቁን አረቦች ሲሆኑ የሰለጠነው ዓለም መሪዎች በነበሩባቸው ጊዜያት ይህንን በስፋት ተጠቅመውበታል።»

ኢብን ሲና (እንደ አውሮፓውያኑ አጠራር አቪሲና) የተባለው የአስረኛው መቶ ዘመን ፈላስፋና ሳይንቲስት የኡዝቤክስታን ተወላጅ ሲሆን የዘመናዊ ሕክምና አባት የሚለውን ማዕረግ ከጥንታዊው



■ የ10ኛው መቶ ክ/ዘመን ሳይቲንስትና ፈላስፋ የነበረው ኢብን ሲና በታጂክስታን ብሔራዊ ጀግና ተደርጐ ይቆጠራል። ለዚህም ብሔራዊ የመገበያያ ገንዘባቸው ላይ ፎቶግራፉን አኑረዋል።

የግሪክ የሕክምና ሊቅ ሂፖክራቲስ ተረክቧል። ‹ካኖን ኦቭ ሜዲሲን› የተባለው የኢብን ሲና መጽሐፍ በ13 ኛው መቶ ዘመን ወደ ላቲን ቋንቋ ከተተረጎመ በኋላ በአውሮፓ እስከ አስራ ስምንተኛው መቶ ዘመን በስፋት ሲሰራበት ቆይቷል።



■ በኢብን ሲና ‘ካኖን ኦቭ ሚዲስን’ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ገጽ።



ምዕራፍ ዘጠኝ

የወንዶች መንትያ ክፋዮች

“ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ ስመለከት ጠላቶችን ስተከላከልልኝ አስተዋልኩ። ... ከእናንተ ውስጥ ኑሰይባ የፈጸመችውን ጀብዱ የሚፈጽም ማን ነው?”[31] (ነቢዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ)

እኩልነት የሚለው ቃል ትክክለኛ ነውን?

ከሁሉም በላይ ኢስላም አጽንኦት የሚሰጠው ጉዳይ አንድ ሰው ከፈጣሪው ጋር ያለው ግንኙነት የሰመረ መሆንና አለመሆኑን ነው። ከዚያ በኋላ የሚነሳው ጥያቄ ኢስላም ሁለቱም ፆታዎች ከፈጣሪያቸው ጋር በእኩል ደረጃ ግንኙነት እንዲመሠርቱ የሚያስችለው ማዕቀፍ አለውን? የሚለው ነው። ለነዚህ ጥያቄዎች የሚኖረን መልስ “አዎን” የሚል ነው የሚሆነው።

እርግጥ ነው የሰው ልጆች (ወንድና ሴት) ሲፈጠሩ በመካከላቸው የተወሰነ ሥነ-ሕይወታዊ ልዩነቶች አሉ። ወንዶች አካላዊ ጥንካሬ፣ ድፍረትና ነገሮችን ቀድሞ ኃላፊነት በመውሰድ የመከወን ብቃት አላቸው። ሴቶች ደግሞ አካላቸው እንደወንዶች ጡንቻማ አይደለም። እንዲሁም ከወሊድ ጋር በተያያዘ በርካታ ውስብስብ ድክመቶች ጋር አብረው ይኖራሉ። ከዚህ ውጭ ግን ሁለቱም ፆታዎች በፈጣሪያቸውና በሸሪዓ ዓይን እኩል ተደርገው ነው የሚታዩት።

ያንዱ ነፍስ ከሌላው በልጦ የሚገኝበት ወይም ወንዶች ከሴቶች ይልቅ ለፈጣሪያቸው የሚቀርቡበት ሁኔታ የለም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ዘራቸውን ለመቀጠል ሁለቱም ፆታዎች አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ መሆኑ እንዳይጣጠሉና አንዱ በሌላው ላይ የበላይነትን እንዳያሳይ ያደርጋቸዋል። ወደ ኢስላም ታሪክ ስንመጣ ምርጥ የሆኑት ሰሐቢያት ማለትም ኸዲጃ፣ ዓኢሻ፣ ሱመያ፣ ኡሙ ሰለማ፣ ኑሰይባ፣ ኸውላ፣ ኡሙ ሱለይም፣ አስማእ እና ሌሎችም ባይኖሩ ኖሮ የኢስላም ታሪክ ምን ይመስል ነበር? እነዚህ ሴቶች የቁርኣን መልዕክት ሕያው ይሆንና ወደ ሰው ዘር ሁሉ ይደርስ ዘንድ ዘላለማዊ ታሪክ ሠርተዋል።[32]

ነቢዩ ሙሐመድም (ሶ.ዐ.ወ) “ሴቶች የወንዶች መንትያ ክፋዮች ናቸው” ማለታቸው ይህንን ሁሉ አይተውና መገዘው ነው። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በሒራ ዋሻ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ

■ “ሴቶች የወንዶች መንትያ ክፋዮች ናቸው”-ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)

ዋሕይ (ራዕይ) ሲወርድላቸው በጣም ተደናግጠው ነበር። ከዚያ ሁኔታ ይወጡና ይረጋጉ ዘንድ ትልቅ ሚና የተጫወቱት ተወዳጇ ባለቤታቸው ከዲጃ (ረ.ዐ) ነበሩ። ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) "መጥፎ ነገር ይደርስብኝ ይሆን?" ብለው ሲጠይቋቸውም ኸዲጃ (ረ.ዐ) እንዲህ አሉ፦ "አንተ የዝምድናን ትስስር ትጠብቃለህ፣ ለድሆች ቸር ነህ፣ በመከራ ጊዜ ታጋሽና እንግዳ አክባሪ ነህ። ሌሎች መከራ ሲደርስባቸውም ከጐናቸው ትሆናለህ። በአንተ ላይ ፈጣሪህ ክፉ ነገር አያመጣብህም።"[34] ከዚያም ወደርሳቸው የወረደው ሌላ ሳይሆን መልአክ እንደሚሆን በመናገር አጽናኗቸው።

ስለሆነም ከሰው ዘር በሙሉ የመጀመሪያዋ ሙስሊም የመሆንን እጣ የታደሉትና ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ) ከሁሉም የበለጠ የሚያውቋቸው እመት ኸዲጃ (ረ.ዐ) ነበሩ። የሁለት ሰዎች ጥምረት አይቀሬ በሆነው ሞት እስኪቋረጥ ድረስ በመልካም አርአያነቱ ዝንታለም የሚጠቀስ ለመሆን በቅቷል።

ኸዲጃ (ረ.ዐ) በሞት የተለዩበት ዓመትም ለእርሳቸው ክብር ሲባል "የሐዘን ዓመት" ተብሎ ተሰይሟል። ስለሆነም በወርቃማ የታሪክ ብዕር ተከትቦ የሚገኘው፣ ኸዲጃ (ረ.ዐ) ከመላው የሰው ዘር ሁሉ ቀድመው ኢስላምን የተቀበሉ ሴት የመሆናቸው እውነታ ነው። ከርሳቸው ታሪክ የምናገኘው ሌላው ታላቅ ቁምነገር አንዲት ሴት ልጃገረድ ባትሆንና ባል አግብታ የምታውቅ እንኳን ቢሆን ለባሏ የደስታው ምንጭ መሆን እንደሚያቅታት ነው።

ሃብታሟንና የጥሩ ሥነ-ምግባር ባለቤት የሆኑትን ወይዘሮ ካገቡ በኋላ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ፍጹም የተረጋጋና ደስታ የተሞላበት ሕይወት መርተዋል። የመዲና ሰዎች የመጀመሪያውን ቃልኪዳን (ዐቀባህ) ላይ ሊፈጽሙ ሲመጡ ከአሥራ አራቱ ሰዎች መካከል አራቱ ሴቶች ነበሩ። ከእነዚያ ሴቶች መካከል ደግሞ ኑሰይባ (ረ.ዐ) አንዷ ናት።

በቁርአን የተለያዩ አንቀጾች ላይ ወንዶች በአንዳች መልካም ወይም እኩይ ምግባር ከተጠቀሱ ሴቶችም አብረው መወሳታቸው አይቀርም።



አይዳ ቤጊች ስናይጅድ ወይንም "የበረዶ ብናኝ" የተሰኘውና በኦገስት 2008 በተደረገው 14ኛው የሳራዬቮ ፊልም ፌስቲቫል የተመረቀው ፊልም ዳይሬክተር ናት። ይህ ፊልም የ2008 የ "ካንዝ ሂስ ሳምንት ታላቅ ሽልማት"ን ያሸነፈ ሲሆን በዓለም ዙሪያ በተደረጉ የፊልም ፌስቲቫሎች ላይም ለዕይታ ቀርቧል።

ለአብነት ያህል “ሙስሊሞች ወንዶችና ሙስሊሞች ሴቶች፣ ምእመናንና ምእመናትም ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶችም እውነተኞች ወንደችና እውነተኞች ሴቶችም...” (አል-አሕዛብ፡ 35)

የሚለውን የቁርአን አንቀጽ መመልከት ይቻላል። ከዚህም በላይ ሦስተኛውን ትልቁ የቁርአን አንቀጽ “አን-ኒሳእ” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ይህም የሴቶችን ክብር የጨመረ ነው። እንዲሁም የመርየም ምዕራፍ ለሴቶች የተሰጠው መለኮታዊ ግምት የት ድረስ እንደሚርቅ ያሳያል።
ቁርአን እንዲያውም ከዚህም ገፋ አድርጐ እንዲህ ይላል፡-

“በሰማያት ያለው በምድርም ያለው ሁሉ የአላህ ነው። ለሚሻው ሰው ይምራል የሚሻውንም ሰው ይቀጣል። አላህም መሓሪው አዛኝ ነው።” (ኣሊ ዒምራን፡ 129)

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የሃምሳ ዓመት ጐልማሳ ሆነው ሳለ በርካታ ሚስቶችን ማግባታቸው በዖታዊ ፍቅር መሳባቸው ተደርጐ መወሰድ የለበትም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ከዐረቢያ ወጣት ሴቶች (ኮረዶች) የፈለጓትን አማርጠው ማግባት የሚያስችላቸው ሥልጣንና ተቀባይነት ነበራቸው።

ከዓኢሻ (ረ.ዐ) በስተቀር ሁሉም ሚስቶቻቸው አግብተው የፈቱ ባንዱ ወይም በሌላው ምክንያት ጉስቁልናና እንግልት የደረሰባቸው ነበሩ። የአላህ ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) ብዙዎቹን ሴቶች ያገቡት አንድም በጋብቻ ሰበብ የተለያዩ ሰዎችን (አቡበክርና ዑመርን ከመሳሰሉት) ታላላቅ ሰብዕናዎች ጋር ለመተሳሰር አሊያም ደግሞ ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በመሰተር (በመጠበቅና በመንከባከብ) ለተከታዮቻቸው ተምሳሌት ሆነው ለመገኘት ነው። ሂውስተን ስሚዝ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ፡-

“ጦርነት ወንዶችን ከፋኖ በመጉዳት ቁጥራቸውን በማመናመን በርካታ ሴቶችን ያለባልና ያለ ልጅ ያስቀራቸዋል። ሃሳባውያን ይህን ሁኔታ የጀግንነት ተግባር አድርገው ይቆጥሩታል። ይሁን እንጂ ይህ የአብዛኛው ሰው ምርጫ ሊሆን አይችልም” ብሏል።[35]



አስማእ አብዱልሐሚድ የፍልስጤም ዝርያ ያላት ደንማርካዊ ሙስሊም ናት። በ2006 ደንማርክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ሂጃብ የለበሰች የተቪ አቅራቢ ሆናለች። ይህ ውሳኔዋ ብዙ ክርክር ያስነሳ ሲሆን በርካታ የድጋፍ/ተቃውሞ መልዕክቶችንም አስከትሏል። በ2007 ለደንማርክ ፓርላማ ለመወዳደር የወሰነች ሲሆን በቀይ-አረንጓዴ ጥምረት እጩዎች ዝርዝር ላይ 7ኛ ደረጃ ላይ ሰፍራ ነበር።

ይሁን እንጂ እንደ አብዛኛው ሙስሊም ምሁራን አስተያየት ከአንድ በላይ ማግባት የሚበረታታ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አርአያነት እንዳለ ቢሆንም በቁርኣን ከተሰጠው ማስጠንቀቂያ አንጻር ከባድ ኃላፊነቶችን ስለሚያስከትል ነው።

ለምሳሌ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ኸዲጃ (ረ.ዐ) በሕይወታቸው እያሉም ሌላ ያላገቡባቸው ሲሆን ከሞቱ በኋላም እንኳ ለረዥም ጊዜ ሳያገቡ ነበር የተቀመጡት። ይሁን እንጂ የሚቀርቧቸው ዘመዶቻቸው የሆኑ ሴቶች ባደረጉባቸው ግፊት የተለያዩ አማራጮችን አቅርበውላቸዋል።

ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባለቤቶች መካከል በጣም ተወዳጇና ታዋቂዋ ዓኢሻ (ረ.ዐ) ስትሆን ከርሳቸው ሞት በኋላ የመጀመሪያው ኸሊፋ የሆኑት የአቡበክር (ረ.ዐ) ልጅ ናት። ምንም እንኳን በዓኢሻ (ረ.ዐ) እና በነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መካከል ሰፊ የሆነ የዕድሜ ልዩነት ቢኖርም ጥምረታቸውን ምርጥ ከሚባሉት እንዳይሆን አላገደውም። ይሁን እንጂ በዚያ ጋብቻ ዓኢሻ (ረ.ዐ) እድሜዋ ከፍ እስኪል (እንደ አንዳንድ ምሁራን ለአቅመ ሔዋን እስክትደርስ ድረስ) ወደ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ቤት አልገባችም። በዛሬዋ ዓለማችን በአንዳንድ የዩናትድ ስቴትስ ግዛቶች አሁንም ድረስ ከሰባት ዓመት በታች የሆኑ ልጃገረዶች ይዳራሉ።[36]

የዓኢሻ ጋብቻ እጅግ የተባረኩ ከሚባሉት ጋብቻዎች አንዱ ሲሆን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ባሳለፈቻቸው የተቆጠሩ ዓመታት ሁለት ሺህ የሚሆኑ ሐዲሶችን ማስተላለፍ ችላለች። ከነዚህ ሐዲሶች አብዛኛዎቹ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰባዊ ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥኑና እርሷን ከመሰሉ ሰዎች በስተቀር በሌላ በማንም ሊገኙ የማይችሉ ምስጢራትን ጭምር የያዙ ናቸው።

የኢስላምን መልዕክት ወደ ሰው ያደርሱ ዘንድ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የመጀመሪያው መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) በሒራ ዋሻ ሲገለጽላቸው በድንጋጤ ወደ ኸዲጃ (ረ.ዐ) እቅፍ እንደገቡት በሕይወታቸው የመጨረሻ ሰዓቶችም በዓኢሻ (ረ.ዐ) ክንዶች ውስጥ ሆነው ነው ያለፉት።



ፋዲም ኡርጉ ለደች ፓርላማ መመረጥ ከቻሉ የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ናት። ወደ ፖለቲካ የገባችው በ 15 ዓመቷ የኔዘርላንድ ሊበራል ፓርቲ ውስጥ ለኢኮኖሚያዊ ነጻነት የሚሰራ የሴቶች ቡድን በማቋቋም ነው።

በባልና ሚስት መካከል የሚኖር መቀራረብ

ቀድሞ እንደ ርክሰት የሚታይ የነበረን ጉዳይ በሚገርም ሁኔታ የተቀደሰ ማድረግን ምናልባትም የትም ቦታ አናገኘውም። በኢስላም የሁለት ተጓዳኞች ግንኙነት ማማር በትዳር ውስጥ ወሳኝና ውብ የሆነ ጉዳይ ተደርጎ ነው የሚታየው። እንዲያውም ነገሩን ገፋ አድርገን ካየነው ወንድ ልጅ ከባለቤቱ ጋር የሚያደርገው ወሲባዊ እርካታ ሳይቀር እንደ ሶደቃ (ምጽዋት) እንደሚቆጠር ተጠቅሶ ይገኛል።[37] ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ወንዶች ከባለቤቶቻቸው ጋራ ልክ እንደ እንስሳ ዝም ብለው ግንኙነት እንዳያደርጉና በመደባበስና በመሳም እንዲያሟሙቋቸው ሁሉ ማበረታቻ ሰጥተዋል።[38]

በእርግጥ በባልና ሚስት መሀከል የሚገኝ ወሲባዊ እርካታና ፍቅር በኢስላም እንደተቀደሰ ተግባር መቆጠሩ ሁሌም እንደ አኩሪ ተግባር የሚታይ ነበር ማለት አይቻልም። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሙስሊሞች ከምዕራቡ ዓለም ሴኩላራዊ ባህል ጋር አብረው እንደማይሄዱ ብቻ ሳይሆን በጣም ስሜታዊና ዓለማዊ እንደሆኑ አድርጎ በማንኳሰስ የማቅረብ ሁኔታ ነበረ።

ለመሆኑ ከኢስላም ውጭ ምን ዓይነት ሃይማኖት ነው ባል ሚስቱ ጋር ወሲባዊ ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት የፈጣሪውን ስም እንዲጠራና (ቢስሚላህ) ከሰይጣን ርክሰት እንዲጠብቀው እንዲማጸን የሚያዘው? እንዲሁም ወሲባዊ እርካታንስ ምንዳ (አጅር) እንደሚያስገኝ ጉዳይ የሚቆጥርስ ሃይማኖት የቱ ነው? ባልና ሚስት እጃቸውን ሲጨባበጡ ወንጀሎቻቸው ከጣታቸው መካከል እንደ ውሃ ጠብታ እንደሚንጠባጠቡ የሚቆጥርስ የትኛው እምነት ነው? ጀነት በመንፈሳዊ ሽልማት ብቻ ሳይሆን በቁሳዊ ሽልማቶችም ቁምር የተሞላች እንደሆነች በግልጽና ያለምንም ሃፍረት የሚናገርስ የትኛው ሃይማኖት ነው?



ዩሉድ አልፊቂህ በፍልስጤም ግዛት ውስጥ ወንዶች ብቻ የተቆናጠጡትን የኢስላማዊ ህግ ዳኝነት ጥሳ መግባት የቻለች የመጀመሪያዋ የዘመናችን ሴት ናት። በስተመጨረሻም ለአዲስ ዳኞች በተዘጋጀው ፈተና ከሌሎች ሴቶች ጋር በመሆን ከፍተኛ ውጤት በማምጣት በሃላፊነት ልትቀመጥ ችላለች።

በምዕራቡ ዓለም የሴቶች መብት የተከበረው ከብዙ ረዣዥምና ከባድ ፍልሚያዎች በኋላ ነበር። በስልጣን ላይ የነበሩት አካላት እነዚህን መብቶች ያለፍላጎታቸው ወቅቱ የፈጠራቸው ለውጦች የግድ ስላደረጉባቸው የሰጧቸው ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) ግን ከዚህ በተለየ መልኩ በተለይ ደግሞ በመጨረሻው ወህይ ፖለቲካዊ ከባቢው እስኪበስል አይጠብቅም። በኢስላም ለወንድም ሆነ ለሴት የተሰጡት መብቶች ልዩ የሆኑና ተለዋዋጭ ከሆነው የህዝባዊ አስተያየት ማዕበል ጋር የተቆራኙ አይደሉም።

> "ሐዲስን እየፈበረኩ የሚያስፋፉ በርካታ ወንዶች ነበሩ። ነገር ግን በኢስላም ታሪክ አንዲትም ሴት ሐዲስ በመፈብረክ ተወንጅላ አታውቅም።"
>
> -ኢማም አዝ-ዘህቢ
> በዶ/ር ሙሐመድ አክረም ነደዊ እንደተጠቀሰው፣
> ኤ ግሊምፕስ አት ኸርሊ ዉሜን ኢስላሚክ ስኮላርስ

የሴቶች መብት ንቅናቄዎች በሙስሊም አገራትም ይሁን ምዕራቡ ዓለም በሚገኙ ሙስሊም ማህበረሰብ አባላት መካከል ይገኛሉ። ነገር ግን ጠርዘኛና ሙሉ በሙሉ የምዕራቡን ዓለም የሴቶች መብት ንቅናቄ ዘይቤ የተከተሉ አቀንቃኞች ሚና አናሳ ነው። በሌላ በኩል በኢስላማዊው ባህል ማዕቀፍ ውስጥ የተፈጠሩ የሴቶች ቡድኖች በቁርአንና በሱንና እንዲሁም ለዘመናት ተዘንግተው የቆዩ ጀግና እንስቶችን ባፈራውን የሃይማኖት መንፈስ ውስጥ ወደተደነገጉት የሴቶች መብቶች መመለስ እንደሚያስፈልግ የሚደረገው እንቅስቃሴ ፈጣን እድገት እያሳየ ነው።

አሁንም በሙስሊሙ ዓለም የሴቶች መብቶችን አስመልክቶ መሰራት ያለበት በርካታ ስራ አለ። ነገር ግን ሙስሊም በሚበዛባቸው አገራት የሚገኙ ሴቶች በርካታ ብሶቶች ያሉባቸው ቢሆንም እነዚህ ብሶቶች የምዕራቡ ዓለም ከሙስሊም ሴቶች ጋር ጥቅል በሆነ ሁኔታ አያይዞ ከሚያነሳቸው ጉዳዮች ይለያሉ። አቅም ያለመጎልበት፣ ትምህርት እጦትና የገንዘብ ጥገኝነት ከሴቶች በላይ ባይሆንም ወንዶችም ላይ ጭምር የሚደርሱ ችግሮች እንደመሆናቸው ውጤት ማምጣት ከተፈለገ ጉዳዩን ሰፋ ባለ ኢኮኖሚያዊ ማዕቀፍ ውስጥ መያዝ ይፈልጋል።

አንዳንድ ሰዎች እያንዳንዱ ጾታ አንዱ ከአንዱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዳለ ሆኖ ነገር ግን በራሱ የተሟላ መሆኑን በመግለጽ "የመንትያ ክፋዮች" የሚለውን አመለካከት ሊቃወሙ ይችላሉ። ምንም እንኳን አንድ ወንድና አንዲት ሴት በተናጠል የተሟሉ መሆናቸው የማያሻማ ቢሆንም እንደ ህብረተሰብ ግን ወንዶችና ሴቶች በተናጠል የተሟሉ ሊሆኑ አይችልም።

> "ኢስላም ሴቶችን የወንዶች መንፈሳዊ እኩያዎች አድርጎ ይመለከታል። ይህ ማለት ግን ሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ጭቆናና ሌሎችም ስራዎቻቸውን በኢስላም ሽፋን የሚሰሩ ሰዎች የሉም ማለት አይደለም።"
> ዶ/ር ኢንግሪድ ማትሰን

ምዕራፍ አሥር


ምስላዊ ወግ፦ ኢስላምና ባሕል

በዴንማርክ ኤም ቲቪ የሚቀርበውን የላቀ ብቃት ሽልማት ያሸነፉት አውትላንዲሽ የተባለው ባንድ አባላት መንፈሳዊና ማሕበራዊ ጉዳዮችን እያነሱ በኪነ-ጥበባዊ ሥራዎቻቸው ያቀርባሉ አንድ የታወቀ አሜሪካዊ ሙስሊም መምህር ሥራዎቻቸውን "የሚደነቁ ናቸው" በማለት ወጣት ሙስሊሞች በሶላቶቻቸው ላይ እንዲጸኑ መገፋፋታቸውን አወድሷል።





■ ናጂ ኑርዲን የታወቀ የዐረብኛ የቁም ጸሐፊ (Calligrapher)





የመንፈሳዊ ነጸብራቅ ምንጭ በዘመናችን የሚገኝ ቁርኣናዊ ሥነ-ጥበብ

ሥነ-ጥበብንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የምሉዕነትና ውበት ምንጭ የሆነውን ቁርኣን ለእይታ ለማቅረብ የሚጥረው ኤዲቶ ኤሌክቶርን የተባለው ኩባንያ ኢስላማዊ ጥበባትን ጠብቆ በማቆየት ረገድ የተዋጣለት ሆኗል። ይህ ቡድን በጣም የተዋቡ ቁርኣናዊ የቁም ጽሑፎችን በመምረጥ በዲጂታልና ጂኦሜትሪ ጥበብ በመታገዝ የተራቀቀ ሥራ ማቅረብ ተሳክቶለታል።

ቡድኑ ይህን ፕሮጀክት የመካከለኛውን ዘመን አንጡራ ቋንቋዊ ውበት ብቻ ሳይሆን እጅግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አዳዲስ ዲዛይኖችን እንዴት መሥራት እንደሚችል ለማሳያነት ተጠቅሞበታል። ይህ ሥራ በመላው ዓለም በርካታ ጐብኚዎችን ስቧል። ቁርኣን የምንጊዜም የውበት ምንጭ በመሆን ሙስሊሞችን ለፈጠራ ሥራና ዕደ ጥበብ ያነሳሳቸዋል።


Entering the Islamic Spirit

ምዕራፍ አሥራ አንድ

ፍትሕ እና ሰላም በኢስላም

ሰላም ማለት በኢስላም በማኅበረሰቡ ውስጥ ጭቆናና ሙስና አለመኖርና የፍትህን መስፈን የሚያመለክት ሁኔታ ነው። ይሁን እንጂ ኢስላም ሰላም የሚገኘው ጦርነቶችን ሁሉ በመተውና በመወያየት ብቻ ነው ብሎ አያምንም። ምክንያቱም የዓለም ታሪክ ያስተማረን ሁልጊዜም ቢሆን ሰላም፣ ፍትሕና መልካም ነገር የማይገዛቸው ጭቆናንና የንጹሐንን ሞት የሚያስፋፉ ኃይሎች እንዳሉ ነው።

ስለሆነም የኢስላም ሥነ-ምግባር አስተምህሮት የሚያሳየን የንጹሐን ሙስሊሞችን ንብረት ክብርና ደም ለመጠበቅ፣ አምባገነኖችን ለማንበርከክና ተጽዕኖአቸውን ለመግታት ግጭት ውስጥ መግባት የግድ የሚሆንባቸው ክስተቶች ያሉ መሆኑን ነው። ይህ ሁኔታ የሙስሊሙ ኡምማ በጦርነቶች ውስጥ ሲገባ ሊከተላቸው የሚገባቸውን መርሆች በሚገባ እንዲቀርጽ አስችሎታል።

ሰላምን ከሚሰፈን የሚከፈል ቤዛ

ጦርነትና ግጭት በሚከሰቱባቸው ጊዜያት ሙስሊሞች የሚያራምዷቸውን ፖሊሲዎች በተመለከተ ለምዕተ ዓመታት ጥንቃቄ የተሞላባቸው ስልቶች፣ ውይይቶችና ክርክሮች ሲካሄዱ ቆይተዋል። የሙስሊሞች አዛዥ የነበሩት ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ግጭቶችና ጦርነቶች በሚከሰቱባቸው ጊዜያቶች መከተል ስለሚኖርባቸው የሥነ-ምግባር መርሆች ሙስሊሞችን በየጊዜው ያስተምሩ ነበር። ስለሆነም ከአላህ መጽሐፍ ከቁርአን ቀጥሎ የምንከተለው የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) ሱንና እንደመሆኑ የርሳቸውን ፈለግ መያዝ ግድ ይለናል ማለት ነው። በዚሁ መሠረት በዘመናችን እዚህም እዚያም በሙስሊሙ ስም የሚፈጸሙ ደም አፋሳሽ ግጭቶችም መቃኘት የሚኖርባቸው ከቁርአንና ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ፈለገ ሕይወት አንጻር መሆን ይኖርበታል።

እናም ቁርአን ሰላምን የማስፈን ዓላማ ባነገበ ግጭት ውስጥ ሙስሊሞች ምን ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያዎችን አስቀምጧል። ከሓዲያኑ ሙስሊሞቹን ለዓመታት ሲያሰቃዩዋቸውና መከራቸውን ሲያባዩዋቸው ከቆዩ በኋላ እንደገና የከፋ ማዕቀብ ጣሉባቸው። ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ሙስሊሞች እንዲዋጉ አልተፈቀደላቸውም። በመጨረሻ ግን በሚከተለው አኳኋን ራሳቸውን እንዲከላከሉ መለኮታዊ

■ ጋዜጠኛ፣ ደራሲና የጦርነት ዘጋቢ ሆነው ክሪስ ሄጅስ ቶሮንቶ ካናዳ በተካሄደው "ሪቫይቪንግ ዘ ኢስላሚክ ስፕሪት" ኮንፈረንስ ላይ ንግግር እያደረገ።



■ ህንዳዊ ሙስሊም አስር ቀን በሚቆየውና በህንድ ቦምቤይ በተደረገው ኢስላማዊ የሰላም ኮንፈረንስ መክፈቻ ላይ።

መመሪያ ወረደላቸው፡- (ያታልሉህም ቢፈልጉ አላህ በቂህ ነው።እርሱ ያ በእርዳታውና በምእምናን ያበረታህ ነው።) (አል-አንፋል፡ 61-62)

"ለእነዚያ ለሚገደሉት (ምእመናን) እነርሱ የተበደሉ በመሆናቸው (መዋጋት) ተፈቀደላቸው። አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥም ቻይ ነው። እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት (ተፈቀደ)።" (አል-ሐጅ፡ 39-40)

ጦርነትን የሚመለከቱ የቁርኣን አንቀጾች ላይ ሙስሊሞች የትና እንዴት ኃይልን መጠቀም እንዳለባቸው እንዲሁም ወረራን እንዴት እንደሚገቱ ያወሳሉ።
ለምሣሌ፡- "ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፤ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት፤..." (አል-በቀራህ፡ 191)

ይሁን እንጂ ከሐዲያኑ ከጦርነትና ከግጭት የሚታቀቡ ከሆነ ሙስሊሞችም ከተመሣሣይ ድርጊት እንዲቆጠቡ በሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ ታዟል፡-

> ሌላው ቀርቶ ጨካኝ (አምባገነን) በሚባሉ ሙስሊም መሪዎች ሥር የነበሩ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በሙስሊሙ ግዛት ስር ተጽዕኖአቸው እንዳለ የቆየ ሲሆን ሃይማኖታዊ ነፃነታቸውም አልተሸራረፈባቸውም።"
> ሂውስተን ስሚዝ 'ኢስላም ኤ ኮንሳይስ ኢንትሮዳክሽን

"ሁከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተዋጓቸው፤ ቢክከለከሉም፥ ወሰንን ማለፍ፥ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)።" (አል-በቀራህ፡ 193)

የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በጦርነቶች ውስጥ ሲቪሎች እንዳይጐዱ በጽኑ ይከላከሉ ነበር። እንደ አጠቃላይ ጦርነቶችን በአነስተኛ የሕይወትና የገንዘብ ኪሣራ ማሸነፍ ትልቅ ቦታ የተሰጠው ሲሆን ምድርን ማበላሸት ደግሞ ፈጽሞ የተወገዘ ተግባር ነው።

የታላቁ መምህራቸውንና ጓደኛቸውን ምክር ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ያደረጉት ኸሊፋው አቡበክር አስ-ሲዲቅም (ረ.ዐ) እንዲሁ ወታደሮቻቸውን ወደ ጦር አውድ ከመላካቸው በፊት እንዲህ የሚል ምክር ይለግሷቸው ነበር፡- "አታላይ፣ ከዳተኛና ቂመኛ አትሁኑ። የጦር ጉዳተኞችን አካላት አትቀራርጡ። ሕፃናትና፣ አረጋውያንንና ሴቶችን አትግደሉ። የቴምር ዛፎችንና አትክልቶችን አታቃጥሉ አትቁረጡ። በጐችን፣ ላሞችን፣ ግመሎችን ለምግብነት ካልሆነ በቀር አትግደሉ። እንዲሁም በዋሻ፣ በቤተክርስቲያንና በምኩራቦች ውስጥ የምታገኙዋቸውን ሰዎች ለተመሠጡበት ነገር ተውዋቸው።" የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አዛኝ የሆነ ተፈጥሮ የምንገነዘበው እንደዚያ መከራቸውን ያበሏቸውንና ቁምስቅል ያሳዩዋቸውን ከሐዲያን መካ የተከፈተ ዕለት ከፊት ለፊታቸው ሲመለከቱ የተናገሩትን ስናስብ ነው። "ሂዱ ዛሬ በእናንተ ላይ ወቀሳ የለባችሁም" ነበር ያሏቸው።[39]

የፍትሕን መንገድ መከተል ከእኛ ተጨባጭ ጋር ሲገናዘብ

የኢስላም ፀሐይ ከወደ ሒጃዝ ኮረብቶች በኩል ሲፈነጥቅ በዐረቢያ ምድር የነበሩ ጐሣዎች በትንሽ በትልቁ ጉዳይ ሁልጊዜም ይቆራቆሱ ነበር። አንዳንድ ጦርነቶች እጅግ ከመራዘማቸው

የተነሣ ከየጐሣው የቀሩ ጐበዛዝት ቁጥር እጅግ አናሣ ነበር ማለት ይቻላል። በዚያ ሁኔታ ነው እንግዲህ ቁርአን የወረደውና የመጀመሪያው ኢስላማዊ ማሕበረሰብ የተፈጠረው። ከዚያም የኢስላም ክንፎች በየአቅጣጫው ሲዘረጉ በርካታ ግዛቶች (ኢምፓየሮች) ለመመስረት በቅተዋል።[40]

ቀደምት ሙስሊም ምሁራን ምድርን ለሶስት በመክፈል የሚከተለውን ትንታኔ ሰጥተዋል፦ የመጀመሪያው ሙስሊሞች ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩትና ኢስላምን በሁለንተናው ለመተግበር ያልተሸራረፈ ነፃነት የሰፈነበት ምድር ነው። ሁለተኛው እንደ ሃበሻ ምድር ያሉ ሃገራት ሲሆኑ ምንም እንኳን ሙስሊሞች አመራሩን ባይጨብጡም ኢሰላምን ለመተግበር ግን አልተከለከሉም።
ሶስተኛው ደግሞ ለሙስሊሞች ጠላትነት ያላቸው ሕዝቦች የሚኖሩበትና የሃይማኖት ነፃነት የሌለበት ነው። መጨረሻ ላይ የተጠቀሰውን ምድር በተመለከተ ሙስሊም ተዋጊዎች በየጊዜው ባደረጓቸው ተጋድሎዎች ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ ወደ አንደኛው ወይም ሁለተኛው ምድብ እንዲገባ ለማድረግ ጥረዋል። በዚህም ጥረታቸው ረድኤት ሙስሊሞች ነፃነታቸው ተከብሮና ፍትሕን አግኝተው የሚኖሩበት ሁኔታ በየማዕዘናቱ ተፈጥሯል። እንግዲህ በእንዲህ ዓይነት ምድር ነው ጦርነት እጅግ የማይፈለግና የሚጠላ ቢሆንም እንኳን አይቀሬ ሆኖ የሚገኘው።[41]

እነዚህ ግጭቶች (ጦርነቶች) ምንም እንኳን የተፈቀዱ ቢሆኑም ቁርአን ግን እንደማይበረታቱ በሚከተለው አኳኋን ይገልፃል፦

"ወደ ዕርቅም ቢያዘነብሉ ወደ እርሷ አዘንብል። በአላህም ላይ ተጠጋ። እነሆ እርሱ ሰሚ ዐዋቂ ነውና። የሙስሊሙ ሠራዊት አሸናፊ ሆኖ አካባቢውን ሲቆጣጠር በዚያ መቆየት የሚፈልጉ ሰዎች (የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች) በአዲሱ ኢስላማዊ መስተዳድር ሥር የንብረት፣ የሕይወትና የአምልኮት ነጻነታቸው ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ይሆናል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ሙስሊሞች የሚከፍሉትን ዘካ ሰለማያወጡ ለጥበቃ ዋስትናቸው 'ጂዝያህ' የሚባል የጥበቃ ታክስ እንዲከፍሉ ይደረጋሉ። ጂዝያህ የሚከፍል ማንኛውም ሙስሊም ያልሆነ ዜጋ ሙስሊሞች በሚሳተፉባቸው ውጊያዎች የማይካፈል ሲሆን መስተዳድሩ ተገቢ ጥበቃ የማያደርግለት ሆኖ ሲገኝም የከፈለው ታክስ ይመለስለታል።

እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ በሁለተኛው ኸሊፋ በዑመር ኢብን አል ኸጣብ (ረ.ዐ) የአስተዳደር ዘመን እንደተከሰተ ታሪክ መዝግቦታል። ዑመር (ረ.ዐ) በሶሪያ የሚገኙ ክርስቲያን ዐረቦችን ከቤዛንታይኖች ጥቃት ሊጠብቋቸው ስላልቻሉ ከእነርሱ የሰበሰቡትን የጂዚያ ገንዘብ መልሰውላቸዋል።

ፍትሕ የሰላም ዋልታ ነው

ኃያሉ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፦
(እናንተ ያመናቹ ሆይ! ፍትህን አስፍኑ። ለአላህ ስትሉም (በእውነት) መስክሩ፤ በራሳችሁ፤ በወላጆቻቹ ወይም በቅርብ ዘመዶቻችሁ ላይም ቢሆን እነኳ። አላህ ለነርሱ ከናንተ ይበልጥ ቅርብ ነው (ያስባልና)። ስሜትን አትከተሉ በደል እንዳትፈጽሙ። (ፍትህን) ብታዛቡ ወይም (ፍትህን ከማስፈን) ብትሸሹ፤ አስከፊ ቅጣት ይጠብቃቹኃል። አላህ የምትሰሩትን ጠንቅቆ ያውቃልና)።(አን-ኒሳእ፣ 135)

ሰላምን ለማምጣት የሚደረገው ፍትሕን የማስፈን ሂደት አንዳንድ ጊዜ ኃይልን መጠቀምን ግድ ይላል። በዛሬዋ ዓለማችን ብዙ ሙስሊሞች የፍትሕን መታጣት አስመልክተው ተቃውሟቸውን በብዙ መንገዶች

እያሰሙ ይገኛሉ። በ2003 (እ.ኤ.አ) በሳኡድ አረቢያ የተደረገ የዘጋቢ ጥናት መሠረት መጠይቅ ከተደረገላቸው ሰዎች 99 ከመቶ የሚሆኑት በሲቪሎች (ሰላማዊ ሰዎች) ላይ የሚደረጉ ጭቆናዎች እንዳልተወገዱ ተናግረዋል። [42]

በአሁኑ ጊዜ በሲቪል ሕዝቦች ላይ የሚፈጸሙ የሽብር ድርጊቶችን የሚቃወሙ ድርጅቶች ቁጥር በርካታ ነው። በአሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ስፔይን፣ ኢራቅ፣ አፍጋኒስታንና በሌሎች ሃገራት የሚኖሩ ሙስሊሞችና ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያሰሙ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ ታላላቅ የሚባሉ የዓለማችን ኢስላማዊ ተቋማት ሽብርተኝነትን በማውገዝ ፊታውራሪነቱን ይዘዋል። ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል 'ኦርጋናይዜሽን ኦፍ ኢስላሚክ ኮንፈረንስ' እና በዩናይትድ ስቴትስና በሌሎች ሃገራት የሚገኙ ዋና ዋና ኢስላማዊ ተቋማት ይገኙበታል።

በስፔን የሚገኘው 'ኢስላሚክ ኮሚሽን ኦፍ ስፔን' የተባለው ድርጅት መሪ በመቶዎች ከሚገኙና ሽብርተኝነትን ከሚቃወሙ ኢማሞች መካከል አንዱ ሲሆኑ ሼኽ መንሱር አስኩድሮ ይባላሉ። እኚህ ኢማም በሰጡት አስተያየት በስፔን አሸባሪዎች ያደረሱት ጥፋት ከኢስላም አስተምህሮት ፍጹም ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መሆኑን ከገለጹ በኋላ እንዲህ ብለዋል፦ "ከእነዚህ ቡድናት ወይም ከሌሎች የብቀላ እርምጃ ቢሰነዘርብኝ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ። ከአላህ ውጪ ማንንም አልፈራም። እርሱ ከሁሉም የተሻለ ጠባቂ ነውና።" [43]

ምዕራፍ አሥራ ሁለት


ሙስሊሞች በዛሬው ዘመን
ሕዝብ ነክ መረጃዎችና ባሕል

ከጥንቷ የኢስላማዊ ስልጣኔ መነሻ መዲና የፈነጠቀው የኢስላም ብርሃን በዓለማችን የነገሰውን ጽልመት እየገፈፈ ከሞሮኮ ጫፍ እስከ ቻይና ደጃፍ ያለውን ምድር አዳርሷል። በሶስቱ ክፍለ ዓለማት ማለትም በአፍሪካ አውሮፓና እሲያ ሙስሊሞች ያሉባቸው በርካታ ቋንቋ የሚናገሩ ማሕበረሰቦች ይገኛሉ። ዛሬ ምድራችን የሙስሊሞች ቁጥር 1.3 ቢሊዮን እንደሚሆን ይገመታል። ይህ ማለት ከእያንዳንዱ አምስት ሰዎች አንዱ ሙስሊም ነው ማለት ይሆናል።

አሲያ

ኢስላም ወደ ኢንዶኒዢያ የገባው በሕንድ ነጋዴዎች አማካይነት በአስራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ነው። ከዚያም በጃቫና ሱማትራ ሃይማኖቱ በእጅጉ ተስፋፋ። ዛሬ ከኢንዶኖዢያ ሕዝብ 90 ከመቶ የሚሆነውና ከሁለት መቶ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ሙስሊም መሆኑ ይታወቃል። ይህም ኢንዶኒዢያ በርካታ ሙስሊሞች የሚኖሩባት የመጀመሪያዋ ሃገር እንድትሆን አስችሏታል። በኢንዶኔዢያ ምድር አነስተኛ ሙስሊሞች የሚኖሩት በባሊ ደሴት ሲሆን ቁጥራቸው አስር በመቶ ብቻ ነው። የቀሩት የደሴቷ ነዋሪዎች ሂንዱዎች ሲሆኑ ቁጥራቸው ሶስት ሚሊዮን ይሆናል። ፓኪስታን፣ ሕንድ፣ ባንግላዲሽና ኢራን በርካታ ሙስሊሞች የሚኖሩባቸው የእሲያ ሃገራት ናቸው። በማሌዥያም ቢሆን ሙስሊሞች አብዛኛውን ቁጥር ይዘዋል። ይኸውም 60 ከመቶ (አሰራ አምስት ሚሊዮን) ነው።





አውሮፓ

ኢስላም በደቡባዊ አውሮፓ በኮሚኒስቶች አስተዳደር ወቅት በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳልነበር ይታወቃል፥ ኮሚኒስቶች በተፈጥሯቸው ማንኛውንም ሃይማኖት ስለማያበረታቱ ኢስላምን ያጋጠመው እጣ ፋንታም የተለየ አልነበረም። በአልባኒያ፣ ቦስኒያ ኮሶቮ ሙስሊሞች በየተራ 70፣ 60 እና 90 ከመቶ የሚሆን ቁጥር ይሸፍናሉ። ከሌሎቹ የአውሮፓ ሃገራት በተለየ መልኩ ሞንቴኔግሮ፣ ሜቄዶኒያ፣ ሩሲያ፣ ቡልጋሪያና ፈረንሳይ ከ10 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝባቸው ሙስሊም እንደሆነ ይታወቃል። በተለይም በፈረንሳይ ሙስሊሞች በበቂ ሁኔታ የአናሳነት (minority) ደረጃን ተጐናጽፈዋል። በጀርመን ደግሞ ከ2.5 ሚሊዮን በላይ ቱርኮችና ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ኩርዶች ይኖራሉ። ከተለያዩ ሃገራት የመጡና የሃገሬው ሙስሊሞች (ኢስላምን የተቀበሉ ጀርመናውያን) ሲታከሉበት ከጀርመን ሕዝብ ከ4-5 ከመቶ የሚሆነው ሙስሊም እንደሆነ ይገለፃል።

በዩናይትድ ኪንግደም ሙስሊሞች ወደ 2.8 ከመቶ የሚሆነውን የሕዝቧን ቁጥር የሚሸፍኑ ሲሆን ጐላ ብለው የሚታዩ አናሳዎች (minorities) ለመሆን ችለዋል። በኔዘርላንድ፣ በግሪክ፣ በቤልጂዬምና በስካንዲኔቪያ ሃገራትም ሙስሊሞች ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይታያል።







አፍሪካ

ኢስላም ገና እንደተወለደ ወደ አፍሪካ የገባበት የመጀመሪያዋ ሃገር አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) ናት። ሕዝባቸው ሙስሊም እንደሆነ የሚታወቁት ሃገራት የሰሜን አፍሪካዎቹ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ቱኒዚያ፣ ግብጽ፣ ሊቢያ፣ ሞሪታኒያ ሲሆኑ ሱዳን፣ ቻድ፣ ኒጀር፣ ናይጄሪያ፣ ሴኔጋል፣ ቡርኪናፋሶ፣ ጊኒ፣ ኮትዲቫር ሌሎችም አብዛኛው (Majority) ሕዝባቸው ሙስሊም ነው። ሶማሊያ፣ ጁቡቲና ኮሞሮስ ደሴቶች 97 ከመቶ የሚሆነው ሕዝባቸው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነው። ዛንዚባር፣ ታንዛኒያ፣ ኬኒያና ኡጋንዳም የበርካታ ሙስሊሞች መኖሪያ መሆናቸው ይታወቃል። ማሊን በተመለከተ የጥንታዊቷ ኢስላማዊ ስልጣኔ እንብርት ቲምቢክቱ መገኛ ስትሆን ማንስ ሙሳ የመሳሰሉ ገናና መሪዎችን አፍርታለች።







አሜሪካ

በአሜሪካ የኢስላም ታሪክ ገና እየተመረመረና እየተፃፈ ይገኛል። የሰው ዘር፣ ታሪክና ባሕልን የሚያጠኑ ተመራማሪዎች (anthropologists) ራቅ ባለ የኔቫዳና ቴክሳስ ምዕራባዊ ግዛቶች ሙስሊሞች የኖሩባቸውን ሥፍራዎች አግኝተዋል። የዛሬው የአሜሪካ ሙስሊሞች ሁኔታ በየዕለቱ ይቀያየራል ማለት ይቻላል። ይህም ብዙ ሰዎች ኢስላምን የሚቀበሉ በመሆናቸውና ከተለያዩ ሙስሊም ሃገራት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወደ አሜሪካ ስለሚገቡ ነው። በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሜሪካ ሙስሊሞች ከተለያዩ ብሔራት የተዋቀሩና የአንድ ብሔር ወይም ሕዝብ የበላይነት የማይጫናቸው ሊሆኑ ችለዋል። ሙስሊሞች እዚህ አሜሪካን ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጡት የባሪያ ንግድ በተስፋፋባቸው ዘመናት (መቶ ዓመታት) ነው። በእነዚያ ጊዜያት በሺዎችና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከአፍሪካ ምድር በባርነት እየተፈነገሉ ወደ አዲሱ ዓለም ገብተዋል። አፍሪካ አሜሪካውያን ዛሬም ድረስ በሃገረ አሜሪካ ካለው የሙስሊሞች ቁጥር አንድ ሶስተኛ የሚሆነውን ይሸፍናሉ። በአሜሪካ የሚገኙ ሙስሊሞች እንደ አጠቃላይ ከሌሎች የሃይማኖት ቡድኖች በተሻለ ሁኔታ የተማሩ ከማሕበረሰቡ ጋር የተዋሃዱና ከሌሎቹ የአውሮፓ መሰሎቻቸው ይበልጥ። ለሃገራቸው (አሜሪካ) ራሳቸውን የሰጡ ናቸው።




I
NY



ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ኢስላም እና ዘመናዊው ዓለም

ኢስላም ከዘመናዊው ዓለም ጋር አብሮ የሚራመድ ሃይማኖት ነውን? ለዚህ ጥያቄ መልስ፤ አይደለም! የሚል ቢሆን ኖሮ ምን ሊፈጠር ይችላል? በዚህ መጽሐፍ ቁጥራቸው 1.3 ቢሊዮን እንደሚደርስ የተነገረላቸው ሙስሊሞች እምነታቸውን እየተገበሩ መኖር ይችሉ ዘንደ ሌላ ምድር ወይም አጽናፈ ዓለም ማፈላለግ ይኖርባቸዋልን? ነው ወይንስ ለሃይማኖታቸው ሕግጋት ጀርባቸውን ይሰጡ?

ይበልጥ ምክንያታዊና ገንቢ በሆነ ሁኔታ ይህን ጥያቄ ለማስቀመጥ ሙስሊሞች በዘመናዊው ዓለም ውስጥ በምን መልኩ ነው መንቀሳቀስ ያለባቸው? አንድ ሃይማኖት ያለተከታዮቹ ምን ገጽታ ሊኖረው ይችላል?

የሙስሊሙ ዓለም በሥልጣኔ ማማ ላይ በተፈናጠጠባቸው አንድ ሺህ የሚሆኑ ዓመታት ሙስሊሞች በጊዜያቸው ከነበረው ዓለም በሁሉም ዘርፍ ቀዳሚ የነበሩ ብቻ ሳይሆኑ የዓለምን ቅርጽም ቀይረዋል። ኢስላማዊ ኢምፓየሮች (ግዛቶች) በተቋቋሙባቸው የዓለም ክፍሎች ሁሉ ዓለም እማኝነቱን የማይነፍጋቸው ሥልጣኔዎችና ባሕላዊ እምርታዎች በታሪክ አምዶች ሁነኛ ቦታ አግኝተዋል። የዚያን ሥልጣኔ መዘውር ጨብጠው የነበሩ ሕዝቦች ዝርዮች ናቸው እንግዲህ አሁን በዘመናችን የሥልጣኔ ተቃዋሚዎችና ኋላቀሮች ተደርገው እየተሳሉ የሚገኙት። ዛሬ አሸባሪዎች፣ ጨለምተኞችና ጸረ ምዕራባዊያን ስልጣኔ ተደርገው በስፋት የሚገለጹት የዚያ ታሪክ ሰሪ ትውልድ የልጅ ልጆች ሲሆኑ ምዕራቡ ዓለም ደግሞ ትሁትና ደስተኛ ተደርጉ ነው በየቴሌቪዥኖቻቸው የሚቀርበው። አሁን በቅርቡ በኢንተርኔት የተለቀቀና ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች እንደተመለከቱት የሚገመት የቪዲዮ ምስል "አንቲ ዋርፕ" በተባለች የቤልጂየም ከተማ የባቡር ጣቢያ ሲወረርና በርካታ ቤልጄማዊያን ሲጨፍሩ ያሳያል።

እንግዲህ ይህ የእብደት ተምሳሌት የሆነ ድርጊት የዘመናዊነትን ካባ እንዲደርብ ተደርጉ ሲወደስ በዚህ ሙዚቃዊ ጭፈራ መሳተፍ ያልፈለጉ ሙስሊሞች ደግሞ የቀድሞ ዘመን ባህልን የሚከተሉ ገትጋቶች

■ ሰማይ ጠቀስ በሆኑ ሕንፃዎች መካከል የቆመ አቡ ዳቢ ውስጥ የሚገኝ መስጊድ።

መሆናቸው ነው። ለምን እንደዚህ ሆነው ተሳሉ? ይህን ሃሳብ ለማራመድ የሚሹ ካሉ በመላው የሰለጠነ ዓለም በየማህበረሰቡ በስፋት የተሰራጩትን ትጉህ ሙስሊሞች ችላ ማለት ግድ ይላቸዋል። አዎን! ለሳይንሳዊና ለማሕበራዊ እመርታ፣ እንዲሁም ለፖለቲካው መሳለጥ ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ ያሉ ሆኖም ግን ፈጣሪያቸው ባወረደላቸው ሕግጋት ለማደር የሚሹ ሙስሊሞችን እንደሌሉ መቁጠር ሊኖርባቸው ነው።


ዓለም አቀፋዊው ፍትሕና የሙስሊሞች ጩኸት

ዛሬ ዛሬ ከየትኛውም የዓለም ክፍልና አቅጣጫ የሙስሊሞች ጩኸት ይሰማል። እሪታቸው ስሜትን ያምሳል። ኡኡታቸው ሰሚ አጥቷል። በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ አምሳያ ያልተገኘላቸው ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "አማኞች ልክ እንደ አንድ አካል ናቸው። አንዱ ክፍል ሲጐዳ ሌላው በድካምና በትኩሳት ይጠቃል።"[44]

በዕለተ ጁሙዐህ ስብከቶች ከየትኛውም የምድር ማዕዘን የሚሰሙ ዱዓዎች አንድ የሚነግሩን ሐቅ አልለ። ይኸውም ሙስሊሞች ያለማንም ጠበቃ እዚህም እዚያም እየተጠቁ፣ እያለቁ፣ እየተገፉ፣ እየተጨቆኑ፣ ሰቆቃ እያስተናገዱ መሆኑን ነው። እናም ሙስሊሞች እርስ በርሳችን ካልተዛዘንንና አንዱ ለሌላው ጥብቅና ካልቆመ ማንም እንደማይደርስልን የገሃዱ ዓለም እውነታ ፍንትው አድርጐ እያሳየን ነው። የፍትሕን አንድ ዓይን ያጠፋ ጨቋኞች በርክተዋል። ዛሬ ለሙስሊሞች የሚፈርድ ሕሊና እጅግ ተመናምኗል። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ቢሳካለትም ባይሳካለትም ቅድሚያ የሚሰጠው የራሱን ምኞት ለማደላደል መሆኑን ሙስሊሞች ጠንቅቀን ማወቅ አለብን። ከዚያ በኋላ ነው ስለ ፍትሕና ዲሞክራሲ መጮህ የሚጀመረው። የምዕራቡ ዓለም ዋና ዋና የዜና ማሠራጫዎች የሙስሊሞች ጉዳት የቱንም ያህል ቢሆን ያንን ከማጐላት ይልቅ ትንሿን ጥፋታቸውን አግዝፈው ማሳየቱን ተክነውበታል።

በሰለጠነው ዓለም ያሉ የዲሞክራሲ እሴቶች 'ህሁ...' ማስቆጠሪያ ተቋማትና ት/ቤቶች የሙስሊሞችን መብቶችና ሃይማኖታዊ እሴቶች ከጉዳይ አይጥፏቸውም። በየሃገራቱ የሚኖሩ ስደተኛም ሆኑ ኢስላምን የተቀበሉ ዜጐች ሊበራልም ሆኑ ኮንሰርቫቲቭ ሙስሊሞች የእነርሱ ጉዳይ የሚነሳው ትኩስነቱ ከበረደና ያን ያክልም ትኩረት በማይስብበት ወቅት መሆኑ ልብ ይሰብራል። በሌላ በኩል በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ተንታኞች ሃይማኖታቸው ክፋኛ ሲብጠለጠልና በሽብርተኝነት አጉራህ ጠናኝ እዚህም እዚያም ጥፋት ሲላከክበት ክፉኛ በሃዘን ይቆዝማሉ። ብዥታም ውስጥ ይገባሉ።

"የኢስላም ኃይልና ጉልበት ያለው በሰይፍ ላይ ነው" የሚለው ጠንጋራ ምልከታ ከቅማት ወደ አያት ከዚያም ወደ ልጅ ልጆች እንደ መልካም ትውፊት ሲተላለፍና የሃቅ ማንጸሪያው ሲጣመም ይተክዛሉ። እናም ሙስሊሞች "የመካከለኛው ዘመን ባርባሪያን ሕግጋትን የሚያራምዱና ከዘመናችን የዲሞክራሲ ይትባሃል ጋር የማይሄዱ" ተብለው ሲተቹ ውስጣቸው ይታመማል። የአንድ ክርስትና ሃራጥቃ (sect) ጳጳስ ብድግ ብለው ስለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አክብሮት የጐደላቸውን ቃላት ሲሰነዝሩ ወይም አንዱ አፈንጋጭ ጋዜጣ የእዝነቱን ነቢይ በአጓጉል የካርቱን ስዕል ሲያወጣ የሚቆጡ አካላት መኖራቸው



■ ሙሐመድ ዩኑስ የግራሚን ባንክ ፈልሳፊ ሲሆኑ በዘመናዊው (የተለመደው) የባንክ አሠራር ብድር ለማኘት ያልቻሉ ሰዎች ብድር የሚያገኙበትን መንገድ የማይክሮ ክሬዲት ስልት ያስተዋወቁ ሰው ናቸው።

የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። እነዚህ ቡድኖች ጠጠሮችን አንስተው በቅርባቸው የሚገኙ መስኮቶችን ቢሰባብሩና በሥነ-ምግባር የታነጸ ስብዕናቸው ተጐድቶ በካሜራ ፊት በቁጣ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ቢታዩና መስኮቶችን ቢሰባብሩ አያስደንቅም።[45]

በሙስሊሙ ዓለም የሚገኙ ብሄራትን የነቀዙ ሰዎች ሲመሯቸው የሚፈጠሩ ብልሹ አስተዳደሮችን ዜጐች ሲመለከቱ ሁኔታውን ከምዕራቡ ዓለም ዲሞክራሲ ጋር እያነፃፀሩ ያዝናሉ። እናም ምዕራባዊያኑ "ኢስላም ለዘመናዊ ዲሞክራሲ ምቹ ማዕቀፍ የለውም" የሚለውን የተሳሳተ እይታ የሚጋሩ ሙስሊሞች ቁጥራቸው እያደገ ይገኛል።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሙስሊሞች በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደርስባቸው ተጽዕኖና መገፋት የተነሣ በየሃገራቱ የሽብር ድርጊት የሚፈጽሙትን ማውገዝ አይፈልጉም። እንዲያውም አንዳንዴ "ደግ አደረጉ" ዓይነት ስሜት የሚያንጸባርቁ አይታጡም። በካራቺ ፓኪስታን መጽሐፍት የሚያቃጥሉና የሚጮሁ ስብስቦችን ስንመለከት እንደነቅ ይሆናል። ሆኖም ግን ይህ ዓይነት ስሜት በየትኛውም የሙስሊሙ ዓለም ያለና ውስጥ ውስጡን የሚንተከተክ ቁጭትና ብሶት መኖርን ማወቅ ብልህነት ነው። ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ በዚህ ትዕይንት ከክርስቲያኖች፣ አይሁዶችና ሴኩላሪስቶች የበለጠ ሙስሊሞች የተሰላቹ መሆኑን ነው። ፍትሕ ቢሰፍንና ፈጣሪያቸውን በሰላም እያመለኩ ቢኖሩ ብዙዎቹ ደስተኞች ናቸው።[46]

እርግጥ ነው በየማዕዘናቱ የተለያዩ የሽብር ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሙስሊሞች አብዛኛውን አማኝ የማይወክሉ ብቻ ሳይሆኑ ተግባራቸው እንወዳቸዋለን ከሚሏቸው ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ድርጊት ጋር ፈጽሞ

የተፋታ መሆኑ እውነት ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በጐ አሳቢና የዓለምን መልካም ገጽታ የሚያስተውሉ ነበሩ። መዲና በኖሩባቸው ዓመታት በዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴያቸው ያሳዩት መተዛዘንን ሰብዓዊነትን፣ የሌሎችን ባሕል ማድነቅን (የሃበሻ ሰዎች ያደረጓቸውን ባሕላዊ ፌስቲቫሎች ከዓኢሻ (ረ.ዐ) ጋር ማየታቸውን ያጠኗል) ነው። በሕይወታቸው ውስጥ ምሬትና ተስፋ መቁረጥ ፈጽሞ ተስተውሎ አያውቅም። የከፋ ሁኔታና ምርጫ ማጣት እስካለስጨነቃቸው ድረስም ወደ ግጭት መግባት አይወዱም ነበር። ከዚህም በላይ ራሳቸው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦

"አግራሩ አታክብዱ። አብስሩ አታስፈራሩ።"[47]

የኢስላም (የሸሪዓ) ሕግ አስደንጋጭ ወይስ ብስራት?

ከእንግዲህ አጠቃላዩን ውይይታችንን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተከሰቱ ባሉ ሁኔታዎች ላይ ብቻ እንዲያጠነጥን ማድረግ አይኖርብንም። ከዚያ ይልቅ ላቅ ወዳሉና አጽናፍ ወደማይገድባቸው ጥያቄዎች መንደርደር ይኖርብናል። እናም ኢስላም ዲሞክራሲያዊ የሕይወት ዘይቤ ነውን? ሌሎች ሴኩላር ሕግጋትንስ ያከብራል? ሙስሊሞች የተለያዩ አስተሳሰቦች የሚንሸራሸሩበትን ማሕበረሰብ ያከብራሉን? የፆታ ጉዳይን በተመለከተስ ኢስላም ያለው ሃሳብ ምንድን ነው? እነዚህና እነዚህን የመሳሠሉ ጥያቄዎች በአሁኑ ጊዜ በዘመነው ዓለም ከመነሳታቸው በፊት ኢስላም ቀድሞ መልስ ሰጥቶባቸዋል።

በዚህ ምዕራፍ ለማየት የምንሞክረውም የታወቁ ምሁራንና ታሪካዊ እውነታዎች በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የኢስላምን አቋም ያንጸባረቁበትን መንገድ ነው። ለመቶ ዓመታት የተደረጉ ኢስላማዊ የትምሕርት (የዕውቀት) ፍለጋዎች ያፈሯቸው መጽሐፍትና ድርሳናት በየመስጂዶች የሞሉ ሲሆን ይህም በከተሞች ቤተ መጽሐፍት ካሉት መጽሐፍትና መዛግብት በቁጥር የሚልቅ ነው። የዚህ ምክንያቱ የኢስላማዊውን ተርቢያ (ኩትኩታ) የተሟላ ለማድረግ የተደረጉ ያላሰለሱ ጥረቶች ውጤቶች ቁርኣንንና ሱናን ማዕከል አድርገው መቀጠላቸው ነው።

የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዮቻቸው ቁርኣንንና የእርሳቸውን ሱና አጥብቀው እንዲይዙ ሲመክሩ ለእያንዳንዱ ችግር የቁርኣናዊ አንቀጽ መልስ እንዳይጠብቁ መፈለጋቸው የታወቀ ነው። ይህን ለማለት በቂ ምክንያት ማስቀመጥ ይቻላል።

ወጣቱንና መልከመልካሙን ሙዓዝ ኢብኑ ጀበልን (ረ.ዐ) ወደ የመን መሪ (ዳኛ) አድርገው ሲልኩት እንዴት አድርጐ የዳኝነቱን ሥራ ሊያከናውን እንዳሰበ ጠይቀውታል። ሙዓዝም (ረ.ዐ) "ከቁርኣንና ከመልእክተኛው ሱንና መረጃ እፈልጋለሁ" አላቸው። "ከሁለቱ ምንም ዓይነት መረጃ ካላገኘህስ ምን ታደርጋለህ?" በማለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲጠይቁት ሙዓዝ (ረ.ዐ) "ያቅሜን ያክል ጥረት (ኢጅቲሃድ) ከማድረግ ወደኋላ አልልም " በማለት መልስ ሰጣቸው ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ዓይነት ብቃት ያለውን ሰው ወደ የመን እንዲልኩ ያደረጋቸው ፈጣሪያቸውን ማመስገናቸው በሐዲስ ተወስቷል። [48]

ሃሺም ካሚል የተባሉ ምሁር ኢጅቲሃድን "ሃይማኖታዊ ፈትዋ ለመስጠት የሚደረግ ምሁራዊ ጥረት" ሲሆን "ይህም ከሸሪዓ መሠረታዊ የሕግጋት ማዕቀፎች (frame works) ባላፈነገጠ መልኩ የሚፈጸም ምርምር ነው።"በማለት ትርጓሜውን አስቀምጠዋል።[49] እንግዲህ ኢጅቲሃድ ማድረግ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቀዋልና የኢስላምን ሃይማኖት ጊዜ አይሽራ እንዲሆን ዋስትና የሚሰጥ በመሆኑ ታላቅ ጸጋ ነው ማለት ይቻላል። ሌሎቹ ከኢጅቲሃድ ጋር አብረው የሚሄዱ ቃላት ደግሞ 'ዑርፍ' እና 'ኢስቲሕሳን' የሚሰኙት ናቸው።

የመጀመሪያው የሚወክለው መልካምነቱ በሕገ ሸሪዓ የታወቀን ነገር ሁሉ ሲሆን 'ማዕሩፍ' ወይም መልካም የሚለው የዓረብኛ ቃል ጋር ይዛመዳል። 'ኢስቲሕሳን' ማድረግ ደግሞ የሃይማኖቱ ሊቃውንት (ፋቀሃእ) እንድን ጉዳይ አስመልክተው ኢጅቲሃድ ሲያደርጉ ጥሩነቱን የሚደግፉትን ነገር ከሸሪዓው ጋር የሚያስማሙበት ሂደት ነው።

የዑርፍ ጽንሰ ሃሳብ ምንድን ነው?

አንድ ኢስላምን የሚያጠና ተማሪ ኃይማኖቱ ለውጦችን ያለምንም መደናገር ማቀፍና ማስተናገድ መቻሉን ሲገነዘብ መደነቁ አይቀርም። በ7ኛው መቶ ዘመን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመካ ማሕበረሰብ ኢስላምን ሲያስተዋውቁ ያመጧቸው ሕግጋት ሥር ነቀልና ለብዙ ምእተ ዓመታት የሰውን ዘር ሕልውና የሚነኩ ነበሩ። ይሁን እንጂ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያረጀና ያፈጀውን የጃሂሊያ (የድንቁርና) ስርዓት ውርሶች ሁሉ የማፈራረስና በአዲስ የመተካት ተልዕኮን ይዘው አልነበረም የተላኩት። ከዚያ ይልቅ መልካም (ዑርፍ) የሆኑና ከሸሪዓ ጋር የማይጋጩ ባሕሎች በማቀፍ የኢስላማዊው ሕግ አካል አድርገዋቸው ነበር የተገዙት። ሙሉ ለሙሉ መጥፋት ያለባቸውን በማክሰምና መጠነኛ ማስተካከያ የማያስፈልጋቸውንም በማስተካከል ነው የኢስላም ሕግ የቆመው።

ጎጂ ከሚባሉት የዘመናችን ባሕሎች መካከል ለምሳሌ በፓኪስታንና አፍጋኒስታን የሚገኘው የፖሽቱን ጐሣ የሚገለገልበት 'ቫኒ' የተባለው ደንብ ይጠቀሳል። የቫኒ ደንብ እንደሚያዘው አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሞ ቅጣት ሲበየንበት ልጆችን ለተጐጂው አካል በመስጠት (በካሳ መልክ) እርቅ ይፈጽማል። ይህ ፈጽሞ በሕገ ሸሪዓ ተቀባይነት የሌለው ነው። እንዲሁም በምስራቅ፣ ሰሜን አፍሪካና በዐረቢያ ባሕረ ገብ መሬት የተለመደው የልጃገረዶች ሐፍረተ-ገላ ዝል ዘላ ከሕገ ሸሪዓ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ የሚወገዝ ሆኗል።

ዓለም አቀፋዊ ግንዛቤና የአስተሳሰብ ውስንነት በዘመናችን የሽብር ጥቃት የሚፈጽሙ ግለሰቦች (ቡድኖች) እና የኢስላም ጠላቶች ለቁርኣን ያላቸው ግንዛቤ የተንሻፈፈ መሆኑ ይስተዋላል። እነርሱ የሚያራምዱትን ዓላማ እስከደገፈላቸው ድረስ የቁርኣን አንቀጾችን ከዋናው ይዘታቸው ነጥለው በማውጣት ሲጠቀሙባቸው ይታያሉ።

ለምሣሌ፦ "... ባገኛችኋቸው ሥፍራ ሁሉ ግደሏቸው..." የሚለውን አባባል ከዋናው ቁርኣናዊ አንቀጽ አግባቡ (context) ነጥለው በማውጣት "ሙስሊሞች ከሃዲያንን የትም ሥፍራ ቢያገኙ እንዲገድሉ" ታዝዘዋል ብለው ይናገራሉ። ይህ አንቀጽ የወረደው አጋሪ የሆኑት የኢስላም ጠላቶች ሙስሊሞችን

ከፋኛ ይፈታተኑ በነበሩባቸው ጊዜያት የእነርሱን ሃይል ለመስበር ነው። እናም ለዚያ ጊዜና ሁኔታ ብቻ ተመጥኖ የወረደ አንቀጽ ነው ማለት ነው።

ይሁን እንጂ ሽብርተኞች በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ ኢስላምን የማይከተሉ ሕዝቦችን ለመግደል መለኮታዊ ፈቃድ እንደተሰጣቸው በማድረግ ይህንን አንቀጽ ይጠቅሳሉ። በሌላ በኩል የምዕራቡ ዓለም ጋዜጠኞችና የኢሲላም ጠላቶች ኃይማኖቱን ለማጠልሸትና ለጥፋት ፕሮፖጋንዳቸው ይህንኑ አንቀጽ ቆንጽለው በማውጣት ይጠቅሳሉ።

የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) "የእዝነት ነቢይ" ሲሆኑ ለዓለማት ሕዝቦችም የተላኩት በዚሁ መንፈስ መሆኑን ቁርአን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፦

" (ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።"

ስለ ኢስቲሕሳንስ ምን ከሚከት ይቻላል?

'ኢስቲሕሳን' የሚለው የዐረብኛ ቃል በጥሬው ሲተረጐም 'አንድን ነገር ጥሩ፣ የሚያምርና ተመራጭ አድርጐ ማየት' ማለት ነው።[50] ኃያሉ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፦

«ይህችንም ከተማ ግቡ፤ ከርሷም በሻችሁት ስፍራ ሰፊን (ምግብ) ተመገቡ፤ በሩንም ያንነበሳችሁ ኾናችሁ ግቡ፤ (ጥያቄያችን የኃጢአታችን መርገፍ ነው) በሉም፤ ኃጢአቶቻችሁን ለናንተ እንምራለንና፤ በጎ ሠሪዎችንም (ምንዳን) እንጨምርላቸዋለን፤ ባልን ጊዜ (አስታውሱ)።» (አል-በቀራህ፣ 58)

ኢስቲሕሳን የማድረግ ሂደት ብዙዎቹ መከተል እንደሚፈልጉ ይታወቃል። በተለይም ወደ ምዕራቡ ዓለም በስደት የሄዱ ሰዎች ሙስሊም ባልሆኑ ሃገራት ያለችግር ለመኖር ኢስቲሕሳንን ይጠቀሙበታል። ቀደምት አባቶችም ቢሆኑ ኢስቲሕሳን ማድረግን ለብዙ ሁኔታዎች ይገለገሉበት እንደነበር ከኢስላማዊ ታሪኮች እንረዳለን። ለምሳሌ ኸሊፋው ዑመር (ረ.ዐ) የኢስቲሕሳን መርሆችን በውርስ ሕግጋትን ለመተግበር አውለውታል። የእርሳቸውን ፈለግ በመከተል ሌሎች ዋና ዋና ሰሐባዎችም ሲሰሩበት ቆይተዋል።

> "ኢስቲህሳን የሰውን ልጅ ዕውቀት ዘጠኝ አስረኛውን ይወክላል"
> -ኢማም ማሊክ፣ ከአራቱ የኢስላማዊ ህግ ሊቆች አንዱ

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ኢስቲህሳንን ተግባራዊ በማድረግ ኢስላምን ለሁሉም የሰው ዘሮች ፍላጐት እንዲንበረከክ የማድረግ ዓላማን ማንም ማራመድ አይፈልግም። የኢስላም ምሁራን ፈትዋ ከመስጠታቸው በፊት ታላቅ የሆነ የሃይማኖታዊ ዕውቀት ማማ ላይ መድረስ ይጠበቅባቸዋል።[51] አንድ የማይታበል ሐቅ ይስተዋላል። ይኸውም ሙስሊሙ ዓለም ብቃት ያላቸው የሃይማኖት ሊቃውንት የሌሉት

መሆኑ ነው። እንበለ እውቀት ፈትዋ የመስጠትን ስልጣን በዘፈቀደ የያዙ ሰዎች የሞት ቅጣትን ጨምሮ የፈለጉትን የቅጣት ዓይነት ይገባዋል ብለው ባሰቡት ሰው ላይ የመጫን መብት ያላቸው ይመስላቸዋል። በካሊፎርኒያ የበርክሌይ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት (ኻቲም) በዘመናችን የሚሰጡ ብስለት የጐደላቸው ፈትዋዎችንና የጅሃድ ጥሪዎችን በመታዘብ መጣጥፍ አስነብበዋል።

"ኢስቲህሳን ከሰው ልጅ ዕውቀት ዘጠኝ አሥረኛ የሚሆነውን ይወክላል" ኢማም ማሊክ ምንም ሁን ምን አንተን አልመስልም። በዛሬው ጊዜ ዲሞክራሲ በምዕራቡ ዓለም ላሉ ሃገራት ሁነኛ የሃብት ምንጫቸውና የደህንነታቸው ዋስትና የሚረጋገጥበት ሥርዓት መሆኑ እውነት ነው። ሃብቱ ወይም ደህንነቱ (ወይም ሁለቱም) በሚጠፋ ጊዜ "ነፃ ምርጫ" እያሉ መጮሁ ትርጉም አይኖረውም። የዲሞክራሲ ወግና ባሕል ከሙስናና ሃብት ከማጋበስ ጋር ከተሣሠረ ጌጡና ውበቱ ተበላሽቶ ወደ ጨቋኝነት ብልሹ አስተዳደርነት ይዘቅጣል። ለዚህም ነው ሁሉም ባይሆኑ የአብዛኞቹ ኢስላማዊ ጽንፈኞች መርህ ጥብቅና ደረቅ ከሆነው የሌኒኒዝም መርህ ጋር የሚመሳሰለው በተጨማሪም ነፃ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ማሕበረሰቦች ብልጽግና በማይታይባቸው ጊዜያት የሥርዓቱን መሠረታዊ ዋጋማነት ማጠያየቅ ይጀምራሉ። በታላቁ የኢኮኖሚ ድቅቀት (economic depression) ወቅትና ከዚያም በኋላ በርካታ አሜሪካውያን የኮሚኒዝምና ሶሻሊዝምን ጽንሰ ሃሳቦች ወደማቀንቀኑ ማዘንበላቸው በዚህ የተነሣ ነበር።

ኢስላምን ከዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ጋር በማነጻጸርና ኢስላም ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ኢስላም ጊዜ በማይሽረው መለኮታዊ ብርሃን የሚመራ ራሱን የቻለ የሕይወት ዘይቤ እንደመሆኑ ከሰው ሰራሹ ዲሞክራሲ እጅግ ላቅ ያለ ነው። የወደፊቶቹ ሙስሊም ትውልዶች ዳግም ይህን ያማረ ሕገ ተፈጥሮ (ፈጥራ) ሲኖሩትና ለዓለም ማንጸባረቅ ሲችሉ የግለሰቦችና የቡድኖችን መብቶች በማክበርና የሰውን ዘር ልዕለና ከፍ በማድረግ ከዲሞክሲያዊ ሃገራት በአላህ ፈቃድ እጅግ ይልቃሉ ።

ክብ ኪባኩ የሚገባቸው ጉዳዮች

የሰለጠኑ የሚባሉ ማሕበረሰቦች የሚታወቁበት ሌላው መልካም ነገር ልዩነቶቻቸው ማቻቻላቸው ነው። ይሁን እንጂ እዚህ ደረጃ የደረሱት ገና በቅርቡ ሲሆን አሁንም ብዙ የሚጐድሏቸው ነገሮች እንዳሉ ግልጽ ነው። ኢስላም ግን ገና ከጥንት ጀምሮ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመዲና ከተማና በዙሪያዋ በሸሪዓ የሚተዳደር መንግሥት ሲያቋቁሙ ጀምሮ ይህ መቻቻል ሁነኛ መሠረት ተጥሎለታል።

የአላህ ነቢይ መዲና ላይ የመንግሥቱን ቻርተር (መተዳደሪያ ደንብ) ሲነድፉ የማሕረሰቡ አባላት ሙስሊም ሆነ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ወንድ ሆነ ሴት፣ ጥቁር ሆነ ነጭ፣ ሃብታም ሆነ ድሃ የሚታቀፉበትን አሠራር መዘርጋት ችለው ነበር። በአይሁድ ክርስቲያን አፈታሪክ እንደሚነገረው አብረሃም (ነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ)) የእስማኤል እናት የሆነችውን አፍሪካዊቷን ሃጀርን እቁባት አድርገው ይዘዋታል። ይሁን እንጂ ቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ይህን አይሉም።

ሃጀርን ራሷ ባለቤታቸው ሳራ ናት ሚስት ትሆናቸው ዘንድ የዳረችላቸው። ኢስላማዊው ትውፊትም ሃጀር ትክክለኛ የነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ሚስት እንደነበረች ነው የሚናገረው። የታላላቆቹ ነቢያት ሁሉ አባት የሆኑት ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ይህንን በኢስላም ትልቅ ቦታ የተሰጠውን ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የመጋባት ሂደት አፍሪካዊቷን ወይዘሮ ሃጀርን በማግባት አስተዋውቀዋል።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላቁን አደራቸውን ይዘው ወደ ሕዝባቸው ሲመጡ ዐረቢያ ታላቅና አስደንጋጭ በሆነ የዘረኝነት ልክፍት ተይዛ ነበር። እርሳቸውም በዚህ ጉዳይ ላይ መለሳለስን ባለማሳየት እስከመጨረሻው ድረስ ተፋልመውታል። ከባልደረቦቻቸው ውስጥ ቢላል (ረ.ዐ) አፍሪካዊ ባሪያ የነበረ ሲሆን፤ ሳልማን (ረ.ዐ) ከፋርስ፣ ሱሃይብ ደግሞ ከሮም የተገኙ ባሮች ነበሩ። ዛሬ እነዚህ ሰዎች ከቀለማቸው ባሻገር በማንነታቸው ልቡ በሚነካው ሙስሊም ማሕበረሰብ በእኩል ዓይንና በክብር የሚታዩ ናቸው።
ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕልፈት በኋላ ብዙ ዓመታት ቆይተው የኸሊፋነቱን ሥፍራ የተረከቡት ዐሊ (ረ.ዐ) የግብጽ አስተዳዳሪ አድርገው ለሾሙት ሰው እንዲህ የሚል ማስጠንቀቂያ ልከውለታል፦ "እዚያ የምታስተዳድራቸው ሰዎች አንድም በሃይማኖት ወንድሞችህ ናቸው ካልሆነም ደግሞ እንዳንተው ሰብዓዊ ፍጡር ናቸው።"

ዓሊይ (ረ.ዐ) በአንድ ወቅት በዑመር (ረ.ዐ) የአስተዳደር ዘመን በአንድ አይሁድ ተከሰው ችሎት ፊት ቀርበው ነበር። ቃዲው (ዳኛው) ራሳቸው ዑመር (ረ.ዐ) ሲሆኑ ዓሊይን (ረ.ዐ) እንዳዩዋቸው በክብር "አቡል-ሐሰን" በማለት በሰላምታ ተቀብሏቸው። አይሁዳዊውን ግን በመደበኛ ስሙ ብቻ ጠርተው ሠላም አሉት። በዚህ ጊዜ ዑመር (ረ.ዐ) ከዓሊይ (ረ.ዐ) ፊት ላይ ደስታ የማጣት ስሜት አነበቡ። ቆየት ብለው ከአይሁዳዊው ሰው ጋር ጐን ለጐን መሆናቸው አስከፍቷቸው እንደሆን ዑመር (ረ.ዐ) ሲጠይቋቸው ዓሊይ (ረ.ዐ) በመደነቅ የተከፉት እንዲያውም ከአይሁዳዊው በተሻለ ሁኔታ ክብር የተሰጣቸው በመሆኑ እንደሆነ ተናገሩ። የአስራ ሁለተኛው መቶ ዘመን ታላቅ ምሁር የነበሩት ኢማም አል-ገዛሊ የሰው ልጅ ራሱን ከሌሎች ይልቅ ከፍ አድርጐ እንዲመለከት የሚያደርገው አባዜ የሚመነጨው ከሰይጣን የመጀመሪያ ተግዳሮት (በአላህ ላይ ያሳየው ኩራት) እንደሆነ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፦ "ምንጊዜም ቢሆን ሃብታም የሆነ ሰው ከድሃው እንደሚሻል ያስባል። ነጩ ሰው ደግሞ ከጥቁሩ ይልቅ ብልጫ እንዳለው ይሰማዋል። በዚህም የተነሣ ይኮራል። ይህ ሰው ልክ ዲያቢሎስ የፈጸመውን ዓይነት ሃጢአት ይደግማል። ይህን ሲያደርግም ከተውሂድ ጋር በመቃረን ሽርክ ላይ ይወድቃል።"[52]

የሙስሊሞች መቻቻል አስከምን?

ሙስሊሞች በሆደ ሰፊነትና በመቻቻል አምሣያ የሌላው ታሪክ እንዳላቸው ከሚያሳዩ ናሙናዎች የመካከለኛውን ዘመን አንደሉሲያ (ስፔን) ሁኔታ ማየቱ ይበጃል። በዚያ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖች፣ አይሁዶችና ፈላስፎች (ሴኩላሪስቶች) ሰባት መቶ ለሚሆኑ ዓመታት በመቻቻልና በመከባበር በኢስላማዊው መስተዳድር ሥር ዘልቀዋል።

ይህ ተረት አይደለም በተግባር የታየና የተፈተነ ታሪክ እንጂ። እርግጥ ነው በአነስተኛ ደረጃ የሚታዩ ግጭቶችና መቆራቆሶች አልነበሩም ማለት ያስቸግራል። ቢሆንም ግን በአብዛኛው አንደሉስ በአውሮፓ ምድር የመቻቻል እሴት በጉልህ የተንጸባረቀበት የመጀመሪያዋ ምድር ናት።ይሁን እንጂ ካቶሊኮች ሙስሊሞችን እየገፉ ከደቡባዊው ስፔን ካስወጧቸው በኋላ እዚያ በቀሩት ሙስሊሞችና አይሁዶች ላይ ታላቁን የስቃይ ምርመራ (Inquisition) በማካሄድ ወደር የሌለው ግፍ ፈጽመዋል። ያ ሁሉ ያማረና የሰመረ መቻቻልም አፈር በልቷል።[53]

ይህ የአንዱሉሲያ የመቻቻል ሕይወት በመልካሳ ምድር ፈጽሞ የማይቀራረብ በሆነው የቀድሞዋ ዩጐዝላቪያ ግዛት በቦሳኒያ ሳራየቮ ተደግሟል። በ17ኛው መቶ ዘመን ሳራየቮ ከተማ በአውሮፓ የአቶማን ቱርኮች የንግድ ማዕከል ሆኖ ነበር። በዚያ ጊዜም እንዲሁ ሙስሊሞች፣ አይሁዶችና ክርስቲያኖች (ሰርቦች) በመቻቻልና በመከባበር መኖሩን ችለውበት ታይተዋል። በሚያሳዝን ሁኔታ ይህ መቻቻል በመጨረሻ ምን እንደደረሰበት ሁላችንም የምናውቀው ነው። ፍፃሜው ልክ በአንደሉሲያ እንደተደረገው በጭካኔ መደምደሙ ያስደንቃል። ምናልባትም ለወደፊቱ የአላህ ፈቃድ ከሆነ ይህ መቻቻል በአንደሉሲያ (ስፔን) እና በሰራይቮ ደግሞ በቀጣዮቹ ትውልዶች ሊከሰት ይችላል።

በሰራይቮ ቦስኒያ ሄርዚጐቪና በ1941 የኦዶልፍ ሂትለር ቅርብ የሆነ ሰው የቦስኒያ መንግስት አይሁዶችንና ሰርቦችን እንዲያጠፋ ትዕዛዝ ሰጠ። ለብዙ ዓመታት ከሙስሊሞች ጋር ጐን ለጐን የኖሩት አይሁድ፣ ጅብሲዎችና ሰርቦች የሃገራቸው ሰዎች ከሆኑት ሙስሊሞች ዘንድ መጠጊያ ለማግኘት ዋተቱ። በዚያ ክፉ ሁኔታ በሰፈነበት ጊዜ ደርቪስ ከርኩት የተባለ አልባኒያዊ ሙስሊምና በቦስኒያ ብሔራዊ ሙዚየም ቤተ-መጽሐፍት ባለሙያ (librarian) የነበረ ሰው የተለየ ታሪክ ሰርቷል። ከርኩት በኢስታንቡል (ቱርክና) በፈረንሳይ የተማረ ሲሆን ለሳራየቮን አይሁድ ማሕበረሰብ መብት በመቆርቆር ብዙ ጽፏል። ይሁን እንጂ የዚህ ሰው ተቆርቋሪነት በንግግር (በጽሑፍ) ብቻ የተገደበ አልነበረም።በ1942 ጆሃንና ፎርተነር የተባለ ጨካኝ የናዚ መኮንን ኮርኩት በሙዚየሙ ቤተ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ የአይሁድ ድርሳኖችን እንዲያስረክብ ያዘዋል። የሙዚየሙ ሃብት በሙስሊም አንደሉስ (ስፔን) የተዘጋጀና 'ሃጋናህ' (Passover) መጽሐፍ ነበር።

ይህ መጽሐፍ ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት ከተፈጸመ የመጽሐፍ ማስወገድና ማቃጠል ሂደት መትረፍ ችሎ ነበር። ስለሆነም ከርኩት ማንኛውንም መስዋእትነት ከፍሎ (ሕይወቱን ለአደጋ ማጋለጥ ቢኖርበትም) መጽሐፉን ከጥፋት ሊያድነው ወሰነ። የናዚ መኮንኑ በሙዚየሙ ጉብኝት ሲያደርግ መጽሐፉን በልብሱ ሸፍኖ አሳለፈው። በመጨረሻም የሳራየቮ መስጊድ ኢማም የነበሩ ሰው ዘንድ በአደራ አስቀመጠው።

ጦርነቱ እስኪያበቃ ድረስም እርሳቸው ጋር ቆየ። ይህ የከርኩት ተግባር ተለይቶ የሚታወቅ ነው። ይሁን እንጂ ሌላውና በሚገባ ያልተገለጸ ተግባሩ ደግሞ ሚራ የተባለችን አይሁዳዊት ወጣት



■ ማልኮልም ኤክስ የሐጅን ሥርዓተ ጸሎት ፈጽሞ ከመካ ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ

ከማህበረሰቡ መካከል የዘር መድሎ ችግርን መቅረፍ የቻለ ብቸኛ ሃይማኖት በመሆኑ አሜሪካ ኢስላምን መረዳት ያስፈልጋታል። አሜሪካ ውስጥ ነጭ ተብለው የሚቆጠሩ ነገር ግን ከአዕምሯቸው የነጭነትን አስተሳሰብ ከፋቀላቸው ሙስሊሞች ጋር በሙስሊሙ ዓለም ተገናኝቻለሁ፣ አውርቻለሁ፣ አብሬም በልቻለሁ። ቀለም ሳይለይ ሁሉንም የሰበሰበ ንጹህና እውነተኛ ወንድማማችነት በሁሉም ቀለም ሲተገበር ከዚህ ቀደም አይቼ አላውቅም።

ማልኮም ኤክስ፣ ወደ መካ ካደረገው ቅዱስ ጉዞ የተወሰደ ፅሁፍ

ከሞት መንጋጋ አትርፎ በቤቱ በመደበቅ ወደ ጣሊያን እንድትሄድ ማድረጉ ነው። በዚህ ተግባሩ ከርኩት ቁጥር ስፍር የሌላቸው ቦሰኒያውያን ጋር ተመሣሣይ ታሪክ ይጋራል። የቦሰኒያ ሙስሊሞች አልባኒያውያን ክርስቲያኖችና አይሁዶች ጐረቤቶቻቸው በሃይማኖታቸው ምክንያት ሲታረዱ ከሚያዩ ይልቅ ቢሞቱ ይመርጡ ነበር።

አውሮፓ ውስጥ በናዚ ቁጥጥር ስር ከነበሩ ሃገራት ሁሉ አልባኒያ ውስጥ የነበሩ አይሁዶች ብቻ ነበሩ ተቃውሞ ማድረግ የቻሉት። እያንዳንዱ የአይሁዳዊ ነፍስ ከአደጋ የተጠበቀ ነበር። ኤንቨር አሊያ ሻገር የተባለ የሙስሊም በጐ አድራጊ ልጅና 'ያድ ቫሺም' በሚሰኝው በሆሎከሳት የተጨፈጨፉ አይሁዳውያን መታሰቢያ ስሙ የተመዘገበ ሰው እንዲህ ብሏል፦ "አባቴ የራሱን ሕይወት አደጋ ላይ በመጣል መላውን መንደር ከናዚዎች ጥፋት ለማዳን ለምን ፈለገ? አባቴ ጥልቅ እምነት ያለው ሙስሊም ነበር። የአንድን ሰው ነፍስ በማትረፍ ጀነት እንደሚያስገባ ያውቅ ስለነበር ነው።"

ጠንካራ ባህል ብዝሃነትን ይፈቅዳል። ጠንካራ ባህል የአስተሳሰብ ነጻነትን፣ ከማዕቀፍ ወጣ ማለትን ይፈቅዳል። የአባሲዶች ዘመን [750-1258 ዓ.ል] በዕድገት ጫፍ ሲደርስ በራስ የመተማመን ባህል ሆኖ ነበር። የዚህ ዐይነት በራስ መተማመን ሲኖር ነጻነትንና መንቀሳቀስን ትፈቅዳለህ።በራስ መተማመን አለመኖር የሰብዓዊ መብትና የሴቶች መብትን ጨምሮ በሁሉም ዘርፍ ወደ ደካማ ባህል ያመራል። በዐረቦች ግዛት ከአሁኑ ዐረብ ዓለም የተሻለ ነጻነት ነበር።-

ሰልማን ማሳልሃ፣ ዐረብ ኢስራኤላዊ ሙሁርና ገጣሚ



በዴንማርክ ጋዜጦች ላይ አወዛጋቢ የካርቱን ስዕሎች ከታተመሙ በኋላ አንድ አይሁዳዊ የሕግ ባለሙያ እንዲህ ብሏል፦ “ነቢዩ ሙሐመድ ከተከታዮቻቸው ጋር በተቀመጡበት አንድ የአይሁድ አስከሬን ሲያልፍ ነቢዩ ተነሱ። በዚያ ጊዜ ሰዎች ‘ይህ’ኮ የአይሁዳዊ አስከሬን ነው’ አሏቸው። ነቢዩም ‘ታዲያ ቢሆንስ የሰው ነፍስ አይደለችምን? ተነሱ!’ በማለት አዘዟቸው።”[54] ይህ ሐዲስ በሙስሊሞች ዘንድ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ይህን አባባል የተናገረው የሕግ ባለሙያ “ተነሱ!” የሚለው ትዕዛዝ በጣም ነው ስሜቱን የነካው ይህ አባባል በመቶዎች በሚቆጠሩ ዓመታት አልፎ ያኔ የነበረውን የሰብዓዊነት እሳቤ ቁልጭ አደርጐ አሳይቶታል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰብዓዊው ፍጡር የነበራቸውን ክብር ጊዜ በማይጋርደው መስታወት አርቆ እንዲታዘብም አብቅቶታል አልሃምዱሊላህ (ምስጋና ለአላህ ይገባው)።



<< እንደ አንድ ሃይማታዊ እምነትና ማህበራዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ፣ ኢስላም በዘመናዊው ሳይንስና ርዕዮተዓለም ከሚወዳደሩትና ከሚደጋገፉት አስተሳሰቦች ጎን ለጎን በዘመናዊው ዓለም የሚጫወተው ወሳኝ ሚና አለው።>>

-ማጂድ ቴህራኒያን፣ ኢስላም ኢንድ ዘ ዌስት ሆስቴጅ ቱ ሂስትሪ?

■ ደርቪስ ከርኩት፣ በቦስኒያ ብሄራዊ ሙዚየም ዋና የላይብረሪ ሰራተኛ። የአስራ አምስተኛው ክፍለዘመን ሃጋናህ መጽሐፍ በናዚዎች እጅ እንዳይጠፋ በመታደጉ የታወቀ።

ወደ መፍትሄው ስንጓዝ

ሙስሊሞች ከምዕራቡ ዓለም በተለየ ሁኔታ ጠጣሮች አይደሉም። ከእነርሱ ውስጥ በርካታዎቹ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን፣ ፖለቲካንና ባሕልን ከልባቸው ይወዳሉ ያደንቃሉም። ብዝሃነት (pluralism) ያለ ልዩነት (dissent) ዋጋ የለውም። አንዱ ሌላውን ሲደግፍ ነው ተከባብሮ መኖር የሚቻለው።
ሙስሊሞች በዘመናዊው ሳይንስና ቁሳዊነት እስከተጠመቁ ድረስ ከሃይማኖታቸው እንደራቁ እንዲኖሩ ነው ግፊቱ እያየለባቸው ያለው። ሆኖም ግን ከሃይማኖታቸው ሕግጋት ሳይጋጩና ሳይጣረሱ ዘመናዊውን የስልጣኔ በረከትም መቋደስ እንደሚችሉ በብዙ አጋጣሚዎች ማሳየት ችለዋል።

በሃይማኖታቸው ላይ ዝግመተ ለውጥን ወይም ማሻሻያዎችን እንዲያደርጉ ሳይሆን ወደ መሠረታዊ ሕግጋት ፊታቸውን እንዲመልሱ ብቻ ነው የሚጠበቅባቸው። አሁን እንደምንመለከተው ተቃርኖው ያለው በኢስላምና በምዕራቡ ዓለም ወይም በኢስላምና በዘመናዊነት መካከል ሳይሆን በሁለቱ የአስተሳሰብ አድማሶች መካከል ነው። አንደኛው ወገን የሰው ልጅ ምንም ይሥራ ምን ከሞት በኋላ ከአካሉ ተነጥላ የምትወጣው ነፍሱን ተጠያቂ የሚያደርጋት ሃይልና ሁኔታ መኖሩ ሲያምን ሌላኛው ደግሞ "ሕይወት ማለት አሁን የምንኖረውና ለወደፊቱም በዚህች ምድር የሚቀጥለው ነው" ባይ ነው። ምዕራቡ ዓለም እኛ ሙስሊሞችን ከሃይማኖታችን እንድንፋታ በሚያስጠነቅቁ ተረቶች ከመጠመድ ይልቅ ከኢስላምና ከሙስሊሞች በርካታ ነገሮችን መጠቀም ይችላል። ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ቀውስ ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ በመጣ ቁጥር የዓለም መሪዎች በእርግጥኝነት ረዥሙን የኢስላማዊ መፍትሄዎች ውርስ ይፈልጋሉ።

ማስታወሻ

[1] ኡመር ፋሩቅ አብደላህ ዋን ጐድ መኒ ኔምስ ገጽ 3።

[2] ዝኒ ከማሁ ገጽ 4።

[3] "ዋይን ኦይ" (አል - ጀምሪያህ) ከተባለው የኡመር ኢብን አል - ፋሪድ መጽሐፍ የተወሰደ። የኤሚሊ ሆመሪን ኡመር ኢብን አል - ፋሪድ ሱፊ ቨርስ ሴያንተሊ ላይፍ ገጽ 43ን ተመልከት።

[4] ኢማም አል - ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል - ቡኻሪ።

[5] ዝኒ ከማሁ።

[6] ኢማም አል ቡኻሪ አል - አደብ አል - ሙፍረድ።

[7] ኢማም አል - ቡኻሪ ሶሂህ አል - ቡኻሪ

[8] ዝኒ ከማሁ።

[9] ዝኒ ከማሁ።

[10] ኢማም አል - ቡኻሪ አል - አደብ አል - ሙፍረድ።

[11] ኢማም አል - ቡኻሪ አል - አደብ አል - ሙፍረድ።

[12] ዝኒ ከማሁ።

[13] ኢማም ሙስሊም፣ ሶሂህ ሙስሊም።

[14] ኢማም አል - ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል - ቡኻሪ።

[15] ኢስላማዊው አስተምህሮት የፈጣሪ አላህን ማንነትና ባሕሪያቱን ንግግሩን ጨምሮ በሰው ወይም በአንዳች ግዑዝ ነገር መመሰልንና ማመሳሰልን ፈጽሞ ይከለክላል። ሙስሊም የሆነ ሰው የአላህን ቃል አስመልክቶ ሲናገር እነዚያ ቃላት በፈጣሪ የተመረጡና ወደባሮቹ እንዲደርሱ የተደረጉ መሆናቸውን ከመቀበል (እውቅና ከመስጠት) ባለፈ በምንም መልኩ የፈጣሪ (አላህ) ከፍሎች አድርጎ አይወስዳቸውም።

[16] ፊሊፕ ኬ ሃይት ሂስትሪ ኦቭ ዘ - አረብስ ፍሮም ኸርሊየስት ታይምስ ቱ ዘ ፕረዘንት ገጽ 93

[17] ኢማም አድ - ዳሪሚ ሱናን አድ - ዳሪሚ።

[18] ኢማም አት - ቲርሚዚ፣ ሱነን።

[19] ኢማም አል - ቡኻሪ፣ ሰሂህ አል - ቡኻሪ።

[20] ዝኒ ከማሁ።

[21] ቁርኣን 29 59 እና 16 42ን በተጨማሪ ተመልከት።

[22] ኢማም ሙስሊም ሶሂህ ሙስሊም።

[23] አል - በይሐቂ ደላኢል አል - ኑቡዋህ።

[24] ኢማም አል - ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል - ቡኻሪ።

[25] ዝኒ ከማሁ።

[26] ተሚም አንሳሪ፣ ደስቲኒ ዲስኢረፐትድ። ኤ - ሂስትሪ ኦቭ ዘ ወርልድ ስሩ አረብ አይስ ገጽ 128 - 129።

[27] ነቢል ማታር፣ ተርክስ፣ ሙርስ ኤንድ ኢንግሊሽ ኢን ዘ ኤጅ ኦቭ ዲስከቨሪ ገጽ9።

[28] ካረን አርምስትሮንግ "ሜዲቫል ፕሪጁዲስ ስቲል ኢንፉለንስስ ዘ ዌስትስ ቪው ኦቭ ኢስላም"

Dawn http//www.hartford-hwp.com/archives/276/095-html (accessed Decamber, 2009)::

[29] ከትድ ኢን ሮሳሞንድ ማርክ፣ በዛር ቱ ፒዛ ኢስላሚክ ትሬድ ኤንድ ኢታሊያን አርት ገጽ 1300 - 1600።

[30] ጀናታን ሊዮንስ፣ ዘ - ሃውስ ኦቭ ዊዝደም ገጽ147።

[31] ኑሰይቢያ ቢንት ከዕብ (ረ.ዐ) የመዲና ሴት ስትሆን በኡሑድ ጦርነት ብዙዎቹ ተዋጊዎች ቦታቸውን በመልቀቅ በተበታተኑበት ጊዜ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጐን በመሆን ተዋግታለች። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቆየት ብለው ሲናገሩ "በሁሉም አቅጣጫ ስዞር ኑሰይቢያ በጀግንነት ስትዋጋ ተመለከትኩ" ብለዋል። ኑሰይቢያ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ቃል ኪዳን ከገቡት የመጀመሪያዎቹ የአቀባ ሰዎች አንዷ ናት። በዚህም የተነሣ አቡበከርና ኡመርን (ረ.ዐ) ከመሣሠት አክብሮትን ያተረፈች ሲሆን ምክሯንም ያዳምጡ ነበር።

[32] ሰይድ ሁሴን ናስር፣ ዘ - ኧርት ኦቭ ኢስላም ገጽ 251።

[33] ኢማም አት - ቲርሚዚ፣ ሱነን።

[34] ኢማም አል - ቡኻሪ፣ ሰሂህ አል - ቡኻሪ።

[35] ሂውስተን ሰሚዝ፣ ኢስላም፣ ኤ - ኮንሳይስ ኢንትሮዳክሽን ገጽ 65።

[36] ስቴፈን ሮበርትሰን "ኤጅ ኦቭ ኮንሰንት ሎውስ" ችልድረን ኤንድ ዩዝ ኢን ሂስትሪ።

[37] Elizabeth landau "men see bikini clad women as objects, psychologists say:"

http//www.cnn.com/2009 /health/20/19/women.bikinis-objects/ (accessed November,2009).

[38] አቡ ዳውድ ሱነን።

[39] መሐመድ አል - ጣሂር አት - ተህሪር ወአት - ተንዊር።

[40] ኢማም አል - ቡኻሪ ሶሂህ አል - ቡኻሪ።

[41] ዝኒ ከማሁ።

[42] ኢማም አድ - ደይለሚ ሙሰነድ አል - ፊርደውስ።

[43] ኢማም አጥ - ጦበሪ፣ ታሪኽ አጥ - ጦበሪ፣ ታሪኽ አል - ኧሊፋ አል - ራሺዳ።

[44] Fred Donner, "The sources of Islamic Conceptions of war" in Dr.Sherman Jackson, "

Jihad and the modern world," seaon I (spring, summer 2003)

[45] ዶክተር ሸርማን ጃክሰን "ጂሃድ ኤን ዘ ሞደርን ወርልድ" ሲዝን I (ስፕሪንግ ሰመር 2003) 9

[46] James zogby, "Saudis Reject Bin laden and Terrorism," Media monitors Network,

August 12,2003, http//www.Mediamonitors.net/209by 99-html (accessed

November,2009).

47 http//www.int-review.orglter42ahtml (accessed November, 2009)

48 አማም አል-ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል-ቡኻሪ።

49 such as the now infamous cartoons printed in the dannish newes paper

50 ክርስቶፎር ዲኪይ "ክርስቲያን ሬጅ ኤንድ ሙስሊም ሞደሬሽን" ኒውስዊክ, ሜይ 27 2008።

51 ኢማም አል-ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል-ቡኻሪ።የአስራ አምስተኛው መቶ ዘመን ምሁር አሽ ሻቲቢ ኢስቲሕሳንን በማስመልከት እንዲህ ብለዋል። "እስቲህሳን በባህሪው ከማመሳሰል ይልቅ ምርምርን ያስቀድማል። ማንም እስቲህሳን የሚያደርግ ሰው ስሜቱንና ዝንባሌውን ብቻ አያዳምጥም። ከዚያ ይልቅ የሕግ ሰጪውን አካል (የፈጣሪውን) ፍላጐት በማዳመጥ ውሳኔ ላይ ይደርሳል።..." (አል-መዋፈቃት ክፍል 4 ገጽ 116)

52 ኢማም አህመድ ሙሰንድ።አዚዝ አል-ሃርቢ አን ኢስላሚክ ፐርስፔክቲቭ ኦን ዶሜስቲክ ቫዮለንስ ገጽ 6። ፎርድሃም ኢንተርናሽናል ሎው ጆርናል 195፣ ዲሴምበር 2003።

53 ሃሺም ካሚል ፕሪንሲፕልስ ኦፍ ኢስላሚክ ጁሪስፕሩደንስ I ገጽ 53።ሜኖካል ማሪያ ርዛ ዘ-ኦርናመንት ኦፍ ዘ ወርልድ፣ ሀው ሙስሊምስ፣ ጀውስ፣ ኤንድ ክርስቲያንስ ክርኤትድ ኤ ካልቸር ኦቭ ቶለረንስ ኦን ሜዲቫል ስፔይን ገጽ 11-12

54 ዝኒ ከማሁ 162።ኢማም አል-ቡኻሪ፣ ሶሂህ አል-ቡኻሪ።

የቃላት መፍቻ

ሐ

ሐቅ፡ እውነት ወይም የተረጋገጠ ነገር።

ሐዲስ፡ የነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) የተመዘገቡ ንግግሮችና ድርጊቶችን

ሐጅ፡ ወደ ካዕባ (መካ) በመሄድ የሚፈጸም ሃይማኖታዊ ክንዋኔ ሲሆን ከኢስላም ማዕዘናትም አምስተኛውና የመጨረሻው ነው።

ሒጃብ፡ ኢስላማዊ የሴቶች አለባበስ።

ሒጂ፡ ወደ መካ የተጓዙ ምዕመናን የሚጠሩበት ስያሜ።

ሂጅራ፡ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ስደት።

መ

መዕሩፍ፡ በኢስላማዊ የፊቅህ ጥናት መልካም መሆኑ በግልጽ የታወቀ ነገር።

መድረሳ፡ ኢስላማዊ የትምህርት ተቋም።

መጋዚ፡ ወታደራዊ ዘመቻዎች። በስነጽሑፍ ስለ ወታደራዊ ዘመቻ ሲጠቀስ ጥቅም ላይ የሚውል የቀጥተኛ አገላለጽ ቃል።

ሙአመለት፡ የዕለት ተዕለት (የተለመዱ) የሥራ እንቅስቃሴዎች።

ሙአዚን፡ ለሶላት ጥሪ የሚያደርግ ሰው።

ረ

ረመዳን፡ በኢስላማዊ የዘመን አቆጣጠር ቅዱስ የሆነ ወር። በዚህ ወር ነበር ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) በሂራ ዋሻ ተቀምጠው እያሉ የመጀመሪያው መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) የወረደላቸው። በረመዳን ወር እድሜያቸው ለአቅመ አዳም (ሔዋን) የደረሰና ጤነኛ የሆኑ ሙስሊሞች እንዲፆሙ ግዴታ ተደርጎባቸዋል።

ሰ

ሰለም፡ ሰላም።

ሰይዱና፡ የክብር መጠሪያ ሲሆን የሃይማኖት አባቶችን በተለይ ለመጥራት ያገለግላል። ትርጉሙ ‹አለቃችን ወይም ሹማችን› ማለት ነው።

ሱና፡ 1 የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ፈለገ ሕይወት።

2 ግዴታ ያልሆኑ ሆኖም ግን ቢፈጸሙ ምንዳ የሚያስገኙ አምልኮታዊ ተግባራት።

ሶደቃ፡ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ምጽዋት።

ሸ

ሸሪዓ፡ ኢስላማዊ የሕይወት ሥርዓት የተመሠረተበት መለኮታዊ ሕግ።

ሹራ፡ ምክክር።።
ሽርክ፡ ከአላህ ጋር አንዳች ተጋሪን የማድረግ ሂደት።።

ቀ

ቁርአን፡ በመልአኩ ጅብሪል (ዐ.ሰ) አማካኝነት ለነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) የወረደላቸው መለኮታዊ መጽሐፍ።።

አ

አላህ፡ የአንዱ ፈጣሪ የአረብኛ መጠሪያ ስያሜ ሲሆን ‹አል› እና ‹ኢላህ› ከተባሉ የአረብኛ ገላጭ ቅጽሎች የተዋቀረ ነው።።
አዳብ፡ ትክክለኛ ሥነ ምግባር።።
ኡማ፡ ሙስሊም ማህበረሰብ።።
ኡርፍ፡ በኢስላማዊ የፊቂህ ዕውቀት የተለመደ ባሕላዊ የሆነና ቅድሚያ የሚሰጠው አሰራር።።
ኢጅቲሃድ፡ የኢስላም ሃይማኖት ሕግጋትን ለማበጀት የሚደረግ ምሁራዊ ጥረት።።
ኢስቲህሳን፡ በኢስላማዊ የፊቅህ ጥናት ነገሮችን መልካም አድርጎ የመቀበል የመምረጥ) ስልት።።

ከ

ከዕባ፡ የመጀመሪያውና አንዱን አምላክ (አላህን) ብቻ ለማምለክ የተሠራ ቤት
ኮንቪቨንሲያ፡ በሙስሊም ስፔይን (አልአንደሉሲያ) በስፋት ይሰራበት የነበረው የተለያዩ እምነቶች ተቻችለው የሚኖሩበት ባሕል።።

ኸ

ኸሊፋ፡ የሙስሊሙ ማሕበረሰብ መሪ።።
ኸዋሪጅ፡ አራተኛውን በትክክል የተመሩ ኸሊፋ ዓሊ ኢብን አቡ ጣሊብን (ረ.ዐ) የገደለና ከሙስሊሙ ኡማ ያፈነገጠ ሃራጥቃ(ቡድን)።።

ዘ

ዘካት፡ የአንድ ሰው ሃብት የተወሰነ ደረጃ (ኒሳብ) ሲሞላና ያ ገንዘብ ዓመት ሲደፍን ለድሆችና ለምስኪኖች በግዴታነት የሚከፋፈል ምጽዋት ነው። አንድ ሰው ከገንዘቡ ላይ 2.5 ከመቶ የሚሆነውን አውጥቶ መክፈል ግዴታ (ዋጅብ) ይሆንበታል። ይህም የሚሆነው ሰውየው ዘካ የመክፈል አቅም ሲኖረው ነው። ያንን ካላደረገ ግን ከኢስላም መዕዘናት አንዱን እንዳጎደለ ይቆጠራል።
ዚምማ፡ በሙስሊሞች ቁጥጥር ሥር በሚገኝ ምድር የሚኖሩና በሙስሊሞች የጥበቃ ዋስትና የተሰጣቸው ሌሎች ሕዝቦች የሚተዳደሩበት ስርዓት (ደንብ)

ጀ

ጂዝያ፡ በሙስሊም መስተዳድር ስር የሚገኙ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የጥበቃ
ዋስትና ያገኙ ዘንድ ለመስተዳድሩ የሚከፍሉት ግብር (ታክስ)።።

ጃሂሊያ፡ ቅድመ ኢስላም የነበሩት ዘመናት የሚጠሩበት የኋላ ቀርነትና የድንቁርና ስርዓት መጠሪያ።።
የሚያመለክት ቃል ሲሆን ከቁርኣን ቀጥሎ ሁለተኛው የኢስላም ሸሪዓ መሰረት ነው።።

ጃሂሊያ፡ ቅድመ ኢስላም የነበሩት ዘመናት የሚጠሩበት የኋላ ቀርነትና የድንቁርና ስርዓት መጠሪያ።።
ጂዝያ፡ በሙስሊም መስተዳድር ስር የሚገኙ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የጥበቃ
ዋስትና ያገኙ ዘንድ ለመስተዳድሩ የሚከፍሉት ግብር (ታክስ)።።

ፊ

ፊጥራ፡ ማንኛውም ሰው ሲወለድ በተፈጥሮ የሚኖረው ንጽህና።።

ዋቢ መጽሐፍት

Abdul Rauf, Feisal. *What's Right with Islam*. San Francisco, Harper Collins, 2004.

Abou El Fadl, Khaled. *The Great Theft: Wrestling Islam from the Extremists*. New York: Harper Collins, 2005.

Ansary, Tamim. *Destiny Disrupted: A History of the World Through Islamic Eyes*. New York: PublicAffairs, 2009.

Arberry, A.J. (Editor). *The Koran Interpreted: A Translation*. New York: Touchstone, 1955.

'ĀshÚr, Muḥammad alṬāhir al-. *Al-Taḥrīr wa al-Tanwīr.*

——— *Ibn Ashur: Treatise on* Maqasid al-Shariah. Herndon: International Institute of Islamic Thought, 2006.

Chittick, William (Editor). *The Inner Journey: Views from the Islamic Tradition*. Sandpoint: Morning Light Press, 2007.

Eaton, Charles. *Remembering God: Reflections on Islam*. Chicago: Kazi Publications, 2000.

Haley, Alex. *The Autobiography of Malcolm X*. Ballantine Books/ Random House, Inc., 1964.

Homerin, Emil (tr.). *'Umar ibn al-Fāri\: Sufi Verse, Saintly life*. New Jersey, Paulist Press, 2000.

'Iyad, Qadi. *Muhammad, Messenger of Allah*. Granada, Medina Press, 1991.

Kamali, Mohammad Hashim. *Principles of Islamic Jurisprudence*. London, Islamic Texts Society, 2005.

Khalidi, Tarif. *The Muslim Jesus: Sayings and Stories in Islamic*

Literature. Cambridge, Harvard University Press, 2001.

Lavoie, Louis. *Tides of History: A Review of Three Historic Tides That Have Helped Shape the* 20*th Century, Islam, Russia, and Science*. Plymouth, L. Lavoie, 1997.

Lewis, David Levering. *God's Crucible: Islam and the Making of Europe,* 570–1215. New York, Norton, 2008.

Lyons, Jonathan. *The House of Wisdom: How the Arabs Transformed Western Civilization*. New York, Bloomsbury Press, 2009.

Mack, Rosamond E. *Bazaar to Piazza: Islamic Trade and Italian Art,* 1300–1600. Berkeley, University of California Press, 2002.

Mamdani, Mahmood. *Good Muslim, Bad Muslim: America, The Cold War, and the Roots of Terror.* New York, Doubleday, 2004.

Matar, Nabil. *Turks, Moors, & Englishmen in the Age of Discovery.* New York, Columbia University Press, 1999.

Menocal, Maria Rosa. *The Ornament of the World, How Muslims, Jews, and Christians Created a Culture of Tolerance in Medieval Spain*. Boston, Little, Brown, and Company, 2002.

——— *The Arabic Role in Medieval Literary History, A Forgotten Heritage*. Philadelphia, University of Pennsylvania Press, 1983.

Nasr, Seyyed Hossein. *The Heart of Islam*. San Francisco, Harper Collins, 2002.

O'Shea, Stephen. *Sea of Faith: Islam and Christianity in the Medieval Mediterranean World*. Vancouver, Douglas and McIntyre Ltd., 2006.

Poplak, Richard. *The Sheikh's Batmobile: In Pursuit of American Pop Culture in the Muslim World*. Toronto, Penguin Books, 2009.

Reston, James Jr. *Defenders of the Faith: Charles V, Suleyman the Magnificent, and the Battle for Europe,* 1520-1536. New York, Penguin Press, 2009.

Reston, James Jr. *Warriors of God: Richard the Lionheart and Saladin in the Third Crusade*. New York, Doubleday, 2001.

Ruskin, John. *The Stones of Venice*. New York, Da Capo Press, 1985

Sedgewick, Mark. *Islam and Muslims. A Guide to Diverse Experience in a Modern World*. Boston, Intercultural Press, 2006.

Smith, Huston. *Islam: A Concise Introduction*. San Francisco, Harper, 2001.

Winter, Tim (Editor). *The Cambridge Companion to Classical Islamic Theology*. Cambridge, Cambridge University Press, 2008.

ARTICLES

Abd-Allah, Umar Faruq. *One God, Many Names*, Nawawi Foundation, Chicago, 2004.

Al-Hibri, Azizah. An Islamic Perspective on Domestic Violence, *Fordham International Law Journal* 195, December 2003.

Armstrong, Karen. "Medieval Prejudice still influences the West's View of Islam," *Dawn*, June 21, 2002.

Dickey, Christopher. "Christian Rage and Muslim Moderation," *Newsweek*, May 27, 2008.

The Editors. "Islam and Modernity," *America: The National Catholic Weekly*, November 12, 2001.

Friedman, Thomas. "If it's a Muslim Problem it Needs a Muslim Solution," *New York Times*, July 8, 2005.

Jackson, Sherman. Jihad and the Modern World, *Journal of Islamic Law and Culture*, Spring / Summer, 2002.

Landau, Elizabeth. "Men See Bikini Clad Women as Objects," cnnhealth.com, April 2, 2009.

Sharrock, David. “Spanish Muslims Issue ‘Fatwa’ Against Bin Laden,” *The Times Online*, March 12, 2005.

Stone, Caroline. “Ibn Fadlan and the Midnight Sun,” *Saudi Aramco World*, March / April 1979.

Tehranian, Majid. *Islam and the West: Hostage to History?* University of Hawaii, December, 25, 1997.

Zaimeche, Salah. “The Little Known Tolerant and Humane Aspects of Muslim Civilization,” *Foundation for Science, Technology and Civilization*, October, 2003.

Zakaria, Rafia. “A Response to Modernity,” *The Hindu*, April 13, 2009.

Zuroff, Avraham. “Exhibition Honors Muslim Holocaust Rescuers,” *Israel National News*, January 25, 2009.

OTHER

Abd-Allah, Umar Faruq. *Famous Women in Islam* (Recorded Lectures).


İhsanoğlu, Ekmeleddin. *A Culture of Peaceful Coexistence*, (speech) Howe Center, Stevens Institute of Technology, May 13, 2004.

Robertson, Stephen. “Age of Consent Laws,” *Children and Youth in History*, Item #230, http://chnm.gmu.edu/cyh/teaching-modules/230 (accessed November 2009).

Yusuf, Hamza. *Removing the Silence on Domestic Violence*, sermon held in San Ramon, California, February 20, 2009.

Interview by Kol Hair Jerusalem Weekly, excerpted by orthodoxytoday.org, March 31, 2004.

“Islam and Modernity,” *America Magazine*. http://www.americamagazine.org/content/article.cfm?article_id=1206 (accessed July 2009).



ስለ መጽሐፉ

ይህ በምዕራባዊ ሙስሊም ሴት የተጻፈ መግቢያ ወርቃ መጽሐፍ ምዕራባዊውን አንባቢ ስለ እስልምናና ሙስሊሞች ግ ንዛቤ ለማስጨበጥ ያለመ ነው። ም ንም እንኳን በተለያዩ ሙሁራንና ታሪክ ጸሓፊያን የተዘጋጁ መጽሐፍት ስ ለ እምነቱ በቂ ዕውቀት የሚያስጨብጡ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ ዛሬ ላይ ያሉ የሙስሊም ወንዶችንና ሴቶችን ስሜታዊና ሃይማኖታዊ ተሞክሮዎችን ማስተላለፍ ይሳናቸዋል። መንፈሳዊ ጉጉታቸው፣ ስለ ሰላት ውበት ያላቸው አረዳድ፣ የሀጅ ክብርና ውጣ ውረዶች፣ ለሥነ-ጥበብና ባህል ያበረከቱት አስተዋጽኦ... በአብዛኛው በልብ ውስጥ ተደብቀው የሚቆዩ ወይም በታሪክ ገጾች ውስጥ ተደብቀው የሚያልፉ ያልተገለጹ እውነታዎች ናቸው። ይህ ስራ የእስልምናን፣ የቅዱሳን መጻህፍትንና ታሪክን መሰረታዊ አስተምህሮቶች የሚያቀርብ ቢሆንም ሙስሊሙ ስለ ምዕራቡ ባህል ያለውን በአብዛኛው የተደበላለቀ ሥነ-ልቦናም በማብራራት ለማሳየት ይሞክራል። ፀሓፊዋ በተጨማሪም ሴቶችና ኢስላምን አስመልክቶ የሂጃብን ባህል፣ ሴቶችን ማግለል እና አሁን ባሉ ሙስሊም ማህበረሰቦች ውስጥ ሴቶች ያላቸውን ሰፊ የሚና ልዩነት የሚዳስሱ ነጥቦችን በማካተት አብራርተዋል።

800 555 اتصل على JUST CALL

zhic.uae @zhic_uae zhic_uae #zhic

www.zhic.ae contact@abudhabi.ae

دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

ISBN 9789948220572